ሶተሪያ መጽሐፍ ቅዱስ ኮሌጅ

# የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ከፋፍሎ ማጥናት

በፓ/ር ዳዊት ጥላሁን

## ማውጫ


1. መጻሐፍትን ከፋፍሎ ማጥናት ................................................ 2
2. መከፈል......................................................................... 2
3. መጽሐፍ ቅዱስ ..............................................................4
4. የመጽሐፍ ቅዱስ መዋቅር ................................................11
5. መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማን ይናገራል?.....................................11
6. መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረለት ህያው ቃል ...............................14
7. ሉቃስ 24.......................................................................17
8. ጳውሎስ የሰበከው ኢየሱስን ነው!........................................22
9. መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና በምን መልኩ ነው የምናነበው/ የምናጠናው? ሶስት ጥያቄዎችን እንጠይቃለን።.........................................23
10. መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርላቸው ሶስቱ ሰዎች........................29
11. ሶስት ህዝብ ሲያይ ታዲያ እግዚአብሔር ስለምን እያወራ ነው?30
12. ሰባቱ ክፍለ ዘመናት .......................................................32
13. አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስናጠና መጠየቅ ያለብን አምስት ነገሮች........................................................................39
14. በረከት በብሉይ ኪዳን፣ በመንግስቱ ወንጌል እና በአዲስ ኪዳን51
15. እምነት በብሉይ ኪዳን፣ በመንግስቱ ወንጌል እና በአዲስ ኪዳን 58

# መጻሐፍትን ከፋፍሎ ማጥናት

የዚህ ኮርስ መሪ ጥቅስ ያለው በ2ኛ ጢሞ 2፡15 ላይ ያለው ነው። *“የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር የማያሳፍርም ሰራተኛ ሆነህ የተፈተነውን ራስህን ለእግዚአብሔር ልታቀርብ ትጋ።”* ይህንን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል መከፋፈል የሚለውን ርዕስ የወሰድነው ከዚህ ጥቅስ ነው። “የእውነትን ቃል በቅንነት የሚናገር” አማርኛችን “በቅንነት የሚናገር” የሚለውን እንግሊዝኛው ‘rightly dividing the word of truth’ ይለዋል። የእውነትን ቃል በትክክል ከፋፍለህ የምታቀርብ ሰው እንድትሆን፣ የማታሳፍር ሰራተኛ ሆነህ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ። ራስህን በሰው ፊት ሳይሆን በእግዚአብሔር በራሱ ፊት ልታቀርብ ትጋ። ለምን? በእግዚአብሔር ፊት የእግዚአብሔር ሠራተኛ እና የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሰው ሲመላለስ፣ አሳፋሪ ሰራተኛ ሊሆን ይችላል ደግሞ የማያሳፍር ሠራተኛ ሊሆን ይችላል። ይህ ጳውሎስ ለጢሞቴዎስ የፃፈው ደብዳቤ ነው። ጢሞቴዎስ ሐዋሪያዊ ውክልና ከራሱ ከጳውሎስ የተቀበለ የጳውሎስ እውነተኛ መንፈሳዊ ልጅ የሚለው ሰው ነው። እንግዲህ ለልጁ ጳውሎስ ምክሩ ምን ነበረ? የማያሳፍር ሰራተኛ ሆነህ ራስህን በእግዚአብሔር ፊት ልታቀርብ ትጋ። አንተ የማታሳፍር ሰራተኛ የምትሆነው የእውነትን ቃል በትክክል ከፈፍለህ በማቅረብ ነው።

# መከፈል

የእውነትን ቃል በትክክል ከፋፍለህ የምታቀርብ ሁን። ደግሞም በማቅረብ ውስጥ እግዚአብሔርን ታሳፍራለህ ወይንም የማታሳፍር ሆነህ ትገኛለህ። ማሳፈርም አለማሳፈርም ያለው የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል በመከፋፈል ውስጥ ነው። ጳውሎስ ይህንን ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት ለጢሞቴዎስ ብቻ የተላከ ደብዳቤ ነው፣ ለቤተክርስቲያን የተላከ ደብዳቤ አይደለም። ጳውሎስ ይህንን ለጢሞቴዎስ ሲጽፍለት አዲስ ኪዳን እንደ እኛ ተጠርዞ በመልዕክት ደረጃ ለጢሞቴዎስ እጁ ላይ አልነበረም። እጁ ላይ የነበሩት 39ኙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ብቻ ናቸው። በእነዚህ በ39ኙ መጽሐፍት ውስጥ ግን የእግዚአብሔርን ቃል አውጥተህ ስትሰብክ፣ ስታስተምር አንተም አውጥተህ ስትረዳው የማታሳፍር ሠራተኛ መሆን አለብህ። በማለት ለእውነተኛ መንፈሳዊ ልጁ የማያሳፍር ሰራተኛ እንዲሆንለት አጥብቆ

ይመክረዋል። ከዚህ መልዕክት ውስጥ እኛም የማያሳፍር ሠራተኛ ላለመሆን የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል ከፋፍለን እናጠናለን።

የእግዚአብሔርን ቃል በትክክል መከፋፈል በሕይወቱ ያልተማረ ሰው የእርሱ ያልሆነን መልዕክት ለእርሱ እንደተጻፈ አድርጎ በመውሰድ ሕይወቱን ያስረዋል። ያም ብቻ ሳይሆን ለሌሎችም ሲያስተምር አሳፋሪ ይሆናል። ለምሳሌ *"ሰነፍ በልቡ እግዚአብሔር የለም ይላል"* የሚለውን ቃል *"ይኸው የእግዚአብሔር ቃል እራሱ ይላል"* ብሎ የሚከራከር አለ። ግን መጽሐፍ ቅዱሳችን የተናገረው ሰነፍ ይላል ብሎ ነው እንጂ እግዚአብሔር የለም ብሎ አይደለም ማለት ነው። ድንገትም ደግሞ ከኢዮብ መጽሐፍ ብድግ አድርጎ *"እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ የእግዚአብሔር ስም የተባረከ ይሁን"* የሚልም ሰው ደግሞ አለ። እውነት ነው። የእግዚአብሔር ስም መባረክ አለበት። የጽድቅ ንግግር እና መልካም ደስ የሚያሰኝ ይመስላል። ይሔ ያለ አግባብ ያለ ቦታው በትክክል ሳይከፋፈል የተወሰደ ነው። ምክንያቱም የኢዮብን መጽሐፍ በደንብ ስታጠኑት እግዚአብሔር ከኢዮብ አልወሰደበትም። ወስዶበት ቢሆን ኖሮ አይመልስለትም ነበር። እግዚአብሔር እንደወሰደብን ካመንን በወሰደብን ነገር ሁሉ አሜን ብቻ ነው ማለት ያለብን። ምክንያቱም *"ዳኛ ምነው በተገኘ እንዲፈርድልኝ"* ብሎ እንደ ኢዮብ መፎከር አያስፈልግም እንደ እግዚአብሔር ታላቅ የሆነ አካል ስለሌለ።

ስለዚህ፣ የዚህ መጽሐፍ ዓላማ ምንድነው? የዚህ መጽሐፍ ዓላማ መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉውን ማንበብ እና ማጥናት ሳይሆን ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ለዚህ ዘመን የሚናገረውን ፈልጎ ማግኘት ነው። በተለይ በሰው ሜዳ ስንዳክር እንዳንገኝ ወይም ደግሞ በማይመለከተን ሕይወት ውስጥ ስንዳክር እንዳንገኝ እግዚአብሔር ለእኛ በዚህ ዘመን ላለን ሰዎች ያዘጋጀውን የራሱን በረከት የራሱን እውነት ፈልገን በማግኘት በሕይወታችን ስኬታማ እንድንሆን ነው ወይንም ደግሞ የሚጠበቅብንን ድል ነሺ የክርስትና ሕይወት እንድንኖር ነው ማለት ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናገኘው ሰባት የተለያዩ ክፍለ ዘመናት አሉ።

- የንጽህና ዘመን
- የህሊና ዘመን
- የሕግ ዘመን

- የተስፋ ዘመን
- የሰው አገዛዝ ዘመን
- የጸጋ ዘመን
- የሺው ዓመት መንግስት

በእያንዳንዱ ክፍለ ዘመን እግዚአብሔር መልዕክቱ ምን ነበር የሚለውን ተንትነን እናያለን። በተለይ ዛሬ ከክርስቶስ መስቀል በኋላ ክርስቶስ ኢየሱስ ከሞተልን በኋላ የምንኖር ሰዎች በምንኖርበት በዚህ በጸጋ ዘመን የእኛን መልዕክት ፈልገን እናገኛለን። በምናገኘው በእኛ መልዕክት ውስጥ ነው ሙሉ በሙሉ የከበረን ሕይወት የምንኖረው። ከሙሉ መጽሐፍ ቅዱስ ስዕል ውስጥ የምናገኘው የዚህን የጸጋን ዘመን አጠናን እና አከፋፈል ለይተን እናየዋለን። አንዳንድ መልዕክቶች መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ እኛን ያላማከሉ ሆነው ልናገኝ እንችላለን። በወቅቱ ለነበሩ ሰዎች የተነገረና እነርሱን ብቻ ተደራሽ ያደረገ መልዕክት ዛሬ ደግሞ እኛ እንደሚመለከተን አድርገን ስንኖርባቸው ወይም ለመኖር ለመፈፀም ስንታገል ሕግን እየቀላቀልን ስንሰቃይ ምንገኝበት ብዙዋች አለን።

ከመጽሐፉ ጠቃሚነት አንፃር ከንግግር ባለፈ ጊዜ ወስዶ መማር፣ ማጥናት፣ ማሰላሰል አልፎም ደግሞ ከእናንተ ባለፈ ለሌላውም እንድታስተምሩበት ይሄ ትልቁ መሻቴ ነው።

## መጽሐፍ ቅዱስ

የምንማረው ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ስለሁነ፣ ከመጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔርን እናምናለን። እግዚአብሔርን ከየትም አናገኘውም! ከመጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው የምናገኘው። ምን ማለት ነው? መጽሐፍ ቅዱስ እግዚአብሔር እንዳለ አምኖ ባይጀምርልን እግዚአብሔር እንዳለ ሌላ መጽሐፍ አይነግረንም ነበር። እግዚአብሔር እንዳለ አስረግጦ በመናገር ስለያዝነው ኢየሱስ አስረግጦ በማውራት ወደር የሌለው ብቸኛው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለ መጽሐፍ ቅዱሳችን መሰረታዊ ነገሮችን እንይ።

1. መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ ቁጥር 1 እድሜ ጠገብ ነው። እድሜው እስካሁን ወደር የለውም። እሱን የሚተካ ሌላ መጽሐፍ እስካሁን ድረስ ያልተገኘለት በእድሜው ብዛት ወይም በእድሜው ርዝማኔ አንደኛ ቁጥር 1 የሆነ መጽሐፍ ነው። በሌላ አነጋገር የሁላችንንም እድሜ የሚበልጥ እድሜ አለው ማለት ነው። እድሜው ሁላችንንም የሚበልጥ እጅግ በጣም እድሜው የቆየ ታላቅ መጽሐፍ ነው።

2. ሌሎች መጽሐፍቶች የመሰከሩለት መጽሐፍ ነው። ሌሎች መጽሐፍቶች መጽሐፍ ቅዱስ የሚገርም እና የእግዚአብሔር መጽሐፍ እንደሆነ መስክረዋል። አንደኛ የመሰከረው ቁርአን ነው።

3. እስካሁን ድረስ በሽያጭ ተወዳዳሪ የሌለው ነው። በዓመት ውስጥ ከ11-14 ሚሊዮን መጽሐፍ ይሸጣል። የትኛውም ሰው የፃፈው መጽሐፍ የዚህን ያህል የተሸጠ አንድም መጽሐፍ የለም። እጅግ በጣም ትልቅ ተሸጠ የተባለው አንድ ሚሊዮን ቅጂ ከተሸጠ በሚሊዮን ኮፒ ተሸጧል የሚገርም መጽሐፍ ተብሎ ለብዙዎች መነጋገሪያ የሚሆን መጽሐፍ ይሆናል። መጽሐፍ ቅዱስ ግን በአንድ ሚሊዮን ደረጃ ሳይሆን በየዓመቱ በትንሹ 11 ሚሊዮን ቅጂ በመሸጥ በሽያጭ ወደር የሌለው መጽሐፍ ነው። ማተሚያ ማሽን የተሰራው ለመጽሐፍ ቅዱስ ሲባል ጭምርም ነው ነው።

ወደዚህ ዓለም እንኳን ማተሚያ ማሽንን ያስገባው እጅ ጽሑፍን ወደ ህትመት የቀየረው የመጽሐፍ ቅዱስ መኖር ነው። ሰዎች ጊዜ ወስደው ነበር የሚያባዙት እና በብራና ላይ በጥንቃቄ ይፃፍ ነበረ። ካህናቶች ያባዙት የነበረው ከትልቅ ጥንቃቄ ጋር ነበር። ያንን ሁሉ ትግል ለማሳረፍ ሲባል በመጽሐፍ ቅዱስ በወረቀት ታትሞ እጃችን እንዲገባ የእግዚአብሔር በጎ ፈቃድ ሆነ። እግዚአብሔር ለሰዎች ጥበብን በመስጠት ለመጀመሪያ ጊዜ ማሽን ተሰርቶ የታተመው መጽሐፍ ቅዱስ ነው። እግዚአብሔር ይመስገን! ይሔ በጣም ድንቅ መጽሐፍ ነው!

4. እስካሁን ቁጥር አንድ ተነባቢ መጽሐፍ ነው። ታውቃላችሁ መጽሐፍ ቅዱስ እንደሌሎች መጽሐፎች አንዴ አንብባችሁት ገብቷችሁ የምትጥሉት መጽሐፍ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ ከእድሜያችሁ እስከ እድሜያችሁ ሁሌ ተነባቢ የሆነ መጽሐፍ መልኩን ሳይቀይር ማንነቱን ሳይቀይር ቃሉን ሳይቀይር ግን ሁል ጊዜ በየቀኑ የምናነበው ቢኖር ብቸኛ ተነባቢ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የየትኛውም ዓለም ምርጥ

ጸሐፊ የፃፈው ድርሰትም ይሁን መንፈሳዊ እውነታን የያዘ መጽሐፍ ሁል ጊዜ ለማንበብ የሚያስለች ስለሆነ እናቆመዋለን። ብዙውን ጊዜ በጣም አሪፍ የተባለ መጽሐፍ ስናገኝ 3 ጊዜ ነው የምንደግመው። ከዛ በኋላ በቃላችንም ስለምናውቀው እንተወዋለን። መጽሐፍ ቅዱስ ግን እስካሁንም ድረስ በዓለም ላይ ወደር የሌለው ብቸኛ እና አንደኛ ተነባቢ መጽሐፍ ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

5. በእድሜ ዘመኑ ሁሉ ተቃውሞ የበዛበት መጽሐፍ ነው። በ1900 ዓ.ም ላይ መጽሐፍ ቅዱስን በሙሉ የማቃጠል ሥራ ተሰርቶ ነበር። ብዙ ሚሊዮን ቅጂዎች እስከመቃጠል ደርሰዋል።ተቃጥሎ ያልጠፋ መጽሐፍ ቢኖር መጽሐፍ ቅዱሳችን ነው። በመላው ዓለም የትኛውም መጽሐፍ ተቃውሞ አይደርስበትም ትልቅ ተቃውሞ የሚደርስበት መጽሐፍ ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ምክንያቱ ደግሞ የእግዚአብሔርን እውነት በውስጡ ስለያዘ ነው። ሌላው መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ ተግዳሮቶች የሚገጥሙን ከዚሁ የተነሳ ነው።

ሌላ መጽሐፍትን ብታነቡ እንኳን ቀላል ነው ብዙ አይከብዳችሁም። መጽሐፍ ቅዱስን እንዳታነቡ ግን ያለ የሌለ ተግዳሮቶች ይገጥሟችኋል። ምክንያቱም እውነት ያለው በቃሉ ውስጥ ስለሆነ ነው። ስለዚህ ሰዎች ቃሉን እንዳያነቡት፣ እንዳያጠኑት ወይም በቃሉ ውስጥ ያለውን እውነት እንዳይረዱት በተለያየ መልኩ ተግዳሮት አለ። እኔ እንኳን በእድሜዬ የማውቀው ተበልቶ አይነበብም ተብዬ ትራስ ሲደረግ ነው። ሰዎች አንብበውት ነፃ እንዳይወጡ ያለው ተፅእኖ ቀላል አይደለም። አጋንንት ትግሉ ሰዎች እንዳያነቡት ነው። ይሁን እንጂ ሰው ሁሉ ተንቀሳቃሽ መጽሐፍ ቅዱስ እስኪሆን ድረስ እናስነብባለን ደግሞም እናነባለን።

6. እግዚአብሔር ደራሲው ወይም ጸሐፊው የተባለለት ብቸኛው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። በጣም ብዙ ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል…" እየተባለ የእግዚአብሔር ንግግር የተቀዳበት መጽሐፍ ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ለዚህ ነው ጴጥሮስ *"ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና፥ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩ።"* 1ኛ ጴጥሮስ 2፡21 ያለው።

7. እግዚአብሔር ፈጣሪ እንደሆነ የተናገረ ብቸኛ እና የመጀመሪያው መጽሐፍ ነው። ዘፍጥረት 1፡1 *"በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ."* እግዚአብሔር የሚባል ቀይ ቀጭን ረዘም ያለ… ብሎ ምንም አያብራራም። እግዚአብሔር እንዳለ አምኖ የጀመረ ብቸኛ መጽሐፍ ነው። ስለዚህ ፈጠረ ይላል እንጂ ማነው ብትል

አይመልስልህም። ምክንያቱም መጽሐፍ ቅዱስ እንዳለ አምኖ ነው የጀመረው። የት ነው? እንዴት ነው? ብለን እንድንጀምር ሳይሆን ፈጠረ ሲባል ፈጠረ ብለን እንድንጀምር ነው የእግዚአብሔር ፈቃድ። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ብቸኛው የነገሮች ጅማሬ ቁልፍ እግዚአብሔር እንደሆነ የሚነግረን መጽሐፍ ነው።

8. ስለ ሰው መጀመሪያም መጨረሻም የሚናገረው ብቸኛው መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሰዎችን ጅማሬ ሳይንሱ ሰው ከዝንጀሮ እንደመጣ እና በሒደት እንደተለወጠ በሚያምንበት አስተምህሮው መጽሐፍ ቅዱስ ብቻ ነው ሰውን በመልኩ በአምሳሉ ፈጠረው ብሎ የነገረን። ሌሎቹ መጽሐፍቶች በሙሉ ከመጽሐፍ ቅዱስ ቅጂ ተወስዶ የተፃፉ ናቸው እንጂ ምንጩ የእግዚአብሔር ቃል ወይም መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የሰውን ጅማሬ ብቻ ሳይሆን ከሞት በኋላ ያለውን የሰውን ፍፃሜ የሚነግረን መጽሐፍ ነው። የአንዳንድ ቤተ እምነቶች መጽሐፎች "በሕይወት እያለህ መልካም ከሠራህ በሌላ ዓለም በሌላኛው ውልደትህ ምናልባት ንጉስ ልትሆን ትችላለህ ክፉ ከሆንክ ደግሞ ትንኝ ሆነህ ትመጣለህ" ብለው ያምናሉ።

መጽሐፍ ቅዱስ ግን አያወላዳም ከሞት በኋላ ለሰው ልጆች ፍርድ እንዳለ ያስቀምጣል። በሕይወት እስካለ ድረስ ብቻ ነው ሰው ሕይወቱን መምረጥ የሚችለው። ከሞት በኋላ ሕይወት እንዳለ የነገረን ብቸኛ መጽሐፍ መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ሌሎቹ ምንም ችግር እንደሌለው እና በዚህ እስካለህ ድረስ ጨፍር፣ ተደሰት፣ የፈለገህን አድርግ ከዛ ውጪ ግድ የለም ይሉናል።

9. ሌላው ቤተክርስቲያን ምን እንደሆነች የነገረን ብቸኛው መጽሐፍ ነው። ቤተክርስቲያን መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለ ሀሳብ እንጂ ቤተክርስቲያን የተቋም ጉዳይ አይደለችም። ስለሃይማኖት እያወራሁ አይደለም። የቤተክርስቲያን መወለድና የክርስቶስ አካል የሚለውን የሚያወራልን መጽሐፍ ቅዱሳችን ነው። ዓለም ላይ ያለ ሰው በሙሉ የቤተክርስቲያን የአካሏ ብልት እንደሆነ ጽንሰ ሀሳቡን ያወራልን መጽሐፍ ቅዱሳችን ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ በዓለም ላይ ቁጥር አንድ እድሜ ጠገብ ነው ብለናል። በጣም በሚገርም ሁኔታ ለረጅም ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ በተለይ በብሉይ ኪዳን ያሉት አምስቱ የሙሴ መጽሐፍት (ቶራህ) የሚባለው ከዚያም በኋላ ያሉት የነብያት መጽሐፍቶች እስራኤላውያን ሲበተኑ ወይንም ደግሞ ባለመታዘዝ ምክንያት ወደሌላ ምድር ሲሄዱ ካህናቶች ብቻ ናቸው መጽሐፉን እንዲያባዙ የሚሰጣቸው። ለምሳሌ የዘፍጥረት መጽሐፍ ከሆነ ቤታቸው ሲሰደዱ ወይም ተበትነው ሲሄዱ የሚሄዱበት ሀገር ላይ ምንም ማድረግ ስለማይችሉ አንድ ካህን ቁጭ ብሎ ፊደሏን ነቁጣ ሳትቀር እየለቀመ ሌላ ብራና ላይ ይጽፍና ለሌሎች ያስተላልፋል። ይህ ብቻ አይደለም አንዱ ብራና እያረጀ ሲመጣ እድሜው ከማለቁ በፊት በሌላ ይገለብጡ እና ያረጀው ይጣላል።

መጽሐፍ ቅዱስን ልዩ ካደረገው አንዱ በሙት ባህር ላይ የከርሰ ምድር ተመራማሪዎች ሲቆፍሩ ብዙ የብራና ቅጂዎች ተገኝተዋል። በእድሜ ዘመኑ እግዚአብሔር የጠበቀውና እስትንፋሱ ያለበት መጽሐፍ ቢኖር ይሔ መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ እያንዳንዱ የመጽሐፍ ጥቅል ጸሐፊዎቹ ሲጽፉት በቁጥርና በምዕራፍ ያልተከፋፈለ ነበር ነገር ግን ለእኛ በሚገባን መልኩ እግዚአብሔር በእጃችን ያስገባልን ድንቅ መጽሐፍ ነው። ዛሬ በስልካችን ሁሉ አለ የትም ቦታ ሆነን መጠቀም እንችላለን። ይህንን ቴክኖሎጂ እግዚአብሔር ለእርሱ ዓላማ እንድናውለው እጃችን ላይ ስላስገባ ስሙ ይባረክ! ስለዚህ ትኩረት ሰጥተን ልናነበው የሚገባ መጽሐፍ ነው ማለት ነው። እድሜ ዘመኑን ሁሉ በበላይነት ያሸነፈ መጽሐፍ ነው። ወደር የሌለው መጽሐፍ ነው። እድሜው በጣም ረጅም ነው ያልኩት ለዚህ ነው።

ሁለተኛው በሌሎች መጽሐፍት የተመሰከረለት መጽሐፍ ነው ብለናል። ከመሰከረለት አንዱ ቁርአን ራሱ ነው። ሱረቱል አል በቀራህ የሚባለው ክፍል ላይ ምዕራፍ 2 ቁጥር 136 ላይ እንዲህ ይላል፣ "በአላህና ወደ እኛ በተወረደው በቁርአን ወደ ኢብራሂም ወደ ኢሳማኤልም ወደ ኢሳቅም ወደ ያዕቆብም ወደ ነገዶቹም በተወረደው በዚያው ሙሳና ኢሳ በተሰጡት በዚያም ነቢያት ሁሉ ከጌታችን በተሰጡት ከእነርሱም በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን በሉ" ይላል።

አራት ሰዎችን ይጠቅሳል እዚህ ጋር አንደኛ ኢብራሂም - አብርሃም፣ ኢስማኤል - እስማኤል፣ ኢሳቅ - ይስሃቅ (የአብርሃም ልጅ) ፣ እንደገና ያዕቆብ - የይስሃቅ ልጅ የዘር ግንዱን እያወራ ነው። ከቁርአን እና ከመጽሐፍ ቅዱስ በእድሜ ትልቁ የትኛው

ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ነው። ስለዚህ ቁርአን ለመጽሐፍ ቅዱስ እየመሠከረለት እና የያዝነውን መጽሐፍ ቅዱስ እውነተኛነት እያረጋገጠልን ነው። ወደ ነገዶቹም - ወደ ያዕቆብ 12ቱ ነገዶች "በተወረደው በዚያም በሙሳ" - በሙሴ በኩል በወረደው እንደገናም ደግም "ኢሳ በተሰጡት" - ኢየሱስም በተሰጠው "በዚያ ነቢያት ሁሉ ከጌታችን በተሰጡት" - እነሱ ከጌታ መሆናቸውን እያረጋገጠ ነው። "ከእነርሱም በአንድም መካከል የማንለይ ስንሆን አመንን እኛም ለእርሱ ታዛዦች ነን በሉ" - የእምነቱን ተከታዮች "እኛም ከእነርሱ የማንለይ አብረን ያመንን ነን በሉ" እያላቸው ነው።

ሌላ ጥቅስ ደግሞ እንይ ሱረቱ አል ኒሳህ 4፥136 "እናንተ ያመናችሁ ሆይ በአላህ እና በመልእክተኛው በዚያም በመልዕክተኛው ላይ ባወረደው መጽሐፍ ከዚያም በፊቱ ባወረደው መጽሐፍ እመኑ። በአላህ እና በመላእክቱም በመፅሀፎቹም በመልእክተኞቹም በመጨረሻ ቀን የካደ ሰው ከሰውነት የራቀ መሳሳት በእርግጥ ተሳሳተ" ሲል መስክሮለታል።

እንደ እነ አሌክሳንደር ዘ ግሬት የሚባሉት ታላላቅ ጀብደኞችና ጦረኞች እንኳን ሳይቀሩ፣ "እኛ ስንት ሺህ ወታደር አስከትለን ያላሸነፍነውን ህዝብ አንድ ኢየሱስ የሚባል ሰው መስቀል ላይ ሞቶ ሁሉን ማረካቸው" ሲል ተደምጧል።

ሶስተኛው በዓለም ላይ ምርጥ ሽያጭ ወይም ከ11-14 ሚሊዮን ኮፒ በመሸጥ ወደር የሌለው መጽሐፍ ነው። በአንደኛ ደረጃ በጣም ተነባቢ ነው ብለናል። በዓለም ላይ እስካሁን ድረስ ሰዎች እያጠኑት ያሉ አማኞች ብቻ ሳይሆኑ ያላመኑ ሰዎች እግዚአብሔር የለም የሚሉ እንኳን ሳይቀሩ የሚያነቡት መጽሐፍ ነው። ደራሲዎች ሳይቀሩ እየተመራመሩ ለድርሰታቸው እንኳን ሀሳብ የሚወስዱበት መጽሐፍ ቢኖር መጽሐፍ ቅዱስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስ ወደ 2700 በሚሆኑ ቋንቋ ተተርጉሞ ጥቅም ላይ በመዋል ተነባቢነቱ ወደር የለውም። ይህንን በሚያህል ቋንቋ የተተረጎመ መጽሐፍ እስካሁን የለም። ይህን የመሰለ መጽሐፍ ይዘን ልንተኛበት አይገባም። ምክንያቱም 2700 ቋንቋ ማለት በእያንዳንዱ ቋንቋ ውስጥ ብዙ ህዝብ አለ። የወንጌል እውነት ምን ያክል ሰፊ እንደሆነ የሚያሳይ ነው።

ሌላው በጣም ደስ ከሚለን እና ልዩ ከሚያደርገው አንዱ የዓለማችን ኃይለኛ እና ታላቅ መጽሐፍ ነው። ክሊንተን፣ ኦባማ፣ ትራምፕ ወደ ስልጣን ሲመጡ የመጨረሻ የሚምሉበት ከእነርሱ በላይ ታላቅና ኃይለኛ እንደሆነ ያመኑት መጽሐፍ ቢኖር

መጽሐፍ ቅዱስ ነው። የህክምና ባለሙያዎች ተምረው ሲጨርሱ የሰውን ሕይወት እንደሚያድኑ ቃል የሚገቡበት፣ ፍርድ ቤት ለምስክርነት ሰዎች የሚምሉበት መጽሐፍ ነው።

በእድሜ ዘመኑ ሁሉ ሰዎች እንዳያነቡት ትልቅ ተግዳሮት ያለበት መጽሐፍ ነው። በኋላ ታነባለህ ችግር የለውም፣ ሌሊት ተነስተህ ታነባለህ ችግር የለውም እያለ ብርድ ልብስ የሚያከናንበን እዚህች ጋር ስንደርስ ነው። ለማንኛውም ከዚህ ኮርስ በኋላ ግን እንደርሱ አይሆንም።

በ1900ዓ.ም ታላቅ የማቃጠል ስራ ተሰርቶበት ነበር።

ጸሐፊው እግዚአብሔር እንደሆነ የተናገረለት ብቸኛ መጽሐፍ ነው። *"በመጀመሪያ እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ"* ፈጠረ ብሎ ነው የሚጀምረው አሜን ብሎ ነው ሚቀጥለው። ማነው? ምንድነው? እንዴት ነው? እግዚአብሔር አይብራራም ይበራል እንጂ። *"እግዚአብሔር ብርሃን ነው ለእኛም በራልን"* ነው እንጂ *"ተብራራልን"* አይልም። ፊዚክስና ኬሚስትሪ ነው የሚብራራው እንጂ እግዚአብሔር መብራት ነው *ሥራው*። ምናውቀው ወይም ምንረዳው ሳይሆን የሚበራ ነው። እግዚአብሔር ይመስገን! ስለዚህ እኛ በርቶልን ነው የመጣነው። በጨለማችን ላይ ብርሃን ይብራ ያለ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር ራሱ ማንነቱ ብርሃን ነው። በራልን ማለት ተብራራልን ማለት ሳይሆን በጨለማችን ላይ ብርሃን በርቷል ማለት ነው። የወንጌሉን ብርሃን በእኛ ላይ አብርቶታል። አሁን የጨለማ አገር ሰዎች ሳንሆን ከድቅድቅ ጨለማ ወደ ሚደነቀው ብርሃን የፈለስን ህዝቦች ነን።

2ኛ ጢሞ 3፡16-17 ላይ ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ሌላው የሚናገረው

> *"የእግዚአብሔር ሰው ፍፁምና ለበጎ ስራ ሁሉ የተዘጋጀ ይሆን ዘንድ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት መጽሐፍ ሁሉ ለትምህርት፣ ለተግሳፅ ልብንም ለማቅናት በጽድቅም ላለው ምክር ሁሉ ይጠቅማል"*

ይሔ ነው አንደኛው መጽሐፍ ቅዱስ የእግዚአብሔር መንፈስ ያለበት የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለበት ለምክር፣ ለተግሳፅ፣ ሙሉ ሰው ለማድረግ፣ ለእግዚአብሔር ሥራ ብቁ ለማድረግ የሚጠቅም ነውና ስለዚህ ሊነበብ ይገባል።

> *2ኛ ጴጥሮስ 1፡21 "ትንቢት ከቶ በሰው ፈቃድ አልመጣምና ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ተልከው ቅዱሳን ሰዎች በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው ተናገሩለት"*

መጽሐፍ ቅዱስ የሚባለው መጽሐፍ ጸሐፊው ሰው ነው ነገር ግን ተናጋሪው በእነርሱ ውስጥ ሆኖ መንፈስ ቅዱስ ነው። ትንቢት በሰው ፍቃድ ካልመጣ … በመንፈስ ቅዱስ ተነድተው… ካለ የመጽሐፉ ደራሲ መንፈስ ቅዱስ ነው ማለት ነው። በጣም የሚገርመው መንፈስ ቅዱስ፣ የመጀመሪያው ሰው ማለትም ዘፍጥረትን የፃፈው ሙሴ እና የመጨረሻውን መጽሐፍ ራዕይን የፃፈው ዮሐንስ እርስ በእርሳቸው አልተጋጩም። ምክንያቱም የሁለቱንም እጅ የተጠቀመው ደራሲው ሌላ ስለሆነ ነው። በነዚህ ሁሉ ዓመታቶች ውስጥ በማይተዋወቁ ሰዎች መካከል እንኳን ግጭት የሚባል ነገር አልተፈጠረም።

## *የመጽሐፍ ቅዱስ መዋቅር*

እንግዲህ መጽሐፍ ቅዱስ ስናይ ለመፃፍ ከክርስቶስ ልደት በፊት ወደ 1500 ዓመት ፈጅቷል። ከመስቀል በኋላ ደግሞ የአዲስ ኪዳን መልዕክት 100 ዓመት ፈጅቷል። የመጨረሻው መጽሐፍ የራዕይ መጽሐፍ ነው፤ ከ100 ዓ.ም በፊት ተጽፏል ተብሎ ነው የሚገመተው። በ1500 እና ከ100 ዓመት ጋር ሲደመር 1600 ዓመት ይሆናል። ስለዚህ መጽሐፍ ቅዱስ ለመፃፍ 1600 ዓመት ፈጅቷል ማለት ነው። ብሉይ ኪዳን 39 እና አዲስ ኪዳን 27 መጽሐፍትን በአጠቃላይ መጽሐፍ ቅዱሳችን 66 መጽሐፍትን ይዟል። ጸሐፊዎቹ 40 እና ከዛ በላይ የሚሆኑ ሰዎች ናቸው። በአርባዎቹም የተጠቀመው ደራሲው ግን መንፈስ ቅዱስ ነው። በጸሐፊዎቹ ውስጥ ነገስታቶች አሉ፣ ባለስልጣናት አሉ፣ አሳ አጥማጇዎች አሉ፣ ሐኪሞች አሉ፣ ነጋዴዎችም ደግሞ አሉ። እነዚህን ሁሉ ስማቸውን ማውጣት እንችላለን። ነገር ግን ተናጋሪው እግዚአብሔር ነው። *"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል…"* የሚል 397 ጊዜ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ አለ። ማንኛውም መጽሐፍ ይሄን ያህል ጊዜ *"እግዚአብሔር እንዲህ ይላል"* ብሎ የጠቀሰ አታገኙም። መልዕክቱ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው የሰውን ታሪክ ይዟል።

## *መጽሐፍ ቅዱስ ስለ ማን ይናገራል?*

በጣም ብዙ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን የሚያነቡት ስህተታቸውን ለማግኘት ነው። የማያነበው ደግሞ *"እግዚአብሔር የሚለኝን ባላደርግስ አለማወቅ ይሻላል"* በሚል ከፍርድ እና ከቅጣት ለማምለጥ በሚል ነው። ይሄ አስተሳሰብ መንፈሳዊ እውነት ያለው ሳይሆን በብልሃት የተፈጠረ ተረት ነው። በእግዚአብሔር ቃል የምንፈልገው ወይም የምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ችግራችንን ለማወቅ አይደለም። መጽሐፍ

ቅዱስን ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ በቃላችን ለመሸምደድም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን የምናነበው ድክመታችንን ለማወቅም አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስን የምናነብበት ብቸኛው ምክንያት ኢየሱስን ለማግኘት ብቻ ነው። በጣም ብዙ ሰው መጽሐፍ ቅዱስን ላነብ ስል ዱካክ ያዘኝ የሚለው፤ የማንበብ ፍላጎቱ ኖሮት ማንበብ የማይችለው ተጽዕኖ ያደረበት፤ መጀመሪያም መጽሐፉ ያስፈራራው፤ እሱ ካለበት ሕይወት ጋር የሚስማማ ነገር ስለማያገኝ ነው።

አንዲት ዘፋኝ የተናገረችው ትዝ ይለኛል "ድሮ ልክ መጽሐፍ ቅዱሱን ስከፍተው *"እበትንሻለሁ፣ እቀስፍሻለሁ"* የሚል ሳነብ ከድን አደርገዋለሁ" አለች። አንዳንድ መንፈሳዊ ልምምድ ያላቸው የሚመስሉ ደግሞ አሉ። *"ጌታ ሆይ ተናገረኝ"* ብለው መጽሐፍ ቅዱስ ግምስ አድርገው የሚከፍቱ። የመጀመሪያ አይናቸው ያረፈበት ጥቅስ መልዕክታቸው እንደሆ ያስባሉ። ልክ ጸልየው ክፍት ሲያደርጉት "በምድሪቱ ላይ እበትንሻለሁ" የሚል ከሆነ *"በኢየሱስ ስም!"* ብለው መልሰው ይከድኑታል። በመንፈሳዊ ሕይወቴ ልጅ ሆኜ እንደዚህ አድርጌ አውቃለሁ። በጣም ብዙ ሰው አሁንም እያደረገው ነው። ችግር የለውም ስትበስሉ ትተዉታላችሁ።

በድጋሜ ይጸልያሉ *"ጌታ ሆይ የኔን ጥቅስ፣ የኔን መልዕክት ስጠኝ"* ብለው መልሰው ክፍት ሲያደርጉት *"በፊትህ የተከፈተ በር ሰጥቼሃለሁ"* የሚል ካገኙ *"አሜን! ይሔ የኔ መልዕክት ነው!"* ከዚህ በኋላ በአንተ ሕይወት ግን እንዲህ አይነት ነገሮች ይቆማሉ። ምክንያቱም ከዚህ መጽሐፍ ማንበብ በኋላ መጽሐፍ ቅዱሳችንን ለምን እንደምናነብ ስለምናውቀው፣ እግዚአብሔር በቃሉ ውስጥ እንዴት እንደሚናገር ስለምንረዳ በሕይወታችን ትልቅ ፈውስ እናገኛለን።

መጽሐፍ ቅዱስ በዮሐንስ 5፡39 - 40 ላይ ጌታ ኢየሱስ ራሱ እንዲህ አለ *"እናንተ በመጻሕፍት የዘላለም ሕይወት እንዳላችሁ ይመስላችኋልና እነርሱን ትመረምራላችሁ፤ እነርሱም ስለ እኔ የሚመሰክሩ ናቸው፤ ነገር ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም።"* ብዙ ሰው ጥቅሱን እንጂ በጥቅሱ ውስጥ የተነገረለትን ሰውዬ አያገኘውም። 39ኙ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍቶች በሙሉ የሚናረገሩት ስለ ኢየሱስን ነው።

ብሉይ ኪዳንን ከፍተህ ስታነብ ኢየሱስን ካላገኘህበት ዝጋው። ኢየሱስ ምን እያላቸው እንደ ሆነ አስብ፣ ፈሪሳውያን፣ የሕግ ጸሐፊያን፣ መምህራን ናቸው መጽሐፍትን በማወቅ የተመሰከረላቸው ናቸው። በመጽሐፍት ሕይወት ያለ መስሏችሁ ትመረምራላችሁ፤ ከከሙንና ከጥቁር አዝሙድ እንኳ ሳይቀር አስራት

በማስከፈል የተመሰከረላቸው ናቸው። ነገር ግን በሕግ ያለውን ዋናውን ነገር ረስተዋል።

መጽሐፍት ሕይወት አይሰጧችሁም፤ መጽሐፍት ሁሉ ግን ሕይወት መስጠት ስለምችለው ስለ እኔ ይናገራሉ እያላቸው ነው። ስለዚህ መጽሐፍቶች የሚናገሩት ስለ ኢየሱስ ከሆነ እኛ ከየትኛውም ክፍል አውጥተን ኢየሱስን እንጂ የምናወራበት የራሳችንን ሀሳብ አይደለም። አሁን መጽሐፍ ቅዱስን ማንበቡ ችግር የሆነብን ኢየሱስን ለማግኘት ወይ የሆነ ነገር ለሰው ለማካፈል ወይ ደግሞ ለስብከት ስለምናነብ ነው። የምናነብበት መነሻ ሀሳባችን እየሱስ እንደተናገረን መስተካከል አለበት።

ለምሳሌ፡- ከመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ብንመለከት የዳዊት እና የጎልያድን ታሪክ እናገኛለን። በወቅቱ እስራኤል ምድር ላይ ዳዊት የሚባል አንድ ፍሬ ልጅ በጠጠር "በተገዳደርከው በሰራዊት ጌታ እግዚአብሔር ሥም" ጎልያድን ግንባሩን ብሎት እንደጣለው እናነባለን ያም ያለፈና በታሪክ ደረጃ አንድ ወቅት ላይ የተከሰተ ታሪክ ነው። ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ ያለፈ ታሪክ ነው ብሎ አልተወውም፤ ጽፎ አስቀመጠው። ምክንያቱም በዳዊት ውስጥ ያየው ኢየሱስን ስለሆነ ነው። አሁን በዚህ ዘመን ላይ *"ጎሊያድ እንደወደቀ ዛሬ በፊትህ ያለው ጎሊያድ..."* ብትባል ለውጥ የለውም ምክንያቱም ጎልያድ በአንተ ዘመን ላይ የለም፤ አንተም ዳዊት አይደለህም። ነገር ግን በዳዊት የሠራውና ድል ያደረገው እግዚአብሔር ዛሬ በአንተ ሕይወት ምን ዓይነት ሥራ መሥራት እንደሚችል ማየት ትችላለህ። ዳዊት ጎልያድን እንደዘረረው ኢየሱስ ዲያቢሎስን ዘርሮልሃል በማለት ከክርስቶስ ሥራ ጋር ስታገናኘው ጥላው ላይ ያገኘነው ታሪክ በክርስቶስ አካል ይለብሳል። መልዕክቱም የአዲስ ኪዳን መልዕክት ይሆናል። ለምን? በዳዊት ውስጥ ያገኘኸው ኢየሱስን ስለሆነ። ከኢየሱስ አንበልጥም ስለዚህ መጽሐፍት ሁሉ ስለ ኢየሱስ ነው የሚናገሩት። መጽሐፍ ቅዱስን የምናነበው የምናጠናው ስብከታችን ትምህርታችን ሕይወታችንም የምንበላውም የምንተነፍሰው ኢየሱስ ብቻ ነው። የዚህ መጽሐፍ አንዱ ራዕይ ፡- ኢየሱስ + ምንም = ሁሉንም! ማለትም ኢየሱስ ሲደመር ምንም እኩል ይሆናል ሁሉንም ነው።

በዚህ ዘመን የተቸገርነው ሰዎች በኢየሱስ የመስቀል ሥራ ላይ እየደመሩ ነው። እኛ ኢየሱስ ላይ አንደምርም ኢየሱስ ለእኛ በቂያችን ነው ኢየሱስ ካለ ሁሉ ነገር አለ። የሰው ልጅ ችግር ኃጢአት አይደለም! የሰው ልጅ ችግር ዲያቢሎስ አይደለም! የሰው ልጅ ችግር ኢየሱስ ነው! ምክንያቱም ኢየሱስን ያለማወቅ ችግር እንጂ ያለብን የኃጢአት እና የዲያቢሎስ ጉዳይ በኢየሱስ ተፈትቷል። የችግሮቻችን ሁሉ መልስ

የሆነውን ኢየሱስ አለማወቅ ነው። ኢየሱስ *"መጽሐፍትን ትመረምራላችሁ እነርሱ ግን ስለ እኔ ይናገራሉ...ግን ሕይወት እንዲሆንላችሁ ወደ እኔ ልትመጡ አትወዱም"* ነው ያላቸው። አነርሱ መጽሐፉን በትክክል አውቀውት ቢሆን እየመረመሩት ሲመጡ እርሱን ኢየሱስን ያገኙት ነበር።

"ፊሊጶስ ናትናኤልን አግኝቶት *"ሙሴ በሕግ የተናገረለትን ነብያትም ስለ እርሱ የፃፉለትን የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተናል"* አለው። ቀድሞ ሙሴ በሕግ የተናገረለት እንደገና ነቢያት የጻፉለትን አገኘሁት ነው ያለው። እኛ አንረዳው እንጂ እነ ሙሴ ተናግረውለት ሳያገኙት ነው የሄዱት ። እኛ አንረዳው እንጂ ነብያት ጽፈውለት ነው የሄዱት ነገር ግን አላገኙትም። "ፊሊጶስ እኔ ግን አገኘሁት" አለ። ይሔ ሰው ተራ ምናምንቴ የሚባል አይነት ሰው ነው። መጽሐፍቱን ቃሉን የሚያውቁት ሰዎች አላገኙትም ምክንያቱም ወደ እሱ ሊመጡ አልወደዱም። በሰው ዘንድ ተቀባይነት የሌለው ሰው ግን "አገኘሁት" አለ። ፊልጶስ እንዳለ ይህንን መጽሐፍ ካነበብክ በኋላ እኔ እጸልያለሁ እየሱስን ማግኘት ይሁንልህ! 1፡46 1ጴጥ 1፡11

## *መጽሐፍ ቅዱስ የተናገረለት ህያው ቃል*

ኢየሱስ ህያው ቃል እንደሆነ አስተውሉ። ኢየሱስ ህያው ቃል ነው "በመጀመሪያው ቃል ነበረ፣ ቃልም በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ ቃልም እግዚአብሔር ነበረ...ቃልም ሥጋ ሆነ ጸጋንና እውነትን ተሞልቶ በእኛ አደረ አንድ ልጁም ከአባቱ ዘንድ እንዳለው የሆነውን ክብር አየን" በመጀመሪያው ብሎ ሲል "በመጀመሪያው እግዚአብሔር ሰማይንና ምድርን ፈጠረ" አይደል የሚለው፤ በመጀመሪያው ከሚለው መጀመሪያም ቃል ነበረ - ከዛም ሁሉ በፊት። ቃል ደግሞ የት ነበረ? "በእግዚአብሔር ዘንድ ነበረ." ቃል ራሱ ደግሞ "እግዚአብሔር ነበረ."። ያ ቃል ሥጋ ሆኗል ሥጋ ስለሆነ ደግሞ ወዲያውኑ በእኛ ሕይወት ላይ መሥራት ጀምሯል። ህያው የሆነው ቃል ኢየሱስ ነው። እዚህ ክፍል ላይ በመጀመሪያ ቃል ነበረ እያለ የሚናገረው ስለ ኢየሱስ ነው።

"የእግዚአብሔር ቃል ህያው ነውና፣ የሚሰራም ሁለትም አፍ ካለው ሰይፍ ይልቅ የተሳለ ነው ነፍስንና መንፈስን፤ ጅማትና ቅልጥምን እስኪለይ ድረስ ይወጋል። የልብንም ስሜትና ሀሳብ ይመረምራል። እኛን በሚቆጣጠር በእርሱ አይኖች ፊት ሁሉ ነገር የተራቆተና የተገለጠ ነው እንጂ በእርሱ ፊት የተሰወረ ፍጥረት የለም።" ዕብ 4፡12-13 ይህ ክፍል ህያው ቃል እያለ የሚናገረው ኢየሱስን ነው። በእርሱ ዓይኖች ፊት እኛ ሁላችን ራቁታችንን ነን!

*"ሰነፍ በልቡ አምላክ የለም ይላል"* መዝ 13፡1፤53፡1 በሚለው ቃል ፊት አንተ ራቁትህን አይደለህም። *"ሰንዴ ታብቅል አለ ሰንዴም በቀለ"* በሚለው ቃል ፊት አንተ ራቆትህን አይደለህም። ህያው ቃል ከነገሮች ሁሉ በፊት ከእርሱ ጋር የነበረ፣ ራሱ እግዚአብሔር የሆነ ህያው ቃል አለ - ስሙም ኢየሱስ ነው። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ፈልገን የምናገኘው፣ የምንኖርለት ለእኛ ለሕይወታችን የተነገረ ቃል ህያው የምንለው ኢየሱስ ነው።

ስለዚህ ኢየሱስ ህያው ቃል ነው። ህያው ቃል! *"በህያው ቃል ከማይጠፋ ዘር ተወልዳችኋል።"* አንደኛ *"በህያው ቃል"* ነው የሚለው። ሁለተኛ *"የማይጠፋ ዘር"* ነው ቃሉ። ይሄ ቃል መውለድ፣ መፍጠር፣ ማዳን ይችላል። ይህንን እያወራ ያለው ስለ ዳግም ውልደት ነው። ኢየሱስ ስለ ልጅነት ሲናገር *"ከእግዚአብሔር ተወለዱ እንጂ ከደም ወይም ከሥጋ ፍቃድ አልተወለዱም"* አለ። በጣም የሚገርመው *"ሳሩም ይጠወልጋል፣ አበባውም ይረግፋል...የእግዚአብሔር ቃል ግን ለዘላለም ህያው ሆኖ ይኖራል"* ይህን ያለው ጴጥሮስ ነው። ጴጥሮስ *"ሳሩም ይጠወልጋል፣ አበባውም ይረግፋል"* ሲል እየተናገረ ያለው ስለ ሰው *ሥጋ* ነው። 1ጴጥ 1፡23-24 እና ዮሐ 1፤13 ተልከቱ።

ነገር ግን ከማይጠፋ ዘር የተወለደ እዚህ ሥጋ ውስጥ የሚኖር ሌላ ሰውዬ አለ፤ እሱ ከማይጠፋ ዘር ነው የተወለደው። *"ሰማይና ምድር ያልፋሉ ቃሌ ግን አያልፍም"* ሲል ይሄ መጽሐፍ ቅዱስ አብሮ ይጠቀለላል። ምክንያቱም ይህ መጽሐፍ ከእንጨት ውጤት ነው የተሠራው። ስለዚህ ቃሌ ግን አያልፍም ሲል መጽሐፍ ቅዱስ ስለታተመበት ወረቀት እያወራ አይደለም። ህያው ስለሆነው ኢየሱስ ስለሆነው ቃል ነው። አንተን የወለደህ ለዘላለም ህያው የሆነ ቃል አለ እሱ ግን አያልፍም። ከዘፍጥረት እስከ ራዕይ የተተረከለት የተነገረለት የማይጠፋ ዘር የሆነው ኢየሱስ ነው።

መጽሐፍ ቅዱስን ስታነቡ የሰው ቃል አለ፣ የእባቡ ቃል አለ፣ እንደመሰላቸው የሚል ቃል አለ፣ አህያም ተናግሯል፣ የመላእክት ድምፅ አለ፤ በጣም ብዙ አይነት ድምፅ ነው ያለው። በዛ መካከል ለምሳሌ እንደመሰላቸውም ብሎ ሉቃስ ጽፎልናል። ስለዚህ ሰዎቹ እንደመሰላቸው የተወራ እንጂ የሚያወራው እርሱ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም። እባቡም እንዲህ አለ የሚለው ቃል የእግዚአብሔር ቃል አይደለም፤ እባቡ ነው ያለው። እባቡ ሲናገር ግን እኛ አልነበርንም አልሰማንም። የሰማው መንፈስ ቅዱስ ነገረን። *"ሰነፍ እንዲህ አለ..."* ሰነፍ ነው ያለው። *"እግዚአብሔርን ሰድበህ ሙት"* ያለችው የኢዮብ ሚስት ናት እግዚአብሔር አላለም። *"እግዚአብሔር*

*ይገድላል፤ እግዚአብሔር ያድናል .... አትታበዩ በኩራትም አትናገሩ"* ሀና አለች አለ እንጂ እግዚአብሔር አለ አይልም። *"ብዙ የወለደች መከነች"* ስለዚህ ሀና ካለችበት ሁኔታ አንጻር ነው እንጂ ይህንን የተናገረችው እግዚአብሔር አይገድልም። የሚገድል ቢሆን ኖሮ መጥቶ አይሞትልንም ነበር።

ኢየሱስ ክርስቶስ የእግዚአብሔር ትክክለኛ የባህሪው ነጸብራቅ ነው። በጣም ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ የምንፈታው ሙሴ ላይ ቆመን ነው። በጣም ብዙ ጊዜ እግዚአብሔር ማን እንደሆነ የምንፈታው ኢዮብ ላይ ቆመን ነው። መጽሐፍ ቅዱስ አንዳቸውም ላይ ቆመን እንድንፈታ አይነግረንም። *"መቼም ቢሆን እግዚአብሔርን ያየው አንድስ እንኳ የለም በእቅፉ ያለው አንድያ ልጁ ተረከው" ዮሐ 1፡18 ሏይደለ* የሚለው? ስለዚህ እግዚአብሔር ይገድላል ማለት ያለብህ ኢየሱስ ሲገድል አይተህ ነው።

ኢየሱስ ላይ ተቆሞ እንጂ እግዚአብሔር የሚፈታው (የሚተረጎመው) ሌሎች ነብያቶች እና አገልጋዮች ላይ ቆመህ እንዳትፈታ። የዘመኑም አገልጋይ ላይ ቆመህ እንዳትፈታ፣ የበፊቶቹም አገልጋዮች ላይ ቆመህ እንዳትፈታ። ሰው ላይ ተቁሞ እግዚአብሔር አይፈታም። የባህሪው ትክክለኛ ነጸብራቅ ኢየሱስ ነው። ኢየሱስን አይተህ ይገድላል ማለት ትችላለህ። ሙሴ ሲናገር በድንጋይ ውገሯት ነው ያለው፤ ኢየሱስ የባህሪው ትክክለኛ ነጸብራቅ ግን አልፈርድብሽም ነው ያለው። ሙሴ ላይ ቆመህ ከፈታኸው ድንጋይ ይዘህ ነው የምትመጣው። ኢየሱስ ላይ ከቆምክ ግን *"እኔ አልፈርድብሽም"* እንደውም *"አንቺ ሴት ከሳሾችሽ ወዴት አሉ" "አንድስ እንኳ"* አለች እሷም። ዮሐ 8፡1-11 ተመልከት።

አሁን ኢየሱስን ሊመረምሩት ነው በሙሴ ሕግ የተነገረው እጅ ከፍንጅ የተያዘ ነው በድንጋይ ተወግሮ መሞት ያለበት። ምክንያቱም በሕጋቸው የተላለፈ ስለሆነ። ይዘዋት የመጡት ግን ሴትየዋን ነው ሰውየውን አላመጡትም። እጅ ከፍንጅ ከሆነ ማምጣት የነበረባቸው ሁለቱንም ነው። ይዘው የመጡት ነገር ቢኖር ሴቲቱን ብቻ ነው። ኢየሱስን *"ተናገር ሙሴ ተወግራ ትሙት ብሏል አንተ ምን ትላለህ?"* አሉት። ክፍሉን ስታነቡት አጎንብሶ መሬት ላይ ፃፈ ነው የሚለው አልተናገረም ነበር። ሕግን የሰጠ ነው ሕግን የሚተረጉመው፤ በድንጋይ ተወግራ ትሙት የሚለውን ነው እንጂ የያዙት፤ ድንጋይ ወጋሪው ማን መሆን እንዳለበት አላወቁም። ስለዚህ በትክክል ሲፈታ ድንጋይ መውገር ትችላለህ ነገር ግን ሕጉ ሲፈታ ወጋሪውንም ያካትታል። ተወጋሪውን ብቻ አይደለም። *"ከእናንተ መካከል የሷ ሏይነት ኃጢአት የሌለበት ይውገራት"* አላቸው። ወዲያው ሁሉም ውሽሞቻቸውን አስታወሱ፤ ሁሉም ድንጋዩን

ቁጭ እያደረጉ ሹልክ ብለው ወጡ። ስለዚህ *"አንቺ ሴት ከሳሾችሽ ወዴት አሉ" "አንድስ ስንኳ" "እንግዲህ እኔም አልፈርድብሽም።"*

አየህ፣ ሙሴ ላይ ከቆምክ እግዚአብሔርን ለመፍታት መሞከር አስቸጋሪ ነገር ውስጥ ይጥልሃል። *"በእኔ በቀር"* ነው ያለው። አብን ያለ ኢየሱስ ማወቅ የማይታሰብ ነው። ስለዚህ መጽሐፍት ሁሉ አላማቸው ስለ ኢየሱስ መናገር ነበር እንጂ ሌላ አይደለም። የእግዚአብሔር ቃል ሕያው ነው ደግሞም የሚሠራ ነው። የማይጠፋ፣ የማይሞት እኛንም ዳግም የወለደ አዲስ ፍጥረት ያደረገን ቃሉ ኢየሱስ ነው።

## *ሉቃስ 24*

ቁ.1 "ነገር ግን ከሳምንቱ በመጀመሪያው ቀን ያዘጋጁትን ሽቱ ይዘው ከእነርሱም ጋር አንዳንዶቹ ወደ መቃብሩ እጅግ ማልደው መጡ።" ኢየሱስ በተቀበረ በ3ኛው ቀን ማለት ነው።

> *"ድንጋዩንም ከመቃብሩ ተንከባሎ አገኙት፣ ገብተውም የጌታን የኢየሱስን ሥጋ አላገኙም። እነርሱም በዚህ ሲያመነቱ፣ እነሆ፣ ሁለት ሰዎች የሚያንጸባርቅ ልብስ ለብሰው ወደ እነርሱ ቀረቡ፤ ፈርተውም ፊታቸውን ወደ ምድር አቀርቅረው ሳሉ፣ እንዲህ አሉአቸው። ሕያውን ከሙታን መካከል ስለ ምን ትፈልጋላችሁ? ተነሥቶአል እንጂ በዚህ የለም። የሰው ልጅ በኃጢአተኞች እጅ አልፎ ሊሰጥና ሊሰቀል በሦስተኛውም ቀን ሊነሣ ግድ ነው እያለ ገና በገሊላ ሳለ ለእናንተ እንደ ተናገረ አስቡ። ቃሎቹንም አሰቡ፣ ከመቃብሩም ተመልሰው ይህን ሁሉ ለአሥራ አንዱና ለሌሎች ሁሉ ነገሩአቸው። ይህንም ለሐዋርያት የነገሩአቸው መግደላዊት ማርያምና ዮሐና የያዕቆብም እናት ማርያም ከእነርሱም ጋር የነበሩት ሌሎች ሴቶች ነበሩ። ይህም ቃል ቅዠት መስሎ ታያቸውና አላመኑአቸውም። ጴጥሮስ ግን ተነሥቶ ወደ መቃብር ሮጠ፤ በዚያም ዝቅ ብሎ ሲመለከት የተልባ እግር ልብስን ብቻ አየ፤ በሆነውም ነገር እየተደነቀ ወደ ቤቱ ሄደ። እነሆም፣ ከእነርሱ ሁለቱ በዚያ ቀን ከኢየሩሳሌም ስድሳ ምዕራፍ ያህል ወደሚርቅ ኤማሁስ ወደሚባል መንደር ይሄዱ ነበር፤ ስለዚህም ስለ ሆነው ነገር ሁሉ እርስ በርሳቸው ይነጋገሩ ነበር። ሲነጋገሩና ሲመራመሩም፥ ኢየሱስ ራሱ ቀርቦ ከእነርሱ ጋር ይሄድ ነበር፤ ነገር ግን እንዳያውቁት ዓይናቸው ተይዞ ነበር።*
>
> *እርሱም። እየጠወለጋችሁ ስትሄዱ፣ እርስ በርሳችሁ የምትነጋገሩአቸው እነዚህ ነገሮች ምንድር ናቸው? አላቸው። ቀለዮጳ የሚባልም አንዱ መልሶ። አንተ በኢየሩሳሌም እንግዳ ሆነህ ለብቻህ ትኖራለህን? በእነዚህ ቀኖች በዚያ የሆነውን ነገር አታውቅምን? አለው። እርሱም። ይህ ምንድር ነው? አላቸው። እነርሱም*

*እንዲህ አሉት። በእግዚአብሔርና በሕዝቡ ሁሉ ፊት በሥራና በቃል ብርቱ ነቢይ ስለ ነበረው ስለ ናዝሬቱ ስለ ኢየሱስ፤ እርሱንም የካህናት አለቆችና መኳንንቶቻችን ለሞት ፍርድ እንዴት አሳልፈው እንደ ሰጡትና እንደ ሰቀሉት ነው። እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤ ደግሞም ከዚህ ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።" ቁ. 2-21*

የኢየሱስ ሞቷል የሚለው ዜና ሰውን ሁሉ ያጠወልጋል። ሰውን የሚያለመልመው ተነስቷል የሚለው ብቻ ነው። እነዚህ ሰዎች ደግሞ ተነስቷል ላይ አልደረሱም። ምክንያቱም የልቦናቸው አይኖች አልበሩም ነበርና። በመሲህና በነብይ መካከል ልዩነት አለ። አነርሱ እንደ ነብይ እንጂ እንደ መሲህ አላወቁትም ነበር። አይኖቹ የተያዘበት ሰው ኢየሱስን አይለይም። በስም ግን ተከታይ ሊሆን ይችላል። እነዚህም ሰዎች ደቀመዝሙር ናቸው። አብረውት ነበሩ ስብከቱንም ሰምተዋል። እሞታለሁ ሲል አሜን! ያሉም ይመስለኛል። ወቅቱ ሲመጣ ግን ሁሉም ነገር ጠፍቶባቸዋል። እንዴት እንደጠፋባቸው ቀጥሎ ባለው ክፍል እናነባለን። ከሮማ አገዛዝ እስራኤልን የሚቤዥ አድርገው ነበር ያሰቡት።

*"ደግሞም ከእኛ ውስጥ ማልደው ከመቃብሩ ዘንድ የነበሩት አንዳንድ ሴቶች አስገረሙን፤" ቁ. 22*

አንድ የእግዚአብሔር ሰው በጣም ረጅም ጊዜ ይጸልይ ነበርና፤ የሚጸልየው ሽባ ለመተርተር እና ሙታን ለማስነሳት ነበር። እናም ይህ ሰው በጣም አጥብቆ ፆም ጸሎት ይዞ ይጸልያል። ታዲያ አንድ ቀን ተሳካለት አንድ ሽባ የነበረ ሰው ጸልዮለት ተነሳ። ወዲያውኑ ሲነሳ ከተፈወሰው ሰውዬ ይልቅ የፈወስው ሰውዬ በደስታ ብዛት ጮኸ፣ ወንበር ሰባበረ። መንፈስ ቅዱስ መጣና *"ምንም ሆነህ ነው አለው"* ሰውየውም *"ሰውየው ተፈወሰ እኮ!"* አለ። መንፈስ ቅዱስም "ለምን እንደዚህ ጮቤ እንደረገጥክ ታውቃለህ? ይህንን ማደረግ እንደምችል ስለማታምነኝ ነው" አለው።

እነዚህስ ሰዎች ለምን እንደተገረሙ ታውቃለህ? በልባቸው ውስጥ ይነሳል የሚለው እምነት ስለሌለ ነው። እነዚህ ሰዎች ከሴቶቹ በተጨማሪ የኢየሱስን መነሳት ከጴጥሮስ ሰምተዋል።ያንንም ሰምተው ነው እንግዲህ ጉዞ የጀመሩት።

*"ሥጋውንም ባጡ ጊዜ። ሕያው ነው የሚሉ የመላእክትን ራእይ ደግሞ አየን ሲሉ መጥተው ነበር። ከእኛም ጋር ከነበሩት ወደ መቃብር ሄደው ሴቶች እንደ ተናገሩት ሆኖ አገኙት፣ እርሱን ግን አላዩትም። እርሱም። እናንተ የማታስተውሉ፣ ነቢያትም የተናገሩትን ሁሉ ልባችሁ ከማመን የዘገየ፤ ክርስቶስ ይህን መከራ ይቀበል ዘንድና*

*ወደ ክብሩ ይገባ ዘንድ ይገባው የለምን? አላቸው። ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው።" ቁ. 23 - 27*

በዚህ ኮርስ የምታገኙት ይህንን የትርጉም መንፈስ ነው። ጌታ ኢየሱስ ሲያገኛቸው *"ከሙሴና ከነቢያት ሁሉ ጀምሮ ስለ እርሱ በመጻሕፍት ሁሉ የተጻፈውን ተረጐመላቸው"* በጌታ በኢየሱስ ስም ይህ የትርጉም መንፈስ በምታነቡበት ቦታ ያግኛችሁ። ኢየሱስ ተሳስቶ የሰው ስብከት አልሰበከም፤ ስለ እርሱ ብቻ የተፃፈውን ከሙሴና ከነብያት አውጥቶ ተረጎመላቸው። ተስፋ ቆርጠዋል፣ ዝለዋል፣ ደክመዋል። ግን የማታስተውሉ ብሎ ከመዝለፍ ባለፈ ከማመን እንደዘገዩ ነው የተናገራቸው። *"እምነት ከመስማት ነው መስማትም በእግዚአብሔር ቃል ነው"* ይላል።

*"መስማትም በእግዚአብሔር ቃል"* ከሚለው ተነስተን ብዙዎቻችን ሙሉ መጽሐፍን ቅዱስን ከመስማት እምነት የሚመጣ ይመስለናል ለምን? አማርኛችን እንደዛ ብሎ ስለሚገልፀው። ነገር ግን በአንፕሊፋይድ ትርጉም *"እምነት ከመስማት ነው መስማትም ከክርስቶስ ቃል ነው"* ነው የሚለው። ይህም ማለት *"እምነት የሚመጣው ከመስማት ነው መስማትም ከክርስቶስ ነው"* ነው የሚለው። ኢየሱስን ስንሰማው ብቻ ነው ውስጣችን እምነት የሚፈጠርልን። ሙሴን ስንሰማው ኩነኔ ነው የሚፈጠረው። ሙሴ አትስረቅ አታመንዝር ሲልህ ውስጥህ የሚፈጠረው እምነት ሳይሆን አለመቻልህ፣ አለመብቃትህ፣ ኃጢአተኛነትህ ነው ብቅ የሚለው። ነገር ግን ክርስቶስን ስትሰማ እርሱ እንደሞተልህ፣ ከሙሴ ጀምሮ ስለ እርሱ የተነገረውን በጥቅስ እያዋዛ ይተረጉምልሃል።

መጽሐፍ ሲናገር "አመንኩ ስለዚህም ተናገርኩ ተብሎ እንደተጻፈ ያው የእምነት መንፈስ ስላለን" በዛው የእምነት መንፈስ እናምናለን፤ በዛው የእምነት መንፈስ እንናገራለን። ስለዚህ የእምነት መንፈስ ሲያገኝህ እንደ እነዚህ ሰዎች ውዳቂ የሆነ ነገር ማውራት ተያይዞ ሽንፈት ማውራት አትችልም። መጽሐፍ ቅዱስ ለትምህርታችን ነው የተጻፈው ለሕይወታችን ግን ኢየሱስ ነው።

አንድ ጊዜ ኢየሱስን በምኩራባቸው ጋበዙት። በምኩራብ እንግዳ ሆኖ አንድ ሰው በሰንበት እለት ሲገባ፣ በእለቱ የሚነበብ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል አለ እና በጣም በሚገርም ሁኔታ *"እሱ እንግዳ ነው የሚናገረው ነው ይኖረው ይሆናል"* ብለው መጽሐፍ አንስተው ይሰጧችኋል። ያም ሰው የሚናገረው ነገር ካለው ወይ ያስተምራል ወይ ይሰብካል። እናም ኢየሱስን እንደልማዳቸው የሚናገረው ነገር ካለ ብለው ጠሩትና ወጣ። የነብዩን የኢሳይያስን መጽሐፍ አንስተው ሰጡት። የኢሳይያስ መጽሐፍ 66 ምዕራፍ ያለው በመሆኑ ጥቅልሉ ትልቅ ነው። እሱ ያንን ጥቅልል

ተረተረና 61ኛው ምዕራፍ ላይ ቆመ *"ስለ እሱ የተጻፈውን አገኘው"* ይለናል። በኢየሱስ ስም ስለ እናንተ የተጻፈውን ማግኘት ይሁንላችሁ።

"የጌታ የእግዚአብሔር መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥ ለድሆች የምሥራችን እሰብክ ዘንድ እግዚአብሔር ቀብቶኛልና፤ ልባቸው የተሰበረውን እጠግን ዘንድ፥ ለተማረኩትም ነጻነትን ለታሰሩትም መፈታትን እናገር ዘንድ ልኮኛል። ፤ የተወደደችውን የእግዚአብሔርን ዓመእሰብክ ዘንድ ቀብቶገኛል" ብሎ አንብቦ መጽሐፉን ጠቅልሎ ሰጣቸው። የኢሳይያስ መጽሐፍ ላይ ግን "የተወደደችውን የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ" ካለ በኋላ "አምላካችንም የሚበቀልበትን ቀን እናገር ዘንድ፥ የሚያለቅሱትንም ሁሉ አጽናና ዘንድ፤" ብሎ ነው የሚያቆመው። ኢየሱስ ከፋፍሎ በማጥናት ወደር የለውም።

ከፍቶ "አምላካችንም የሚበቀልበት ቀን" አላለም። ክፍሉን ያብራራዋል ብለው ሲጠብቁ መጽሐፉን ጠቅልሎ ሰጥቶአቸው *"ይህ ቃል በጆሮአችሁ ተፈጸመ"* አላቸው። "ይህ ቃል ማለት ይኸው እኔ ነኝ፤ አልብራራም።" ማለቱ ነው። ስለ አንተ የተጻፈውን ስታገኘው ሆነህ ነው የምትሄደው መብራሪያ የለውማ። *"የአምላካችን የበቀል ቀን"*ካለ እግዚአብሔር በኢየሱስ መበቀል አለበት። ነገር ግን *"የተወደደችውን የጌታን አመት"* ነው ያለው። ኢየሱስ መስቀል ላይ ከዋለ ጀምሮ ለእግዚአብሔር 2000 ዓመት አይደለም። ለእግዚአብሔር አንድ ዓመት ነው። የተወደደች የጌታ ዓመት። ያንን ዓመት አውጆ ለእኛ ሁሉ ሰጥቶ ሄዶአል። ለእግዚአብሔር የተወደደች የጌታ ዓመት ምንድነው? እግዚአብሔር የሰው ልጆችን የኃጢአት ዕዳ ሁሉ ከፍሎ ህዝቡን ሁሉ ከታረቀ በኋላ ለእግዚአብሔር በዓል ነው፤ ፌሽታ ነው። ከፋፍሎ በማጥናት ከኢየሱስ ብዙ ምንማረው ነገር አለ።

*"ወደሚሄዱበትም መንደር ቀረቡ፣ እርሱም ሩቅ የሚሄድ መሰላቸው።"* እነርሱ። ከእኛ ጋር እደር፣ ማታ ቀርቦአልና ቀኑም ሊመሽ ጀምሮአል ብለው ግድ አሉት፤ ከእነርሱም ጋር ሊያድር ገባ። ከእነርሱም ጋር በማዕድ ተቀምጦ ሳለ እንጀራውን አንሥቶ ባረከው፣ ቈርሶም ሰጣቸው፤ ዓይናቸውም ተከፈተ፣ አወቁትም፤ እርሱም ከእነርሱ ተሰወረ። ሉቃስ 23፡28-31

*"ልክ ቆርሶ ሲሰጣቸው አይናቸው ተከፈተ"* እንደሚል አንተ የሚያስፈልግህ ጥቅስ መሸምደድ ሳይሆን የዓይን መከፈት ነው። አይንህ ሲከፈት መጽሐፍ ቅዱስን ብቻ ሳይሆን አለምን ራሷን ትተረጉማታለህ። ምክንያቱም አንተ መነጽሩ ነው የሚኖርህ። በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ይህንን መነጽር እንደምታገኘው እርግጠኛ ነኝ። የምታገኘው

ይህንን መነጽር እንጂ ሌላ አዲስ ኢየሱስ አይደለም። በዚህ መነጽር በውስጥህ ያለውን የከበረ ተስፋ የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስን ጠንቅቀህ ታውቀዋለህ። ምክንያቱም መነጽሩ እርሱ ስለሆነ። ለምሳሌ አንድ ሰው ጥቁር መነጽር ቢያደርግ ጥቁር መስለን ነው የምንታየው፤ ቀይ መነጽር ቢያደርግ ቀይ ነው የምንመስለው። አሁን የእኛ ጉዳይ ሳይሆን የመነጽር ጉዳይ ነው።

እግዚአብሔር ኢየሱስ የሚባል መነጽር ካደረገ 2000 ዓመት አልፎታል። አንተን ሲያይህ በክርስቶስ ነው የሚያይህ። ብቻህን አያይህም፤ ብቻህን አያውቅህም። አንተም ብቻህን እግዚአብሔር ጋር እሔዳለሁ ብትል በር እያለ በመስኮት መጥቶ ነው ብሎ ሌባ ነው የሚልህ።በሩ ማነው ኢየሱስ ነው። *"በእኔ በቀር..."* አይደል ያለው? ስለዚህ ወደ አብ ስትሄድ ራሱ ኢየሱስ የሚባል መነጽር አድርገህ *"አባት ሆይ በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ወደአንተ እመጣለሁ"* ስትል *"አቤት፣ በጌታ በኢየሱስ በኩል እሰማሃለሁ።"* ይልሃል። ምክንያቱም እግዚአብሔርንና ሰውን ያስታረቀ መካከለኛው ኢየሱስ ስለሆነ ነው።

ያለ ኢየሱስ መተርጎም አይቻልም። ስለዚህ እንዲያውቁት አይናቸውን ከፈተው። አይናቸው ሲከፈት ምን እንደሆነ እዩ። መሽቶባቸው ነው የመጡት፤ ሊያድሩ ነበር። እራት እየበሉ ቆርሶ ሲሰጣቸው አወቁት። ካወቁት በኋላ ከአይናቸው ተሰወረ። አያችሁ ካወቃችሁት በኋላ ካላየነው ማለት የለም። በእምነት ነው የምትመላለሰው እንጂ "ጌታ ሆይ ክብርህን፣ ክንድህን አሳየኝ ማለት አይኖርም። ኢጋንንት ሲወጣ አይደለም ጌታ ሠራ ብለን የምንደሰተው። በውስጥህ የድነትህ ማረጋገጫ አለ። በውስጥህ ያለው የእግዚአብሔር መንፈስ፦ ልጅ እንደሆንክ፤ ዳግም እንደተወለድክ ከመሰከረልህ የኢጋንንት መጮህ ለሌላ ለማያምን ሰው ነው።<< እንዴ! እንዲህም አለ እንዴ?>> ብሎ በመደነቅ ወደ ጌታ እንዲመጣ ነው። ድንቅ፣ ምልክት እና ተዓምራቶች ለማያምኑ ነው። ለእኛስ? በውስጣችን ያለው መንፈስ ይመሰክርልናል።

> *"እርስ በርሳቸውም። በመንገድ ሲናገረን መጻሕፍትንም ሲከፍትልን ልባችን ይቃጠልብን አልነበረምን? ተባባሉ። በዚያችም ሰዓት ተነሥተው ወደ ኢየሩሳሌም ተመለሱ፤" ቁ. 33-34*

አይንህ ሲበራልህ ወደ ጣልከው ወደ ተውከው ወደ ዋናው ስፍራ ትመለሳለህ። ተስፋ ቆርጠው ነበር የመጡት ነገር ግን ተስፋ አስቆርጧቸው የነበረው አይናቸው ተይዞ ስለነበረ ነው። አይናቸው ሲበራ ደክሞኛል ያሉ ሰዎች፣ ዝለናል ያሉ ሰዎች ማን እንደሆኑ እረሱ። እንደ እብድ ወደ ኢየሩሳሌም መንገድ ጀመሩ። መገለጡን

ሲያገኙ የዛለ እና የደከመ ሰውነታቸው በትንሳኤው መንፈስ ታድሶ እንደገና የመጡትን ረጅም መንገድ ተመለሱ።

በጌታ በኢየሱስ ስም የኤማሁስ መንገደኞችን የትንሳኤው ምስክሮች ያደረገ ያ መንፈስ ያግኛችሁ!

## *ጳውሎስ የሰበከው ኢየሱስን ነው!*

> *"ስለ እናንተ እንደ ተሰጠኝ እንደ እግዚአብሔር መጋቢነት፥ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ እንድሰብክ እኔ የቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆንሁ። ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው፥ አሁን ግን ለቅዱሳኑ ተገልጦአል። ለእነርሱም እግዚአብሔር በአሕዛብ ዘንድ ያለው የዚህ ምሥጢር ክብር ባለ ጠግነት ምን እንደ ሆነ ሊያስታውቅ ወደደ፥ ምሥጢሩም የክብር ተስፋ ያለው ክርስቶስ በእናንተ ዘንድ መሆኑ ነው። እኛም በክርስቶስ ፍጹም የሚሆን ሰውን ሁሉ እናቀርብ ዘንድ ሰውን ሁሉ እየገሠጽን ሰውንም ሁሉ በጥበብ ሁሉ እያስተማርን የምንሰብከው እርሱ ነው። ለዚህም ነገር ደግሞ፥ በእኔ በኃይል እንደሚሠራ እንደ አሠራሩ እየተጋደልሁ፥ እደክማለሁ።" ቆላስይስ 1፡24-29*

ጳውሎስ የሰበከው ኢየሱስን ነው። ማን ቃሉን ሔዶ ያመጣልኛል እንዳይል፣ *"ቃሉ በአፍህም በልብህም ሆኖ ቀርቦልሃል።"* እንዳለው ይህም *"የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው።"* ነው ያለው። በሌላ ስፍራ ጳውሎስ የእግዚአብሔር ምስጢር ክርስቶስ እንደሆነ ነግሮናል። በዚህም ክፍል *"ይህም ቃል ከዘላለምና ከትውልዶች ጀምሮ ተሰውሮ የነበረ ምሥጢር ነው"* የሚለው ኢየሱስን ነው። እናም ይህንን ምስጢር ነው እንግዲህ የእግዚአብሔርን ቃል ፈጽሜ ሰብኬዋለሁ ያለው። አሁን ኢየሱስ ተገልጧል። ኢየሱስ ከመምጣቱ በፊት ግን በብሉይ ኪዳን ውስጥ የተገለጠ ነገር አታዩም። ብዙ ነገር ምስጢር ነው፣ አይደል? አሁን ግን ቅዱሳን ለሆንን ለእኔና ለእናንተ ተገልጧል። ክርስቶስ ተስፋ የነበረው ለአይሁድ እንጂ ለአህዛብ አይደለም። ጌታ ኢየሱስም ሲመጣ *"እኔ ከእስራኤል ቤት ለሆኑት እንጂ ለአህዛብ አልመጣሁም"* ብሏል። ተልኮ የመጣው መሲህነቱ ለእስራኤል ነበር። ከዘላለም ዘመናት በፊት አህዛብ በወንጌል እንደሚድን፣ በክርስቶስ እንደሚጠቀለል ምስጢር ነበር። አሁን ግን ለእስራኤል ብቻ ሳይሆን ኢትዮጲያ ውስጥ ላለ አንድ አማኝ ጭምር ነው። ለእስራኤል ብቻ አይደለም አሁን ኢየሱስ ለዓለም ሆኗል።

ጌታ ኢየሱስ "መጽሐፍት ስለ እኔ ይናገራሉ" ብሏል። የብሉይ ኪዳን ነብያቶች ስለ ኢየሱስ ይናገራሉ። ከመስቀል በኋላ ሐዋርያቶች ስለ ኢየሱስ የመሰከሩት፣ የሚገስጹበት፣ ሰውን

ፍፁም የሚያደርጉበት የሚሰብኩት ክርስቶስ ነው። ስለዚህ መጽሐፍት ስለ ኢየሱስ እንጂ ስለ ሁኔታ እና ስለ እኛ አያወሩም። እኛ ያለነው በክርስቶስ ነው። ጳውሎስ ሰውን ሁሉ የሚመክርበት *"አንዱ መመሪያው የምንሰብከው ክርስቶስን ነው"* ። ከኢየሱስ ውጪ ሌላ ነገር መስበክ ነውር ነው። እሱ ካለ ሁሉ አለ። ያለ እርሱ ግን ሁሉ ነገር ባዶ ነው።

## *መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና በምን መልኩ ነው የምናነበው/ የምናጠናው? ሶስት ጥያቄዎችን እንጠይቃለን።*

1. *መጽሐፍ ቅዱስን ሙሉውን መስበክ እና ማጥናት አለብን ወይንስ ከመጽሐፍ ቅዱስ ሁሉና ሙሉ ውስጥ ኢየሱስን መስበክ እና ማጥናት አለብን?*

ይሔ የብዙዎቻችን ጥያቄ ነው። በጣም ብዙ ጊዜ የሚገጥመኝ "እኔ ምለው እንዴት ነው ጥቅሱን በቃልህ የምትይዘው? እኔ በቃሌ ለመያዝ በጣም እታገላለሁ፤ ነገር ግን ይጠፋብኛል። የተለየ የአጠናን ዘዴ አለህ?" ይሉኛል።የተለየ የአጠናን ዘዴ የለኝም። ለመያዝ ስትታገሉ ትረሱታላችሁ። መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እና ስናጠና ማጥናትም ማንበብም ያለብን በመጀመሪያ ደረጃ ክርስቶስ ኢየሱስን ለማግኘት እንጂ ጥቅስ ለመያዝ መሆን የለበትም። ጥቅስ የማያውቅ ኢየሱስ የገባው ሰው፤ ጥቅስ ከሚያውቅ ግን ኢየሱስን ከማይገልጥ ሰው ይሻላል። ጥቅስ ማወቅ የመንፈሳዊ ደረጃ መለኪያም አይደለም። በቤተክርስቲያን ውስጥ የሌሉ በዓለም ያሉ ከእኛ በተሻለ ጥቅስ ይጠቅሳሉ። ነገር ግን ጳውሎስ አዲስ ኪዳን ሳይኖረው በብሉይ ኪዳን ብቻ *"የምንሰብከው እሱ ነው"* ካለ እኛም መጽሐፍ ቅዱስን ስናጠና ኢየሱስ ክርስቶስን ለማግኘት ብቻ መሆን አለበት። አካሉ መጥቶ በጥላው አይኖርምና።

የእግዚአብሔር ሰው ኬኔት ኢ. ሀገን እንደዚህ ይሉ ነበር *"በተቻለህ አቅም መልዕክቶችን ስበክ። ነገር ግን ወደ ብሉይ ኪዳን ከሄድክ እባክህ ኢየሱስን ፈልግ። ካላገኘኸው ግን ዝለለው"* ይላሉ። ለምን? በብሉይ ኪዳን ተሰውሮ የነበረው ኢየሱስ አሁን በአዲስ ኪዳን መልዕክት ውስጥ አለልህ። የአዲሱ ኪዳን መልዕክት በብሉይ ኪዳን ተሰውሮ የነበረ እንጂ አዲስ የሆነ የፈነዳ ነገርም አይደለም። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን መነፅር ወደ ብሉይ ኪዳን ይኬዳል እንጂ፤ በብሉይ ኪዳን መነፅር ወደ አዲስ ኪዳን አይመጣም። እግዚአብሔር ያደረገው መነፅር ኢየሱስ ነው። ስለዚህ ማንንም ሰው ሲያይ ርኩስ፣ ቆሻሻ፣ እድፋም አያይም። ምክንያቱም የከፈለውን ልጁን ያየዋል። ሰውየው ይመንም አይመንም እግዚአብሔር ከሰማይ ሲያየው የተጣላው ሰው የለም። *"ምክንያቱም በክርስቶስ ሆኖ አለሙን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር።"*

በሌላ አነጋገር ታርቆ ጨርሷል ማለት ነው። እግዚአብሔር ከዓለም ጋር ታርቆ ጨርሷል፤ አሁን ዓለም ነች ከእርሱ ጋር መታረቅ ያለባት። ሰዎች ናቸው ከእግዚአብሔር ጋር መታረቅ ያለባቸው። በሌላ አነጋገር በመስቀል በተሠራው ሥራ እግዚአብሔር ኢየሱስ የሚባል መነፅር አድርጓል። አንተንም ሲያይ፣ ያላመነውንም ሲያይ፣ እኩል ነውር አልባ ነህ። ልዩ ያደረገህ እሱ እንደሚያይህ አንተ ራስህን እንድታይ አሜን ብለሃል። እሱ ደግሞ አሜን ብሎ አልተቀበለም።አንድ ቀን አሜን ብሎ ሲቀበል ደግሞ እኩል ነው የምትሆኑት። ስለዚህ አሁን እዚህ መጽሐፍ የምናደርገው በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን መነጽር ኢየሱስን አጥልቀን እግዚአብሔር እንደሚያይ እንድናይ ነው።

2. ከመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የምናነበውን ሁሉ መስበክ ወይስ ከምናነበው መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ የጸጋን ወንጌል መስበክ አለብን?

ብዙ ሰው የሚሰብከው ብዙ ነገር አለው። የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት ለመስበክ በጣም አሪፍ ነው ለማስተማር ግን አይሆንም። የምናነበውን ሁሉ መስበክ ነውር ነው።

ለምሳሌ “እግዚአብሔር ይገድላል፤ እግዚአብሔር ያድናል...” የሚለውን ከመጽሐፈ ሳሙኤል አንስቼ ልሰብክ እችላለሁ። ይህ ክፍል ሀና ስለ እግዚአብሔር ያላትን እውቀት ያወራችበት እንጂ እግዚአብሔር፣ *“እኔ እገድላለሁ ከዛም አድናለሁ”* አላለም። ፍናና ታስቆጣት ስለነበረ የመልስ ምት እንጂ የእግዚአብሔር ቃል አይደለም።

*“እግዚአብሔር ሰጠ እግዚአብሔር ነሳ የእግዚአብሔር ስም ይባረክ”* ብሏል ኢዮብ። ዛሬም ሰው ይሔን እጠቀምበታለሁ ቢል፣ ምስኪን ነው የምንለው። ምክንያቱም እግዚአብሔር *“እኔ ሰጠሁ፣ እኔ ነሳሁ”* አላለም። ስለዚህ የእግዚአብሔርን ቃል ከፋፍለን ስናጠና የኢዮብን ንግግር ኢዮብ አለ ነው እንጂ የምንለው እግዚአብሔር አለ አንልም። ኢዮብን እግዚአብሔር መጥቶ ሲያወራው ግን *“በል ወገብህን ታጠቅ፤ እኔም እጠይቅሃለሁ አንተም መልስልኝ። ለሜዳ አህያ ነጻነቱን የሰጠው ማነው?”* እኔ እኮ እግዚአብሔር የምባል የሰራሁ አላለም። *“ለክፉ ቀን ለጦርነት ጊዜ ያዘጋጀሁት የበረዶ ቤቱ የት ነው ታውቀዋለህ?”* አለው። እግዚአብሔር ጥያቄ ብቻ ነው የጠየቀው፤ እናም ኢዮብ ግራ ተጋባ። ምክንያቱም ቀድሞ ብዙ ብሏል። *“እኔ እንደ እግዚአብሔር አይደለሁም ባገኝሁት፤ እጁን በእኔና በእሱ ላይ የሚጭን ዳኛ ምነው በተገኘ”* ብሏል።

አልፈራውም እናገረው ነበር። እኔን እንዴት እንዲህ ያደርገኛል። እሱ ነው በቁስል የመታኝ አለ። ግን መጽሐፉን ሲዘጋው *"ያለ እውቀት የሚነገር የጨለማ ምክር"* ብሎ ነው የዘጋው። ለ38 ምዕራፍ በሙሉ ያለእውቀት የሚነገር የጨለማ ምክር ነበር። በል አሁን እኔና አንተ እናውራ። እንዋቀስ ብለህ የለ፣ ዳኛ ምነው በተገኘ ብለህ የለ፤ ችግር የለም ሰውም ባይኖር እኔ እጠይቅሃለሁ አንተ መልስ። *"ፈረስ በጦርነት ጊዜ ይስቃል።"* አለው። ይህ ለኢዮብ ምትሀት ነው። ለካ እስከዛሬ በስሚ ነው የኖርኩት አለ። አሁን ግን አይኔ አየችህ።

እዮብ እግዚአብሔር እጥፍ አድርጎ መለሰለት። "የካሳ ዓመትህ ነው የሚባል ስብከት ሰምታችሁ ታውቃላችሁ? እግዚአብሔር የካሳ ክፍያ የሚባል ነገር የለውም። እግዚአብሔር እየካሰሸ ከሆነ ቀድሞ በድሎሻል ማለት ነው። ሰይጣን ያከሰረህን ግን እግዚአብሔር ሊበቀል ይችል ይሆናል። ግን እግዚአብሔር በድሎህ አይክስህም። "ተምች እና ኩብኩባ የበላብህን አመት እኔ እመልሳለሁ" ስለዚህ የበላብህ ተምች ነው፤ እግዚአብሔር አይደለም። እግዚአብሔር ግን እንደ ተምች እንደበላብህ አይመልስልህም። ስጦታው ግን እንደ በደላችን መጠን አይደለም ነዋ የሚለው። ስለዚህ ስጦታው በበደልህ ልክ ሳይሆን ያንተን በደል የሚያስጥል፤ እጅ በአፍ የሚያስጭን መልስ ነው የሚመልሰው። ለዚህ ነው እዮብም እጁን በአፉ ላይ እስኪጭን ድረስ የተገረመው።

ሐዋርያት ስራ 15 ላይ ስታነቡ ትልቅ የቤተክርስቲያን ስብሰባ እንደነበር ታያላችሁ። አህዛብ በወንጌል እውነት አምነው ሲድኑ አሁን የመጀመሪያው ቤተክርስቲያን ነው። የመጀመሪያዎቹ ሐዋሪያቶች የአይሁድ ሐዋርያት ናቸው። ጴጥሮስ በራዕይ *«ሂድ አርደህ ብላ»* ሲባል *እንኳን* እኔ አልበላም ርኩስ ነው ነበር ያለው። እኔ ያነጻሁትን አንተ አታርክስ ተብሎ በስተመጨረሻ ወደ ቆርኔሌዎስ ቤት ሔደ። ልክ ሲገባ ግን *"እኛ አይሁዶች ታውቃላችሁ ከእናንተ ጋር ህብረት የለንም እምቢ እንዳልል አርደህ ብላ ብሎኝ"* ብሎ ነው የጀመረው። ልክ አፉን ከፍቶ መናር በጀመረ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ይህንንም ለአዕማድ ሲናገር ልክ *"እኛ ላይ እንደወረደው አይነት"* ነበር ያለው። እጅ ጭኖ መንፈስ ቅዱስ እንዲወርድ አልጸለየላቸውም። ልክ እነሱ ላይ እንደወረደው ቃሉን በሰሙት ሁሉ ላይ መንፈስ ወረደባቸው።

አህዛብ መዳን ሲጀምሩ ፀብ መፈጠር ጀመረ። ምክንያቱም አይሁዶች በመገረዝ ስለሚያምኑ፣ አህዛብን *"በወንጌል ብቻ አትድኑም መገረዝ ደግሞ አለባችሁ"* ብለው ወንጌሉ ላይ መገረዝን ጨመሩበት። በዚህ ምክንያት ፀብ ስለተፈጠረ በዚህ ጉዳይ ላይ ለመወሰን በኢየሩሳሌም ተሰበሰቡ። ምን ትላላችሁ ሲባል ጴጥሮስ "ያው

ታውቃላችሁ አርደህ ብላ ስባል እምቢ ብዬ ነበር ነገር ግን እኔ መናገር በጀመርኩ ጊዜ ያኔ ልክ በእኛ ላይ እንደወረደው መንፈስ ቅዱስ በእነሱም ላይ ሲወርድ አይቻለሁ እና እግዚአብሔር አህዛብን በንስሀ ሊያድን እንደወደደ ገባኝ።

ስለዚህ አሁን ስለገባኝ እኔ እጄን በዚህ ውስጥ ጣልቃ አላስገባም። እርሱ ካዳነ እኛም አብረን መተባበር ነው ያለብን እና እረፉ" ሲል ተናገረ። ስለዚህ ያዕቆብ ጠቀለለና *"እኛና አባቶቻችን ልንሸከመው ያልቻልነውን ቀንበር በአህዛብ ላይ ደግመን አንጭንም"* መገረዝ እና ሕግን መጠበቅ ሊሸከሙት ያልቻሉት ቀንበር ነው። *"እንግዲህ ሙሴ በየሰንበቱ የሚሰብኩለት አሉ"* አያችሁ ሙሴን የሚሰብኩ አሉ ማለት ነው። ያነበብነው ሁሉ አይሰበክም። ኤልያስን ሰብካችሁ አትውረዱ፤ ኢየሱስን ብቻ ስበኩ። ያነበብነው ሁሉ አይሰበክም፤ ካነበብነው ውስጥ የጸጋው ወንጌል ብቻ ይሰበካል።

ሐዋርያት ስራ 20፡24 ላይ ጳውሎስ እንዲህ አለ፣ *"ነገር ግን ሩጫዬን እና ከጌታ ከኢየሱስ ክርስቶስ የተቀበልኩትን አደራ፤ እርሱም የእግዚአብሔርን ጸጋ ወንጌልን መመስከር እፈፅም ዘንድ ነፍሴ በእኔ ዘንድ እንደማትከብር እንደ ከንቱ ነገር እቆጥራለሁ"* ከጌታ ከኢየሱስ የተቀበልነው አደራ እርሱ ሰርቶ የጨረሰውን እንድንነግር እንጂ ሙሴን እንድንሰብክ አልተጠራንም። ሙሴና ኤልያስ ኢየሱስን ሰብከው ነው የሞቱት። እኛም በዚህ ያለነው ኢየሱስን ብቻ ልንሰብክ ነው።

ማቴ. 17፡1-9 ላይ ኢየሱስ ያዕቆብን፣ ዮሐንስን እና ጴጥሮስን ይዞ ወደ መገለጥ ተራራ ወጣ። በዛም እየፀለዩ እያለ ድንገት የኢየሱስ ፊት ተለወጠ። ልክ ፊቱ ሲያበራ ሙሴና ኤልያስ ደግሞ ተገለጡ። ሙሴንና ኤልያስን ከዚህ በፊት አይተዋቸው አያውቁም። ነገር ግን በመገለጥ ውስጥ ሲመጡ እነሱ እንደሆኑ እርግጠኛ ሆነው ነበር። በዚህም ምክንያት ያዕቆብ፣ ዮሐንስ እና ጴጥሮስ በጣም ደንግጠዋል። ሙሴና ኤልያስ ከኢየሱስ ጋር እየተነጋገሩ ሳሉ ጴጥሮስ መጥቶ *"ጌታ ሆይ፣ አንድ ላንተ፣ አንድ ለሙሴ፣ አንድ ደግሞ ለኤልያስ ድንኳን እንሥራ። ለእኛ በዚህ መሆን መልካም ነው። "* አለ

እኛም ሶስት እናንተም ሶስት ናችሁ። ስለዚህ አንዳንዴ እኔ አንተ ጋር ስመጣ፣ ዮሐንስ ደግሞ ሙሴ ጋር ይገባል። ያዕቆብ ደግሞ ኤልያስ ጋር ይገባል። እንደዚህ እየተፈራረቅን ብቻ እንማር። ሙሴ ሕግን የሰጠን ነው፤ ኤልያስ ደግሞ የሚገርም ነብይ ነው። አንተም ያው ቸር መምህር ነህ። ስለዚህ ለእኛ በዚህ መሆን ይሻለናል። ስለዚህ ሶስት ድንኳን እንስራ። ለራሱ አላሰበም ምክንያቱም እሱ ከእነሱ ጋር ሊዳበል

ነው ያሰበው። ይህንን ንግግሩን ሳይጨርስ ሰማይ ተከፍቶ *"የምወደው ልጄ እሱ ነውና እሱን ብቻ ስሙት"* አለ። እነርሱን ሳይሆን እርሱን ብቻ ስሙት አለ። ወዲያውኑ ይሔ ድምፅ በመጣ ጊዜ ሙሴና ኤልያስ ሰላም ብለው ሔደዋል።ሙሴም ኤልያስም አልቀጠሉም የቀረው ኢየሱስ ብቻ ነው። ጴጥሮስ ንግግሩን እስኪጨርስ ድረስ ሰማይ አልታገሰም። ምክንያቱም የጴጥሮስ ንግግር ጤናማ እንዳልሆነ ሰማይ አውቋል። ጣልቃ ገብቶ ነብይ ወይም የሆነ የእግዚአብሔር ባሪያ የሚባል የተቀባ ሳይጠቀም ሰማይ ተከፍቶ ራሱ መልስ ሰጠ። ጴጥሮስ ሶስት ድንኳን የፈለገው ሶስቱም ጋር ለመስማት ስለነበር ነው። ሁለት ባል በአንድ ቤት ውስጥ አይፈቀድም። ራስ ክርስቶስ ነው፤ ሲደመር ምንም ነው።

ሌላ ምንም የለም፣ ሙሴ የለም፣ ኤልያስ የለም፣ መገረዝ የለም፣ ሕግ የለም፤ ኢየሱስ ሲደመር ምንም እኩል ይሆናል ሁሉንም ነው። ጴጥሮስ በመልዕክቱ ከገናናው ክብሩ የክብርና የምስጋናን ዘውድ ሲቀበል ሰምቻለሁ አለ። ኢየሱስ ይህንን ሞቶ እስኪነሳ እንዳይናገሩ ተናግሯቸው ነበር። ምክንያቱም ከትንሳኤው በኋላ የሚገባበትን ክብር ነበር ያዩት። ሮሜ 3፡21 *"ሕግ እና ነቢያት የመሰከሩለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጧል"* ነው የሚለው። ነቢያት የተነበይንለት እርሱ ነው ብለው ነው የመሰከሩት።

ሙሴ *"እግዚአብሔር እንደ እኔ ያለ ነብይ ያስነሳላችኋል"* ብለን የተናገርነው እርሱን ነው ብሎ መሰከረ። *እርሱን የማትሰማ ነፍስ ትጠፋለች።* ስለዚህ መጽሐፍት በሙሉ ስለ ኢየሱስ ስለሚናገሩ ከምናነበው መጽሐፍ ውስጥ የጸጋውን ወንጌል ነው የምንሰብከው። በዮሐንስ 1፡17 ላይ *"ሕግ በሙሴ ተሰጥቶ ነበር፣ ጸጋና እውነት ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ሆነ።"* ይላል። ጸጋና እውነት ተሰጠ ሳይሆን ጸጋና እውነት ሆነ። ኢየሱስ ሲባል ጸጋ ነው ኢየሱስ ሲባል እውነት ነው። *"እኛም ሁላችን አንድ ልጁ በአብ ዘንድ ያለውን ክብር አየን… በጸጋ ላይ ጸጋ ተሰጥቶናል"* ጸጋ ማለት ነጻ የእግዚአብሔር ስጦታ ሲሆን ርካሽ ሳይሆን እግዚአብሔር የከፈለበት እኛ ልንከፍል የማንችለው የከበረ ስጦታ ነው።

3. አሁንም በአሮጌው ኪዳን ስር እንዳላችሁ በማሰብ መጽሐፍ ቅዱስን ትሰብካላችሁ፣ ታጠናላችሁ ወይስ በአዲሱ የጸጋ ኪዳን ስር እንዳላችሁ ታስባላችሁ?

መጽሐፍ ቅዱሳችን ላይ አዲስ ኪዳን እና ብሉይ ኪዳን የሚል ሁለት ቃል እናገኛለን። ልክ የሚልክያስን መጽሐፍ ስንጨርስ አዲስ ኪዳን የሚል እናገኛለን። ነገር ግን ሰዎች እንጂ እግዚአብሔር እሱን አዲስ ኪዳን አላለውም። ምክንያቱም ጌታ ኢየሱስ

የመጨረሻውን ራት ሲሰጥ *"ይህ ስለእናንተ የሚቆረስ ሥጋዬ ነው ካለ በኋላ እንደገና ጽዋውን አንስቶ ስለ ኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው።"* የሚፈስ ካለ ገና አልፈሰሰም ነበር። ደም ሳይፈስ ደግሞ ኪዳን የለም። ስለዚህ ከማቴዎስ 1፡1 ጀምሮ እንትና እንትናን ወለደ የሚለው የአዲስ ኪዳን መልዕክት አይደለም። አዲስ ኪዳን ኢየሱስ ደሙ ሲፈስ እና ከሞተ ሲነሳ ነው ኪዳኑ የጸናው። በየትኛው ኪዳን ሥር ነው ያለነው የሚለውን ለመፍታት ብሉይ ኪዳን የጀመረው መቼ እና እንዳት እንደሆነ ማውቁ መልካም ነው ።በዘጸአት ምዕራፍ 20 ላይ ሳይሆን 24 ላይ፣ ሕጉ ሲሰጥ ሳይሆን መጽሐፉን አንብቦላቸው በደም ሲረጩ ሕጉን እንፈጽማለን ብለው ኪዳን ሲገቡ ነው። አዲስ ኪዳን ደግሞ የጀመረው ኢየሱስ ደሙን ሲያፈስ መስቀል ላይ ተፈፀመ ባለበት ውቅት ነው። ታዲያ ማርቆስ፣ ሉቃስ፣ ዮሐንስ እና ያዕቆብ አዲስ ኪዳን አይደሉም ማለት ነው? ይህን ጥያቄ በጊዜው እንመልሰዋለን።

**ለምሳሌ፡-** *"አይንህ ብታሰናክልህ አውጣት፣ እጅህ ደግሞ ብታሰናክልህ ቁረጣት፤ ሁለት እጅ ኖሮህ ሲኦል ከምትገባ አንድ እጅ ኖርህ መንግስተ ሰማያት ብትገባ ይሻላል።"* ይላል። የመንግስተ ሰማያት መግቢያ በሩ በኢየሱስ ማመን ነው እንጂ አይን ማውጣት ወይም እጅ መቁረጥ አይደለም። ስለዚህ ይሔ መልዕክት የአንተ አይደለም ማለት ነው። አይንህን አውጣ፣ እጅህን ቁረጥ የሚለው ለእኛ በክርስቶስ ለምናምን የተጻፈ አይደለም። ጌታ ኢየሱስ ይህን እየተናገረ የነበረው እዛው ተራራው ስር ለተሰበሰቡት ነው እንጂ ኢትዮጵያ ውስጥ ላለነው ለእኛ አላወራም።

መንፈስ ቅዱስ ከመስቀል በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ተነድቶ በዛ ስፍራ ላልነበርነው ለእኛ ታሪኩን ተረከልን። ይህን ለትምህርታችን መንፈስ ቅዱስ እንዲጻፍ አድርጎታል። ለሕይወታችን ግን እሱ ቃል አልተሰጠም። በእኔ ብታምኑ የዘላለም ሕይወት አላችሁ አለ እንጂ አይናችሁን ብታወጡ መንግስተ ሰማያት ትገባላችሁ አላለም። አይኑ የማያሰናክለው ማን አለ። አለ ቢባልም ውሸት ነው *"የአይን አምሮት፣ የሥጋ ምኞት፣ ስለ ኑሮ ትምክህት..."* የሚለው ለዚህ ነው። እኛ የእነዚህ ሶስቱ ተጠቂዎች ነን። ይህንን ቃል እንተገብራለን ካልን ቸርች ቄራ ነው የምትሆነው።

ዘጸአት 24 ላይ ሕጉ ሲሰጥ ሁሉም እናደርጋለን ስላሉ። በዘጸአት 32 ላይ "በዚያን ጊዜ 3000 የሚያክሉ ሰዎች ሞቱ" ይላል። ሕጉ በተሰጠበት በኪዳኑ በተስማሙበት በዚያን ጊዜ 3000 ሰው ሞተ። መንፈስ በመጣበት በዚያን ጊዜ ደግሞ 3000 ሰው ዳነ። የትኛው ጋር ነህ? ገዳዩ ጋር ነህ ወይስ አዳኙ ጋር? የቱ ጋር ሆነህ ነው መጸሀፍ የምትፈታው? የሚለው ወሳኝ ጥያቃ ነው። ይህንን ልዩነት ያመጣው ደግሞ

የክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ነው። የእሱ መስዋዕትነት ሰማይን ከምድር አስታርቋል ሰማይ መግባት ያልቻለን ሰው ልጅ አድርጎ ያስገባው እሱ ነው።

አሁንም በብሉይ ኪዳን ስር እንዳለ የሚያስብ ሰው "ጌታ ሆይ እኔ አሁን የበደሉኝን ይቅር እንደምል በደሌን ይቅር በለኝ" ይላል። ምክንያቱም ኢየሱስ ሲያስተምር እኛም የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን ብላቹሁ ጸልዩ ብሏልና ሊል ይችላል።

የበደሏችሁን ይቅር እንደምትሉ አባታችሁ ኃጢአታችሁን በሙሉ ይቅር ይላችኋል የሚል ስብከት ነው የሰበከው። ለማን ነው ሲባል አንደኛ፣ ጸሎት መማር ለፈለጉ። ሁለተኛ፣ ለደቀመዛሙርቶቹ። በዚህ መሰረት እኛ ይቅር የምንባለው እኛ ሌሎችን ይቅር ባልነው ልክ ነው። ያንን ለማለት ደግሞ እኛ ምን ያህል ይቅር ባዮች ነን የሚለው ጥያቄ ውስጥ ይገባል። እኛ በሕይወታችን ይቅር የምንል ሳንሆን እንደውም ብዙዎችን የምናሳዝን ነን። በአዲሱ ኪዳን ስር ያለ ሰው ደግሞ "ማንንም ይቅር ሳልል ይቅር ስላልከኝ ሁሉን ይቅር እላለሁ" ይላል። ምክንያቱም

ከመስቀል በኋላ ጳውሎስ፣ *"በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ። እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳላችሁ ይቅር ተባባሉ"* ብሏል። ስለዚህ አሁን እኛ ይቅር የምንለው እግዚአብሔር በክርስቶስ ይቅር እንዳለን እንጂ፤ ይቅር ያለልነውን ቆጥረን *"ይኸው 10 ሰው ይቅር ብያለው"* ብለህ አስቆጥረን አይደለም ይቅር የምንባለው። ስለዚህ በየትኛው ኪዳን ስር ሆነን እንደምናነብ መፍታት የግድ ነው።

*"ፊደል ይገድላል መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል"* ስለሚል። ብዙ ሰው ይህንን ቃል የሚረዳው መጽሐፍ ቅዱስን ማጥናትና የእግዚአብሔርን ቃል ማወቅ ይገድላል ብሎ ነው። ክፍሉ ግን ፊደል ይገድላል ያለው ሕጉን ነው። ስለዚህ ከመስቀል በኋላ ቆመህ ሕጉን የምትሰብክ ከሆንህ ገዳይ ነህ እንጂ አዳኝ አይደለህም። ነገር ግን ኢየሱስን ስትሰብክ ለሰዎች ሁሉ ሕይወት ነው።

## *መጽሐፍ ቅዱስ የሚናገርላቸው ሶስቱ ሰዎች*

1. አይሁድ
2. አህዛብ
3. የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን (አዲሱ ፍጥረት)

መጽሐፍ ቅዱስ ከእነዚህ ከሶስቱ ውጪ ለማንም አይናገርም።

በተለይ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍት በእስራኤልና በህዝቡ መካከል ያለ ታሪክ ነው። በብሉይ ኪዳን ውስጥ እግዚአብሔር ለአይሁድ ከተናገረው አንጻር ለአህዛብ በጣም ጥቂት ነው የሚናገረው። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስን ስናነብ እግዚአብሔር ከሶስቱ ህዝብ ውጪ እግዚአብሔር ለሌላ አይናገርም። በ1ኛ ቆሮ 10፡32 ላይ

> *"እኔ ደግሞ ብዙዎች ይድኑ ዘንድ ለጥቅማቸው እንጂ የራሴን ጥቅም ሳልፈልግ በሁሉ ነገር ሰውን ደስ እንደማሰኝ ለአይሁድ ለግሪክ ሰዎች ለእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ማሰናከያ አትሁኑ፡፡"*

ግሪክ የሚለው አህዛብን ነው። የእግዚአብሔር ቤተክርስቲያን ደግሞ የሚለው በፊት አይሁዳዊ ወይንም በፊት ግሪካዊ የነበረ አሁን ደግሞ በክርስቶስ ኢየሱስ አምኖ በመዳን አዲስ ፍጥረት የሆኑትን ነው። በቆላስይስ እና ገላትያ መጽሐፍት ላይ *"አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፣ ባሪያ ወይም ጨዋ የለም፣ ወንድም ሴትም የለም ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁ"* ይለናል። ይህ መልዕክት በዋነኝነት አዲስ ፍጥረት ለሆኑት እንጂ ለአይሁድ ወይም ለአህዛብ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በ1ኛ ቆሮ 6፡17 ላይ "ሲናገር ከጌታ ጋር የሚተባበር አንድ መንፈስ ነው።" ስለዚህ ወንድ ካልሆንክ ሴትም ካልሆንክ ዳግመኛ በመወለድ አዲስ ፍጥረት የሆነው መንፈስ የሆነው ማንነትህ ነው።

እየተናገረ ያለው ስለዚህ ስለለበስነው *ሥጋ* አይደለም። ጌታን የተቀበልን ቀን ጆሮዎቻችን ያደገ ሰዎች አለን? እግሩ በፊት ከነበረው የረዘመ ሰው አለ? ሁላችን ዳግም ሳንወለድ በፊት የነበረን ሰውነት ነው የያዝነው ነገር ግን ውስጣችን የሆነ እንግዳ ነገር ተፈጥሮአል። በዚህ እርግጠኞች ነን፤ ያ ማለት ደግሞ ዳግም የተወለደው መንፈሳችን እንጂ *ሥጋችን* አይደለም ማለት ነው። ይህ ሲገባህ ቤተክርስቲያን ላይ ሴት ማገልገል የለባትም አትልም ምክንያቱም ወንድ የለም ሴት የለም ስለሚል። ታዲያ ማን ያገልግል? አዲስ ፍጥረት የሆነ ሰው ሁሉ አገልጋይ ነው።

አንድ ጊዜ አንዷት ሴት ኬንያ ላይ ስታገለግል ቁጭ ብለው ይሰሟት ከነበሩ ሰዎች መካከል አንድ ሰው። ጉባኤው ሲያልቅ መጥቶ *"አንቺ የምትገርሚ ነሽ። ወንድ ራሱ እንዳንቺ አያገለግልም።"* አላት። እሷም፣ *"አታውቅም እንዴ ወንድም ሴትም እኮ እንደ እኔ አይሰብክም እኮ አዲስ ፍጥረት ብቻ ነው እንደዚህ የሚሰብከው"*አለችው። ሴቶች ተነሱ! እናንተ አዲስ ፍጥረት ናችሁ! ስለዚህ በአገልግሎት አግዙን!!

## *ሶስት ህዝብ ሲያይ ታዲያ እግዚአብሔር ስለምን እያወራ ነው?*

- አይሁድ ያለው ሕግ የእግዚአብሔር ሕግ ወይንም የሙሴ ሕግ ነው።
- አህዛብ ያለው ሕግ ደግሞ ሕሊና ሕግ ነው።
- ቤተክርስቲያን ደግሞ ያላት ሕግ ፍቅር ነው።

በጣም ብዙ ጊዜ ቤተክርስቲያን ውስጥ እየተፈጠረ ያለው ችግር፣ የአይሁድን መልዕክት በቤተክርስቲያን ላይ እናመጣዋለን። የአህዛብን መልዕክት ደግሞ አይሁድ ጋር እናመጣዋለን። በዚህም ምክንያት የመንፈሳዊ ሕይወት እድገት ሳይሆን መገታት ነው ያለው። መንፈሳዊ ዓለም ላይ ሥር ሰደን ውጤታማ እንዳንሆን ካደረገን አንዱ ለኛ ያልሆነን መልዕክት የኛ አድርግን መውሰዳችን ነው።

ለምሳሌ ሮሜ መጽሐፍ ለቤተክርስቲያን የተጻፈ መልዕክት ነው። ሮሜ 7 ስታነቡ ግን *"ወንድሞች ሆይ ሕግን ለሚያውቁ እናገራለሁ…"* ብሎ ነው የሚጀምረው። ለሮሜ ቤተክርስቲያን የተፃፈ ነው ነገር ግን የሚያወራው ሕጉ ለተሰጣቸው ለአይሁድ ነው። ገላ 3፡13-14 *"በእንጨት የሚሰቀል ሁሉ የተረገመ ነው ተብሎ እንደተጻፈ ክርስቶስ ስለ እኛ እርግማን ሆኖ ከሕግ እርግማን ዋጀን"* ይሔ መልዕክት ቤተክርስቲያንን ወይንም አዲስ ፍጥረት የሆኑትን አያወራም። ምክንያቱም ከሕግ እርግማን ዋጀን ያለው ሕግ የተሰጣቸውን አይሁድን ነው።

በዚህ አጋጣሚ ሶስት ዓይነት እርግማን አለ። አንደኛ፣ የአዳም እርግማን፤ ሁለተኛ፣ የሕግ እርግማን፤ ሶስተኛ እርግማን አለብኝ ብሎ ማመን በራሱ እርግማን ነው ። ምንም እንኳን አዳምን እግዚአብሔር ባይረግመውም ምድር ግን ከአዳም የተነሳ ተረገማለች። "እሾህና አሜኬላ ታበቅልብሃለች" ብሎታል። ኢየሱስ በተሰቀለ ጊዜ የእሾህ ጉንጉን ያደረጉለት ይህንን የምድርን እርግማን በመስቀል ላይ ተሸክሞ ያስወገደው ዘንድ ነው። የእግዚአብሔር ቃል እውነት ነው። የምድር እሾህ ማብቀል አሁን እኔን የእግዚአብሔርን ቃል እንዳላምን አያደርገኝም። ምክንያቱም የምናምነውን ቃል ነው እንጂ የምንኖረው ሁኔታን አይተን የእግዚአብሔርን ቃል አንፈታተነውም። ቃሉ የሚፈታው በእምነት ነው። የአዳም እርግማን በክርስቶስ ኢየሱስ መስቀል ላይ ተወግዷል።

ሁለተኛው እርግማን የሕግ እርግማን ነው። አንደኛ፣ ይህ እርግማን የሚሠራው ሕግ ለተሰጣቸው ለአይሁዶች ነው። ለአህዛብ አይሠራም ነገር ግን በሕግ ሥር ለሚመላለስ ሁልጊዜ ሕግ "እሺ ብትል ብትታዘዝ የምድርን በረከት ትበላለህ፤ ስትወጣ ብሩክ ነህ፤ ስትገባ ብሩክ ነህ፤ በእርሻ ብሩክ ነህ፤ በከተማ ብሩክ ነህ…እምቢ

ብትል ባትታዘዝ ደግሞ ሰይፍ ይበላሃል፣ እግዚአብሔር ከምድር ገጽ እስክትጠፋ ድረስ በንዳድ ያሳድድሃል፤ ሚስት ታጫለህ ሌላው ሄዶ ያገባብሃል፤ ሰማይ ናስ ይሆንብሃል፤ ምድር ብረት ትሆንብሃለች፤ አንተ ታርሳለህ ሌላው መጥቶ ያጭደዋል፤ አንተ ቤት ትሰራለህ ሌላው መጥቶ ይኖርበታል....” ብሎ ነው የሚናገረው። ኢየሱስ እርግማን ሆኖ አይሁድን ከዚህ ሕግ እርግማን ዋጅቷል። ስለዚህ አሁን አይሁድ የሕጉ እርግማን የለበትም።

ሶስተኛው እርግማን፣ እርግማን አለብኝ ብሎ ማመን ነው። ከዚህ የከፋ እርግማን የለም። ሰው ዳግም ተወልዶ አዲስ ፍጥረት ከሆነ በኋላ እርግማን አለብኝ ብሎ ካመነ ይህ እርግማን ነው። የአዳም እርግማን ባይከፈል እንኳን እኛን አሁን አይመለከተንም። ምክንያቱም እኛ አዳምን አናውቀውም፤ ሕይወትን የጀመርነው በክርስቶስ ነው። ከአዳም ተፋተን ከኢየሱስ ጋር ተጋብተናል። የእግዚአብሔር ልጅ እንጂ የተባልነው የአዳም ልጅ አይደለም። ጳውሎስ *“ከሰበክንላችሁ ወንጌል ውጪ ማንም ቢሰብክ እሱ የተረገመ ይሁን.... እኔ ራሱ እንኳን...”* ሲል ሲኦል ይግባ ማለቱ ነው። እርግማን አለብኝ ብሎ የሚያስብ ሰው ሁሉ እርግማን ለማሰበር ነው የሚዞረው። እርግማን እንደተሰበረልህ ግን እነግርሀለሁ።

## *ሰባቱ ክፍለ ዘመናት*

**1. የጨዋነት (የንጽህና ዘመን) - ከአዳም እስከ ውድቀት ያለው ዘመን ነው።** አዳም በነበረበት ዘመን ንፁህ ወይም ኃጢአትን ያላደረገ ማንነት የነበረው። በዚህ ዘመን ላይ ተሰውሮ የተደረገውንም ገልጦ የማወቅ ጉልበት አለው። ምክንያቱም ምንም አይነት ኃጢአት በሰው ውስጥ ስለሌለ።

ለምሳሌ እግዚያብሔር በአዳም ላይ ከባድ እንቅልፍ ተጥሎበት ሔዋንን ሰርቶ ወደ አዳም አመጣት። ባያት ጊዜም *“ይቺ አጥንት ከአጥንቴ ስጋዋም ከስጋዬ ነውና ሴት ትባል”* ብሎ ነው የወሰዳት። በሌላ አአነጋገር ያልወደቀ መንፈስ ወደ ኋላ መለስ አድርጎ የማወቅ ጉልበት ነበረው ማለት ነው።የእግዚአብሔር ባህሪ በእርሱ ስለነበር። ምንም አይነት ኃጢአት እና ኩነኔ የሌለበት እግዚአብሔር የሰጠውን ብቻ የሚኖር ስብዕና ነው የነበረው።

**2. የህሊና ዘመን - ልክ አዳም ፍሬዋን ከበላ ጊዜ አንስቶ እስከ ኖህ ዘመን ድረስ ያለው ዘመን ነው።** ስለ ህሊና ሁለት ዓይነት አመለካከት አለ። ህሊና ምንድናት? ወይም ከየት መጣች? ብለው ብዙ ሰዎች ይጠይቃሉ። ህሊና የአንድን ነገር እውነታ

ወይም ሀቅ አለመካድ ነው። አንዳንዶች *"ህሊና ተፈጥራ ቆይታ ልክ አዳም ኃጢአትን ሲያደርግ ያኔ ነው የነቃችው"* ይላሉ። ሌሎች ደግሞ *"ህሊና የተፈጠረችው ልክ አዳም ፍሬዋን በበላ ጊዜ ነው።"* ብለው ያምናሉ። ለጊዜው ሁለቱንም ብንወስደው ችግር የለውም። ነገር ግን እኔ ማምነው ፍሬው ነው ህሊና ሆኖ እኛ ውስጥ የገባው ብዬ ነው።

ምክንያቱም ከዛ በፊት ህሊና ኖሮ ሳይነቃ እንዲተኛ ብሎ እግዚአብሔር የፈጠረው ፍጥረት የለም። ነገር ግን ህሊና ልክ አዳም ፍሬውን በበላ ጊዜ የተፈጠረች ናት። ምክንያቱም አዳም እና ሄዋን ራቁታቸውን ሆነው ለረጅም ጊዜ ሳይተፋፈሩ ኖረዋል። ነገር ግን ራቁታቸውን እንኳን እንደሆኑ አያውቁም ነበር፤ ህሊና ካለ፣ ህሊና የአንድን ነገር እውነታ ወይም ሀቅ አለመካድ ወይም ማወቅ ከሆነ ራቁታቸውን ሆነው ካለወቁ ህሊና የለም ማለት ነው። ልክ ፍሬውን በበሉ ጊዜ ያኔ ራቁታቸውን እንደሆኑ አወቁ። ራቁትነታቸውን ያወቁት ያንን ፍሬ በበሉ ጊዜ ነው።እግዚአብሔር መጥቶ፣ አዳም ሆይ ወዴት ነህ? ባለው ጊዜ ራቁቴን ስለሆንኩ ተሸሸግሁ ወይም ፈርቼ ተደበቅሁ ነበር ያለው። ነገር ግን እግዚአብሔር ራቁትህን እንደሆንክ ማን ነገረህ? ብሎ ጠየቀው።

እግዚአብሔር በማንነቱ እርሱ ከፈጠረህ እና ካስቀመጠህ ስፍራ ጎድለህ ስትገኝ ማን ነገረህ ነው የሚለው። እግዚአብሔር ሲፈጥረው ራቆቱን ነው ብሎ አይደለም የፈጠረው። ለእግዚአብሔር ለብሶ ነው የነበረው፤ አዳምም ራቁቱን ሆኖ አያፍርም ነበር። ይህ ማለት ሰውየው በዚህ ሥጋ ውስጥ እየኖረ ሥጋውን እንደ ልብስ የሚጠቀም ሰው ነበር። ፍሬውን ሲበላ መንፈሱ ሲሞት ነው ከውስጥ ወደ ነፍስ አቅም እና ጉልበት ውስጥ ገብቶ በነፍሱ ማየት ሲጀምር የሁለቱም አይኖች ተከፈቱ ራቆታቸውን እንደሆኑ አወቁ። ራቁታቸውን እንደሆኑ ያወቁት አይናቸው ተከፍቶ ነው። ይሔ የውጭው አይን ማለት አይደለም ምክንያቱም በፊትም ያዩ ነበር ነገር ግን ውስጥ ሌላ አይን ተከፍቶ መመልከት ጀመሩ። የነፍሳቸው አይን በመከፈቱ ራቁታቸውን እንደሆኑ አውቀዋል።

አንዳንድ ሰው ሲፀልይ "ጌታ ሆይ እኔ የማልረባ የማልጠቅም ነኝ" ይላል። እናም እግዚአብሔር በተመሳሳይ መልኩ መጥቶ "ማን ነገረህ?" ይለዋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር የማይረባ ፍጥረት የለውም። ለማይረባ ፍጥረት ራሱን መስዋዕት አድርጎ አልሰጠም። አንተ ማለት በእግዚአብሔር ፊት ፍፁም እንደ ክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆንክ ነህ። አዲስ ፍጥረት ደግሞ የማይረባ ሳይሆን በተፈጥሮው ከማይጠፋ ዘር የተወለደ ነው። ለዚህ ምድር እና ለዚህ ለፍጥረታዊው አካል እንግዳ የሆነ እና

ከላይ የወረደ ማለት ነው። ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ *“ከላይ ከወረደው በስተቀር ወደ ላይ የሚወጣ የለም።”* ስንት ሰው እንደሚነጠቅ ያምናል? ወደ ላይ እንደምትሔድ ካመንክ ከላይ ነው የመጣኸው ማለት ነው። በመጨረሻው ዘመን ጌታ ኢየሱስ ወደዚህ ምድር ሲመጣ፣ እኛ ህያዋን የሆንን በአየር ለመቀበል በደመና እንነጠቃለን።

**3. የሰው አገዛዝ ዘመን - ከኖህ እስከ አብርሃም ድረስ ያለው ዘመን ነው።** በዚህ ክፍለ ዘመን ላይ ሰዎች የወደዱትን እና የፈቀዱትን ወይም የራሳቸውን ነገር የሚያደርጉበት ነበር። ይህንንም ስናይ ከጥፋት ውሀ ከተረፉት ስምንት ሰዎች በኋላ እየተባዙ መጥተው *“ኑ ለስማችን ማስጠሪያ ግንብን እንገንባ”* ብለው ዘፍጥረት ምዕራፍ 11 ላይ መገንባት ሲጀምሩ እናያለን። እግዚአብሔር መጥቶ ያፈረሰባቸው እነዚህ ሰዎች በዚህ ከቀጠሉ እኛ ጋር ይደርሳሉ ብሎ ነው። ሀሳባቸው አንድ ከሆነ ያሰቡትን ከማድረግ አይከለከሉም።

«ስለዚህ ኑ እንውረድ እና ቋንቋቸውን እንደባልቅ»። ለምን እግዚአብሔር? እኔን ምሰሉ፤ ወደ እኔ ኑ፤ ወደ እኔ ቅረቡ የሚል አምላክ ወደሱ መቅረባቸውን ጠልቶት ነው? አይደለም! እግዚአብሔር ወደ እሱ እንድንቀርብ ጠልቶ ሳይሆን እግዚአብሔር ወደ እርሱ በራሳችን እንድንቀርብ ስለማይፈልግ ነው። ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ካለብህ በክርስቶስ ነው። በሰው አገዛዝ ዘመን ላይ ያሉ ሰዎች የሠሩት ለራሳቸው ስም ማስጠሪያ ነው። በራሳቸው አቅም እና ጉልበት ነው እንገንባ ያሉት ዘፍጥረት ምዕራፍ 11 ላይ እግዚአብሔር ወርዶ ቋንቋቸውን ደበላለቀ፤ እርስ በእርሳቸው አለመግባባት ሆነ፣ በዚህም ምክንያት ተበተኑ።

**4. የተስፋ (የቃል ኪዳን) ዘመን - ከአብርሃም እስከ ሙሴ ያለው ዘመን ነው።** እዛው ዘፍጥረት ምዕራፍ 11 መጨረሻ ላይ እግዚአብሔር ወደ አብርሃም ይመጣል። ምዕራፍ 12 ጀምሮ አንድ አዲስን ዘር ይመርጣል። ይህ ዘመን ተስፋ የተነገረለት ዘር ወይም ደግሞ ተስፋ የተነገረለት አካል ገና የጀመረበት ሰዓት ነው። *“አብርሃም አንድ ብቻውን ሳለ ጠራሁት፣ ባረኩት አበዛሁትም”* አይደል ያለው። እግዚአብሔር ብቻህን ጠርቶህ መባረክ እና ማብዛት የሚችል ድንቅ አምላክ ነው። ስለዚህ በአብርሃም እና በዘሩ ውስጥ ተስፋ ተነገረ። *“በዘርህ አህዛብ ሁሉ ይባረካሉ። ስምህን ገናና አደርገዋለሁ። የሚረግሙህን እረግማለሁ። የሚባርኩህን እባርካለሁ”* ብሎ በአብርሃም ውስጥ ሌላ ዘር አየ። ያየው ዘር የተስፋ ቃል ዘር ነው። በእስማኤል ዘር እንደማይጠራ አብርሃምም ጠንቅቆ ያውቃል። *“በይስሀቅ ዘር ይጠራልሃል”* የሚል የተስፋ ቃል ስለያዘ ይስሀቅን ለመሰዋት እንኳን እርግጠኛ ነበር።

**5. የሕግ ዘመን - ከሙሴ እስከ ኢየሱስ ሞት እና ትንሳኤ ድረስ የሕግ ዘመን ነው።**
በሕግ ዘመን ላይ ሕግ የሚባል ነገር የጀመረው ዘጸአት 20 ላይ ነው አንድሆነ ብዙዎቻችን የምናስበው። ምንም እንኳን ሕግ በዚህ ምዕራፍ ላይ ቢሰጥም ኪዳኑ በትክክል ኪዳን ሆኖ የጀመረው ዘጸአት 24 ላይ ነው። በዚህ ምዕራፍ ላይ የእስራኤል ህዝብ በሙሉ ሕጉ ተነበበላቸው ሲጨርሱ *"እግዚአብሔር ያለንን በሙሉ እንፈጽማለን በማለት በተነበበው ሕግ ተስማሙ ከእግዚአብሔር ጋር "እንፈጽማለን"* በማለት የእስራኤል ህዝብ ቃል ገባ።

ስለዚህ ሙሴ በሂሶጵ በእነሱ እና በመጽሐፉ ላይ ደም ረጨ። አስተውሉ ሙሴ መጽሐፉን እንጂ እግዚአብሔርን አልረጨም። ስለዚህ ኪዳን የገቡት ከመጽሐፉ ጋር እንጂ ከእግዚአብሔር ጋር አይደለም። ስለዚህ ኪዳኑ እናደርጋለን የሚል ነው። በሌላ አገላለፅ ባያደርጉ ሊያመጣባቸው የሚችለውን እርግማን ችግር እንስማማለን ባናደርግ እርግማኑ ይምጣ ነገር ግን እናደርጋለን በሚል ሕግ እዚህ ጋር ነው የተጀመረው። ሙሴ ጽላቱን ይዞ በመጣ ቀን እንኳን እነሱ ጣኦት ሰርተው ሌላ አምላክ ሲያመልኩ ነው ያገኛቸው። ሙሴም ጽላቱን ወረወረው እሳቱ ነደደ። በዚያን ቀን 3000 ሰው ሞተ።

በጣም በሚደንቅ ሁኔታ ከዚህ በፊት አንድም ሰው ሲሞት አታዩም። በተለይ ደግሞ እግዚአብሔር ከግብፅ ነፃ ካወጣቸው እና በበግ ደም ቀድሶ ከለያቸው በኋላ ሕግ እስከተሰጠበት ጊዜ ድረስ አንድም ሰው አልሞተም ግን ሲያጉረመርሙ እና ሲሳደቡ ነበር። ምክንያቱም ሕግ በሌለበት ኃጢአት አይቆጠርም ነበር። እግዚአብሔር በጸጋ ነው ያኖራቸው። ዘጸአት 12 ላይ የበጉን ቅልጥም በልተው ነው የወጡት። በጉ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። አርባ ዓመት ሙሉ እየኖሩ ያልሞቱት የበሉት በግ ያመጣው መለኮታዊ ጤንነት እንጂ የእነሱ አቅም እና ብርታት አይደለም። ምንም ኃጢአት ስላልሰሩ ሳይሆን የበሉት ክርስቶስ እግራቸው ሳያብጥ ልብሳቸው ሳያልቅ ማኖር ችሏል።

የበላኸው ኢየሱስ ዘላለም የሚያኖር ነው። *"ከእኔ የበላ ለዘላለም አይራብም"* የሚያጠግብ እንጀራ ከምጣዱ እንደሚታወቅ *"ከሰማይ የወረደ እንጀራ እኔ ነኝ"* ብሎ ኢየሱስ ራሱን አቅርቧል። እሱን የበላ ሰው ለዘላለም መኖሩ የተረጋገጠ ነው። ልክ ሕጉ የተሰጠ ቀን ሶስት ሺ ሰው ነው የሞተው፤ ሰው በሕግ እኖራለሁ ካለ አንደኛ ስለ ሕጉ መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን፣ በተለይ በ2ኛ ቆሮንቶስ ጳውሎስ 3 ራሱ ሲያብራራልን *"ፊደል ይገድላል፤ መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል"* አለ። ብዙ ሰው ቲዮሎጂ መማር የሚገድል ይመስለዋል። ጳውሎስ ፊደል ያለው ግን ሕጉን ነው።

ምክንያቱም ከዚህ በፊት ሕጉ 3000 ሰው ገድሏል። መንፈስ ብሎ ያለን ደግሞ በሐዋርያት ስራ 2 ላይ መንፈስ ቅዱስ በወረደበት ቀን ጴጥሮስ ቆሞ ሰበከ፤ 3000 ሰው ዳነ። በህጉ ወይንስ በጸጋ በየትገኛው መኖር ትፈለጋለህ? ።

መጽሐፍንም ስንፈታ በሕጉ ለሚመላለስ ሰው ፍርድ አለበት፤ ኩነኔ አለበት፤ እርግማን አለበት። በክርስቶስ ለሚመላለስ ሰው ደግሞ በረከት አለበት። በሙሴ ሳንሆን በኢየሱስ ነን።ሙሴ በቤቱ የታመነ ባሪያ ነው ልጅ ግን አይደለም። ኢየሱስ ግን ልጅ ነው ስለዚህ፣ በልጁ ነን ወይስ በባሪያው? በባሪያው ከሆንክ ርስት ወይም ውርስ የለህም። በልጁ ከሆንክ ግን የልጁ ሁሉ የአንተ ነው። ስለዚህ መጽሐፍትንም ስንፈታ ለልጁ ነው ወይስ ለባሪያው ነው የተነገረው ብለን ነው የምንፈታው። የዕብራውያን ጸሐፊ ሲነግረን ሙሴ በቤቱ እንደ ባሪያ የታመነ ነበር ብሎናል። ባሪያ አገልግሎ ሲጨርስ "አመሰግናለሁ" ይባላል እንጂ ምንም ርስት የለውም።

ባሪያ ልጆች የሚወልደው ለነጻነት ሳይሆን ለባርነት ብቻ ነው። የባሪያ ልጅ ጨዋ አይደለም፣ ባሪያ ነው። የባሪያን ልጅ ባሪያ ያደረገው ከባሪያ መወለዱ እንጂ ባሪያ መሆን ፈልጎ አይደለም። *"የዘመን ፍፃሜ በደረሰ ጊዜ እግዚአብሔር ልጁን ልኮ… ከሕግ በታች ያሉትን ይዋጅ ዘንድ"* ዋጅቶ ዝም ብሎ አይተውህም። *"አሁን ግን ሁላችን በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን የእግዚአብሔር ልጅ ሆነናል።"* ልጅ ከሆንክ ደግሞ የእግዚአብሔር የራሱ ወራሽ ነህ። ከእግዚአብሔር ትወርሳለህ ሳይሆን እራሱን ትወርሳለህ። ማንነቱን ባህሪውን ተፈጥሮውን ተካፍለህ አንተና እሱ እስከማትለያዩ ድረስ አንድ መንፈስ ሆናችኋል።

በዘጸአት 24 ላይ ኪዳኑ ሲገባ እናደርጋለን ስላሉ፣ ባለማድረጋቸው እርግማን ሲሆን በማድረጋቸው ደግሞ በረከት አለ። ዘዳግም ምዕራፍ 28 ላይ 1-15 ድረስ እሺ ብለህ ብትታዘዝ ብሎ ስለበረከት ይናገራል፤ ከ ቁጥር 16-63 አካባቢ ድረስ እርግማን ነው የሚያወራው። በረከቱ በቁጥር ትንሽ ነው፤ እርግማኑ ደግሞ ብዙ ነው። ግን እነሱ እናደርጋለን ነው ያሉት። ሁልጊዜ ሰው እኔ እችላለሁ ያለ ቀን የውድቀቱ መጀመሪያ ይሆናል። ብዙ ጊዜ ሰው "ገብቼ እጸልያለሁ" ይላል። በኋላ አንድ ሰአት ለመጸለይ አሁን 5 ደቂቃ ጀምር። አሁን ያልጀመርከውን በኋላ አንድ ሰአት አትችልም።

የሕግ ዘመን ሰዎች በራሳቸው ጥረት እና አቅም ላይ ማዕከል ያደረጉበት፤ እግዚአብሔርም ከእነርሱ ጋር ሲነጋገር ማዕከል ያደርግ የነበረው የእነሱ መታዘዝ ላይ ነበር። ይህ ጌታ ኢየሱስ እስኪመጣ ድረስ ብቻ ነበር። እሱ ሲመጣ ተፈፀመ ብሎ ዘግቶታል። ከዛ በኋላ አዲስ ኪዳን ሆነ። ይህ ኪዳን የጀመረው በደም እንጂ

በመጽሐፍ ቅዱሳችን ብሉይ ኪዳን መጨረሻ ላይ ባለው ነጭ ወረቀት አይደለም። ክርስቶስ ከሞት ሲነሳ ባስገባው የኪዳኑ ደም ነው። *"ደም ሳይፈስ ስርየት የለም"* አሮጌውም ኪዳን አዲሱም ኪዳን በደም ነው የተመረቀው። ጌታ ኢየሱስ የመጨረሻውን የፋሲካ ራት በሰጣቸው ጊዜ *"ይህ ስለእናንተ የኃጢአት ይቅርታ የሚፈስ የአዲስ ኪዳን ደሜ ነው"* ሲል የዛች ሰዓት እራሱ አዲስ ኪዳን አልጀመረም ምክንያቱም ገና ደሙ አልፈሰሰም ነበር።ከሞት ከተነሳ ቡሀላ እንኳን ማሪያም ልተነካው ስትል «እንዳትነኪኝ»ሲላት እንመለከታለን። ምክንያቱም *ሥራው* ገና አልተጠናቀቀም ነበርና። ያንን ደም ማስገባት ነበረበት። ያን ደም ካስገባ በኋላ ነው *ሥራው* ሲጠናቀቅ ኑ ዳሱኝ እና ንኩኝ ማለት የቻለው። ስለዚህ አዲሱ ኪዳን የጀመረው እዚህ ቦታ ነው ብለን መጥቀስ ባንችልም፣ በእርግጠኝነት የምንናገረው በመስቀሉ ሞት፣ ትንሳኤ እና እርገት ነው። ሞቱ የአሮጌው ኪዳን ማጠናቀቂያ እና የአዲሱ ኪዳን መጀመሪያ ነው። የኢዲሱ ኪዳን ጅማሬ ደግሞ የተጠናቀቀው ሲያርግ እና በአብ ቀኝ ሲቀመጥ ነው ነገር ሁሉ የተፈጸመው።

የአዲስ ኪዳን አገልግሎት ካልሆነው የኢየሱስ አገልግሎት አንዱን ላሳያችሁ፡- ብዙዎቻችን ጌታ ኢየሱስ በሥጋ ሲመላለስ የአዲስ ኪዳን አገልጋይ ነው የሚመስለን ነገር ግን ኢየሱስ ክርስቶስ በአራቱ ወንጌላት እና በብሉይ ኪዳን ደግሞ ከመስቀል በኋላ ባለው በአዲስ ኪዳን ውስጥ፣ የኢየሱስ ክርስቶስን ጉዞ ዘግበውልናል። አራቱ ወንጌሎች ወንጌል አይደሉም፤ ወንጌል ማለት የምስራች ወይንም መልካም ዜና ማለት ነው። ስለዚህ ለአይሁድም ሆነ ለአህዛብ የምስራቹ ክርስቶስ ኢየሱስ የኃጢአትን ዕዳ ከፍሎላችኋል የሚለው እንጂ ተወልዷል ብለን አጨብጭበን ሳይሞት ቢሄድ ምንም ጥቅም አልነበረውም ።ስለዚህ ለሰው ሁሉ በረከት የሆነው በመስቀል እዳችንን ሲከፍል እንጂ ።

በሥጋው ወራት ሲመላለስ፣ አንድ ሰራብታዊት ሴት "ልጄን ፈውስልኝ" እያለች ከኋላው እየተከተለች ትጨቀጭቀው ነበር። *"እኔ ከእስራኤል ቤት ለጠፉት ለልጆች ነው እንጂ የመጣሁት ለእናንተ አይደለም"* አላት ። ደቀመዛሙርቱም "እባክህ ለዚህች ሴት እዘንላት" አሉት። እሱም *"የልጆችን እንጀራ ለቡችሎች መስጠት አይገባም"* ሲላት ምን እየተናገረ እንደሆነ በደንብ ጠንቅቃ ስለምታውቅ፣ *"እኔን ቡችላ፣ የማን ልጅ እንደሆንኩ አታውቅም።"* አላለችም። *"ቡችሎችም እኮ የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ"* አለችው። ወዲያው ይህን ስትል ኢየሱስ *"እንዲህ ያለ እምነት በእስራኤል እንኳ አላገኘሁም"* አለ። በእስራኤል ከዛ በፊት ብዙ ተዓምራት አድርጓል

ነገር ግን እንደዚች ሴት አይነት እምነት ግን አላየም። በዚህች ሴት እና በእስራኤላውያን መካከል ያለው ልዩነት ምንድንነው?

ኢየሱስ በ4ቱ ወንጌላት ብዙ ድንቅና ተዓምራትን አድርጎ ነበር ነገር ግን ወንድሞቹ እንኳን አላመኑበትም ነበር። በሰዎች ዘንድ ተቀባይነት ለማግኘት ብዙ ተግዳሮት ነበረበት። ባለማመናቸው እንኳን ብዙ ተዓምራት ማድረግ አልቻለም። ይህቺ ሴት አይሁዳዊ አይደለችም፣ የሙሴ ሕግም የላትም። እስራኤል በሙሉ ግን የሙሴ ሕግ አለው ስለዚህ ሰርቶ ነው እንጂ መባረክን የሚያስበው መሲሁ በሚያመጣው በረከት አያምንም። በሰንበት እንኳን ከፈወሰ *"ይሔ ሰው ኃጢአተኛ ነው"* ብለው ነው ሚያጠቃልሉት። ይህቺ ሴት ግን የሙሴ ሕግ የላትም የሰማችው የምታውቀው ኢየሱስን ብቻ ነው። ኢየሱስን ብቻ የሰማ ሰው እምነቱ ታላቅ ይሆናል። ነገር ግን በኢየሱስ ላይ ሙሴን ደምሮ የሰማ ሰው እምነቱ በጣም ደካማ ነው።

*ወንጌል የሚባለው ነገር በሙላት የተገለጠው በጳውሎስ ነው። ጳውሎስ ወንጌላቸው ብሎ ሳይሆን ወንጌሌ ብሎ ነው የሚጀመረው። የነ ማቴዎስ ወንጌል ብሎ አልጀመረም። እኔ ከሰማይ ከራሱ ከኢየሱስ የተቀበልኩት ነው ብሎ በመገለጥ የተቀበለውን ወንጌል ሰበከ። በክርስቶስ ኢየሱስ የተሠራውን ምስጢር ያስተላለፈልን ሰው ጳውሎስ ይባላል። ኢየሱስ በምድር ቆይታው ማጠቃለያ ላይ ለደቀመዛሙርቱ ብዙ ነገር ምነግራችሁነበረኘ ነገር ግን ልትሸከሙት አትችሉም አላቸው።*

*ታዲያ እነዚህ አራቱ ወንጌላት ወንጌል ካልሆኑ እንዴት ነው መፍታት ያለብን? እነዚህ አራቱ ወንጌላት የመንግስቱ ወንጌል ይባላሉ። መጥምቁ ዮሐንስም ሆነ ኢየሱስ የሰበኩት የእግዚአብሔር መንግስት ቀርባለችና ንስሃ ግቡ ብለው እንጂ የእግዚአብሔር ምንግስት ተመስርታለች የሚል ስብከት አይደለም። ምክንያቱም የመንግስቱ ገዢ የሆነው ኢየሱስ ምድር ላይ ስላለ ነው። መንግስቱ የምትመሰረተው በኢየሱስ ነው ደግሞም በመንፈስ ቅዱስ ነው። ስለዚህ አንድን ቃል ስንፈታ በሶስት መንገድ ነው የምንፈታው። ከብሉይ ኪዳን አንፃር፣ ከአዲስ ኪዳን አንጻር እና ከመንግስቱ ወንጌል አንጻር መልእክቱ እንዴት ይታያል? በሚል ነው። ሕግና ነቢያት እስከ ሀንስ እንደሆነ ተናግሯልና።*

**6. የጸጋ ዘመን - ከኢየሱስ ትንሳኤ በኋላ ያለው ዘመን (አሁን እኛ እየኖርንበት ያለው ዘመን) ወይም ከመስቀል በኋላ ያለው ዘመን ነው።** የጸጋ ዘመን የሰው እጅ የሌለበት፣ ክርስቶስ ኢየሱስ ብቻውን የሠራው እና የፈጸመው እኛ ደግሞ በእርሱ ቸር ስጦታ ልጅ ወይም አዲስ ፍጥረት የሆንንበት የእግዚአብሔር ስጦታ ያለበት ነው።

7. የሺው አመት መንግስት - ኢየሱስ ክርስቶስ ሲመጣ የሺው አመት መንግስት ይጀምራል።

## *አንድን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል ስናጠና መጠየቅ ያለብን አምስት ነገሮች*

- ማን ተናገው?
- ለማን ተናገረ?
- ስለምን ተናገረ?
- መቼ ተናገረ (ከመስቀል በፊት ወይስ በኋላ)?
- በመስቀሉ ሥራ (በክርስቶስ ኢየሱስ ስራ) ሲታይ መልዕክቱ ምን ይመስላል?

ለዚህ መነሻ ሃሳብ እንዲሆነን ማቴዎስ 19 ከ16 ጀምሮ እንይ

> *"እነሆም፥ አንድ ሰው ቀርቦ። መምህር ሆይ፥ የዘላለምን ሕይወት እንዳገኝ ምን መልካም ነገር ላድርግ? አለው።"*

አንድ ሰው ቀርቦ እናንተን ይህንን ጥያቄ ቢጠይቃችሁ ምን ትሉታላችሁ? በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ነው አይደል የምትሉት? እሺ፣ በዚህ ታሪክ መሰረት ተናጋሪው አንድ ሰው ነው፤ እየተናገረ ያለው ደግሞ ለኢየሱስ ነው። መልዕክቱ ደግሞ ስለ ዘላለም ሕይወት ነው።መቼ ነው ለሚለው ደግሞ ከመስቀል በፊት ነው።

> *"እርሱም። ስለ መልካም ነገር ለምን ትጠይቀኛለህ? መልካም የሆነ አንድ ነው፤ ወደ ሕይወት መግባት ብትወድ ግን ትእዛዛትን ጠብቅ አለው።" ቁ.17*

አሁን በኢየሱስ እና በእናንተ መካከል ትልቅ ግጭት አለ። እናንተ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን ነው የምትሉት። ታዲያ ጌታ ኢየሱስ "በእኔ እመን" ነው ማለት ያለበት ወይስ ትዕዛዛቱን ጠብቅ ነው ማለት ያለበት? በእሱ የሚያምን የዘላለም ሕይወት አለው" ስለዚህ እመን ማለት ይችል ነበር። ነገር ግን ሰውየው ይዞ የመጣው ጥያቄ በራሱ ችግር አለበት። ከዚህ ሰውዬ አንድ የምንረዳው ነገር አለ። ሰውየው ኢየሱስን ቸር

መምህር ሆይ ነው ያለው። ኢየሱስ ቸር መምህር እንደሆነ ጥያቄ የለውም ነገር ግን ኢየሱስ "ለምን ቸር ትለኛለህ ቸር አንድ ነው" ብሎ ነው የመለሰለት። ሰውየው ኢየሱስን ቸር መምህር ሆይ ያለው ከሌሎች የአይሁድ መምህራን ጋር አወዳድሮ ነው። ሰውየው ሲመጣ ራሱ በሥራ የሚያምን ነው። በሥራ ለሚያምን ኢየሱስ ሲመልስ ስራ ብሎ ነው። ምክንያቱም የሰውየው ጥያቄ እራሱ ምን ልሥራ ነው እንጂ ምን ትመክረኛለህ የሚል አይደለም። ስለዚህ ኢየሱስም *"ትዕዛዞቹን ጠብቅ"* ብሎ መለሰለት።

> *"እርሱም። የትኞችን? አለው። ኢየሱስም። አትግደል፣ አታመንዝር፣ አትስረቅ፣ በሐሰት አትመስክር፣ አባትህንና እናትህን አክብር፣ ባልንጀራህንም እንደ ራስህ ውደድ አለው። ጕበዙም። ይህንማ ሁሉ ከሕፃንነቴ ጀምሬ ጠብቄአለሁ፣ ደግሞስ የሚጐድለኝ ምንድር ነው? አለው። ኢየሱስም ፍጹም ልትሆን ብትወድ፣ ሂድና ያለህን ሸጠህ ለድሆች ስጥ፣ መዝገብም በሰማያት ታገኛለህ፣ መጥተህም ተከተለኝ አለው።" ቁ. 18 - 21*

እነዚህ ሕግጋቶች የተጻፉት የሙሴ ኪዳን ላይ ነው። ኢየሱስ ጸጋ ነው፤ ኢየሱስ ራሱ ሕይወት ነው። ታዲያ እንዴት ሙሴን ይሰብካል? ሰው እንዲጠፋ ይፈልጋል ማለት ነው ኢየሱስ? አይደለም። ሰውየው በሥራ አምኖ ስለመጣ በሥራ ዘመን ላይ ሥራ ነው የሚሰበከው። ሰውየው ግን የፈለገው ሌላ ሥራ እንጂ እነዚህን አይደለም፤ *"እነዚህን ሕጎች ከልጅነቴ ጀምሮ ስፈጽም ነበር"* በማለቱ ሰውየው አይሁዳዊ መሆኑን እንረዳለን። አይሁድ ካልሆነ በስተቀር ከልጅነቱ ጀምሮ እነዚህን ሕግጋቶች ሊፈጽም አይችልም። ኢየሱስ ያለውን ሸጦ ለድሃ መስጠት እንደማያጸድቅ ያውቃል ነገር ግን ሆን ብሎ አዘዘው።

> *"ጕበዙም ይህን ቃል በሰማ ጊዜ ብዙ ንብረት ነበረውና እያዘነ ሄደ። ኢየሱስም ለደቀ መዛሙርቱ። እውነት እላችኋለሁ፣ ለባለጠጋ ወደ መንግሥተ ሰማያት መግባት ጭንቅ ነው። ዳግመኛም እላችኋለሁ፣ ባለጠጋ ወደ እግዚአብሔር መንግሥት ከሚገባ ግመል በመርፌ ቀዳዳ ቢገባ ይቀላል አለ። ደቀ መዛሙርቱም ሰምተው እጅግ ተገረሙና። እንኪያስ ማን ሊድን ይችላል? አሉ። ኢየሱስም እነርሱን ተመልክቶ። ይህ በሰው ዘንድ አይቻልም በእግዚአብሔር ዘንድ ግን ሁሉ ይቻላል አላቸው።" ቁ. 22-26*

ሕጉ "እሺ ብትል ብትታዘዝ የምድርን በረከት ትበላለህ" ስለሚል አንድ አይሁዳዊ ሀብታም ሆኖ ከተገኘ ሕጉን ፈጽሟል ብለው ያምናሉ። ስለዚህ ደቀመዛሙርቱ ውስጥ ያለው መረዳት ይህ ስለሆነ ነው ሀብታም ካልዳነ ማን ሊድን ይችላል ብለው

የጠየቁት። ከትዕዛዛት የመጀመሪያው ሕግ *"ጌታ አምላክህን በፍጹም ልብህ፣ በፍፁም ነፍስህ፣ በፍፁም ሀሳብህ፣ በፍፁም ኃይልህ ውደድ"* የሚል ነው። ስለዚህ ሰውየው ያጎደለው ትዕዛዝ የመጀመሪያውን ነው። ያለህን ሸጥ ሲለው ከእግዚአብሔር ይልቅ ማንን እንደሚወድ እያጣራ ነው።እግዚአብሔር ፊት ጨርሻለሁ ሁሉንም ይኸው ጌታሆይ መልካም ሰርቻለሁ ብለህ ተሸክመህ ስትመጣ አንድ የጎደለህን ያሳይሃል። እዚህኛው ዘመን ላይ ሁሉን ልክ ሆነህ አንዷን ብታጎድል በሁሉ በደለኛ ነህ። ያዕቆብ ሲነግረን ከሕግ በአንዲቷን የሚያጎድል በሁሉ በደለኛ ነው። አዲሱ ኪዳን ላይ ደግሞ ሁሉን አጉድለህ አንድ ኢየሱስን ትክክል ብትሆን በሁሉ ጻድቅ ነህ።

እናም ይህንን ሰውዬ አንዷን ስላጎደለ ኢየሱስ ዜሮ ሰጥቶ ሸኘው። ለዚህ ነው መጽሐፍ ቅዱስ ሲናገር ከሞተ *ሥራ* ንስሀ እና በእግዚአብሔር ማመን እንዳለብህ ነው እሚናገረው። በእግዚአብሔር ፊት አንዳቸውም ያንተ *ሥራ* አይጠቅሙህም። ኢየሱስ ብቻውን ላንተ በቂ ነው። በኢየሱስ *ሥራ* ላይ የእኛን *ሥራ* አንድ ነገር የደመርን እለት ሁሉ ነገር ያበቃል። አንዳንድ ሰው እንዲህ ይላል፣ "ጌታ ሆይ እኔ ከጠዋት እስከ ማታ ስለፋልህ.... እኔ እኮ ለጌታ ብዬ.... ለወንጌል ብዬ..." ይላል። እግዚአብሔር ፊት ግን ዜሮ ነው። ኢየሱስ ብቻውን በቂ ነው።

ይህ ሰው የጠየቀውን አይነት ጥያቄ ሐዋርያት ስራ 16 ላይ ታገኛላችሁ። ጳውሎስ እና ሲላስ በእስር ቤት ታስረው ሳሉ የወህኒው መሰረት ተናወጠ። በዚያች ምሽት ላይ እስር ቤቱ ፈረሰ እና እነሱም ከእስር ወጡ። የእስር ቤቱ ዘበኛ ወደ እነሱ መጥቶ *"ጌቶች ሆይ እድን ዘንድ ምን ላድርግ?"* ብሎ ጠየቃቸው። ጳውሎስ "በሕግ የተጻፈውን እንዴት ታነበዋለህ?" አላለውም። ያለው *"በጌታ በኢየሱስ ክርስቶስ እመን፣ አንተና ቤተሰቦችህም ትድናላችሁ"* ልዩነቱ የማቴዎስ ወንጌሉ ከመስቀል በፊት ነው፤ የሐዋርያት *ሥራው* ደግሞ ከመስቀል በኋላ ነው። ከመስቀል በፊት ኢየሱስ የተናገረው ከመስቀል በኋላ አልሠራም። የመጀመሪያው የኢየሱስ ክርስቶስ ስብከት ለእኛ እንዲሠራልን ያንን ሰው መሆን ግድ ይለናል። ሁለተኛ አንድን ሀሳብ ከመጽሐፍ ቅዱስ ስናወጣ በብሉይ ኪዳን ምን ይመስላል፣ ከመስቀል በኋላ በአዲስ ኪዳን ምን ይመስላል፣ በመንግስቱ ወንጌል ምን ይመስላል በሚል በሶስቱም መፍታት አለብን።

የመንግስቱ ወንጌል የአዲስ ኪዳን እና የብሉይ ኪዳን መሸጋገሪያ (ድልድይ) ነው። በመንግስቱ ወንጌል ኢየሱስ ክርስቶስ ሲሰብክ እና ሲያስተምር ካገኛችሁት ቁጥር 2 ሙሴ ይሆንባችኋል። ከማቴዎስ 5 - 7 ቁጥር 2 ሙሴ ነው። ፈፅሞ የአዲስ ኪዳን ትምህርት አይደለም። በብሉይ ኪዳን፣ ልጅ ለመሆን የአብርሃም ኪዳን ተካፋይ

መሆን አለበት። ስለዚህ በመገረዝ ነው የኪዳኑ ተካፋይ የሚኮነው። በመንግስቱ ወንጌል ደግሞ፣ “የሚያስተራርቁ ብፁአን ናቸው የእግዚአብሔር ልጆች ይባላሉና።” ስለዚህ በመንግስቱ ወንጌል ልጅነት በማስታረቅ ነው።ከመስቀል በኋላ ወደ አዲስ ኪዳን ስንመጣ ደግሞ *“የእግዚአብሔር ልጅ ተብለን እንድንጠራ አብ እንዴት ያለውን ፍቅር እንዳፈሰሰልን እዩ እንዲሁም ነን”።* እንደውም ምን እንደምንመስል ገና አልተገለጠም ሲገለጥ ግን ቁርጥ እርሱን እንደምንመስል እናውቃለን። ስለዚህ መጽሐፍትን ስንፈታ በኪዳኑ፣ በአውዱ እንደመልዕክቱ ነው መፍታት ያለብን።

ለምሳሌ በገላትያ 3፡14 ከሕግ እርግማን ዋጀን ተብሎ ሲነበብ ቤተክርስቲያን አሜን ትላለች። ነገር ግን ቤተክርስቲያን የሙሴ ሕግ አልተሰጣትም፤ የሙሴ ሕግ በሌለበት የሕጉ እርግማንም የለም። ይህንን አሜን ማለት ያለባቸው ጳውሎስና ከአይሁድ የዳኑ አማኞች ናቸው።ምክንያቱም በሕግ እርግማን ሥር ስለነበሩ፤ ጌታ ኢየሱስ መጥቶ ስለዋጃቸው ይህ መልእክት ለእነሱ ነው።

**የኃጢአት ይቅርታን በተመለከተ፣** በብሉይ ኪዳን በዓመት አንድ ጊዜ ይከናወን ነበር። በዘሌዋውያን 16 ላይ ዮምኪፑር የሚባል የስርየት ቀን አለ። ይህ ቀን እስራኤል በሙሉ በፆም የሚውልበት ቀን ነው። ነፍሰጡር፣ ገና የተወለደ ህፃን፣ እንስሳ እንኳን ቢሆን ምግብ የሚባል ነገር አይቀምሱም። የማይበሉበት ምክንያት በዚያን ቀን ሊቀካህኑ የእስራኤልን ህዝብ ወክሎ የህዝቡን ኃጠአት ለማስተሰረይ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የሚገባበት ቀን ነው። ሊቀካህኑ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን ሲገባ በመጀመሪያ ስለ ራሱ ኃጠኢት ቀጥሎ ስለ ህዝቡ ኃጠአት መስዋእት ያቀርባል። ሊቀካህኑ የኃጠኢት ችግር ካለበት እዛው ተቀስፎ ይሞታል፤ በሕይወት መውጣት አይችልም። ሁለተኛ፣ በዚያን ቀን ሊቀካህኑ ምግብ ሳይቀምስ በአግባቡ የሊቀካህን ልብስ ለብሶ ነው የሚገባው።ያን ጊዜ ህዝቡን ወክሎ ሲገባ በሰላም የሚወጣ ከሆነ ዝም ብሎ አይወጣም ከወጣ በኋላ ስራዎች አሉት። የሊቀካህን ሥራ፡-

1. በመጀመሪያ ሊቀካህን የሚወክለው እግዚአብሔርን ነው ሰውን አይደለም። እግዚአብሔርን ሲወክል በኃጢአተኛው ሰው ምትክ ሆኖ የሚመጣውን ማንኛውንም እንስሳ የሚመረምረው ሊቀካህኑ ነው። ካህን መርምሮ ያላፀደቀው ነገር በእግዚአብሔር ዘንድ በፍፁም ተቀባይነት የለውም። ካህኑ መስዋዕቱን ልክ ሲያይ፣ ካህኑ ሳይሆን የሚያየው፣ ካህኑን የወከለው እግዚአብሔር ነው። ካህኑ የሚመረምረው ኃጢአተኛውን ሰውዬ ሳይሆን ኃጢአተኛውን ወክሎ የመጣውን እንስሳ ነው። መስዋዕቱን አገላብጦ ሲያይ የእግዚአብሔር አይን በእሱ ውስጥ ሆኖ ነው የሚመረምረው።

2. መርምሮ ሲጨርስ እንከን አልባ ከሆነ፤ ከጥሎ የሊቀካህኑ ሥራ የሚሆነው በኃጢአት ጉዳይ ላይ እልባት መስጠት ነው። ካህኑ ያንን የመረመረውን እንስሳ መስዋዕት አድርጎ ያቀርብና ደሙን ይዞ ሲገባ አሁን እግዚአብሔርን ወክሎ አይገባም። ሰውን ወክሎ ወደ እግዚአብሔር ይገባል። መጀመሪያ መስዋዕቱ ሊሰዋ ሲል እግዚአብሔርን ወክሎ የሰውን መስዋዕት ይመረምራል። መስዋእቱን ካቀረበ በኋላ ግን ሰውን ይወክልና ያንን ደም ወደ እግዚአብሔር ይዞ ይገባል። ልክ መስዋዕቱ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት ካገኘ ይወጣና የመጨረሻ ሥራው መባረክ ነው።

3. እስራኤል እርግጠኛ የሚሆኑት አሮን ከመቅደስ ወጥቶ በረከትን ሲባርካቸው ነው። *"እግዚአብሔር ይባርክህ፣ ይቀድስህ፣ ፊቱንም ያብራልህ፣ ሰላሙንም ይስጥህ"* ልክ ይህ የበረከት ቃል ሲነገርበት እስራኤል አሜን ይልና በደስታ ይጨፍራል። ሀጋግ የሚባል ዳንስ አላቸው እጅ ለእጅ ተያይዘው የሚጨፍሩት ጭፈራ ነው። ምክንያቱም እስራኤል የሚያውቀው አንድ እውቀት አለ እስከ ሚቀጥለው ዓመት ዩምኪፑር ድረስ በኃጢአት ጉዳይ ላይቀጣን እግዚአብሔር ፈርሞልናል። ምድር የሚገባንን ሰብል ልትሰጠን እና ጠላት መጥቶ ላይወስደን እግዚአብሔር ፈርሞልናል። በኃጢአታችን ጉዳይ ላንጠየቅ እግዚአብሔር ለአንድ አመት ዋስትና ገብቶልናል። በሚል እውቀት ታላቅ ደስታ እና ፈንጥዝያ ይሆናል።

ይህ እንግዲህ የአዲሱ ኪዳን ጥላ ነው። የእኛ ሊቀካህን ራሱ ክርስቶስ ኢየሱስ ነው። እግዚያብሄር ካህንን መርጦ የሚሾመው ከሰው መካከል ነው። አንደኛ ሌዊ የሚባል ካህን እግዚአብሔር አልሾመም። ሌዊ ራሱ ነው ለእግዚአብሔር ራሱን የለየው። ሙሴ ጽላቱን በሰበረ ጊዜ እንግዲህ ለእግዚአብሔር የቀና ይግባ ሲል ሌዊ ተነሳ እና የገዛ ወንድሞቹን ከመሬት እያጣበቀ መግደል ጀመረ። በዚያን ቀን 3000 ሰው ሞተ የተባለው ሌዊ የገደለውም ጭምር አለበት። ሌዊ *"ለእግዚአብሔር ቀንተሃልና ከወንድሞችህ መካከል አንተ ለእኔ ካህን ነህ"* ተብሎ ከአስራ ሁለቱ ነገዶች መካከል አንዱ የሆነው ሌዊ ለአስራ አንዱ ካህን ሆኖ ተሾመ። ነገር ግን እግዚአብሔር አንድን ሀገር ነው ካህን አድርጎ የጠራው። *"በአለም ካለው ህዝብ መካከል የንጉስ ካህናት ትሆኑልኝ ዘንድ"* ብሎ እስራኤልን ጠራ። ለአለም ህዝብ አንድ ሀገር - እስራኤል፤ ለአንድ ሀገር አንድ ነገድ - ሌዊ ነው የተመረጠው። ስለዚህ የሌዊ ሥራ የዓለምን ህዝብ ኃጢአት ማስተሰረይ ሳይሆን የወንድሞቹን ኃጢአት ማስተሰረይ ነው። ለአንድ ሀገር የሚቀርበው አንድ መስዋዕት ስለነበረ ነገዶች ተሰብስበው ሲያቀርቡ ሌዊ ነው ሌሎቹን ወክሎ የሚያቀርበው። የእስራኤል ሥራ ግን የዓለምን ነው። በጣም የሚገርመው ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስን አንድ ነገድ አላቀረበውም። እስራኤል

በሙሉ ነው ደሙ በእኛና በልጅ ልጆቻችን ላይ ይሁን ብሎ የተስማማው። ለመላው ዓለም አዳኝ እንዲሆን ካህን የሆነው እስራኤል ማረድና መሰዋት አለበት። ስለዚህ ልክ ካህኑ ሲወጣ ይባርካል አሜን ይላሉ ያበቃል።

የመንግስቱ ወንጌል ላይ ስትመጡ ግን ጌታ ኢየሱስ ሌላ ትምህርት አስተምሯል፣ *"እኛ የበደሉንን ይቅር እንደምንል በደላችንን ይቅር በለን"* ስለዚህ እዚህኛው ጋር ደግሞ ይቅር የምትባለው ይቅር ባልክበት መጠን ነው። ብዙ የይቅርታ ዝርዝር እግዚአብሔር ፊት ታቀርባለህ። አሁን ሰው ይህንን ጸሎት ሰው ከጸለየ *"ኢየሱስ ስለ እኔ ኃጢአት ያቀረበው መስዋዕት እሱ አይጠቅመኝም። ከኢየሱስ መስዋዕትነት እኔ ይቅር ያልኩት ይበልጣል።"* እያለ ነው። ይህ ፈጽሞ ለቤተክርስቲያን የተሰጠ መመሪያ፣ የፕሮግራም መክፈቻም መዝጊያም አይደለም።

ከሌዊ ነገድ ነው ካህን የሚሾመው። ከይሁዳ ነገድ ንግስና እንጂ ክህነት የለም። አብርሃም የተስፋ ቃል እና ኪዳን ያለው ብዙ የተስፋ ቃል የተገባለት ሰው ነው። ነገር ግን አንድ ጊዜ አንድ ሌላ መልከጼዴቅ የሚባል ሰው መጥቶ ተገናኘው። አብርሃም መልከጼዴቅን አልተገናኘውም ነገር ግን መልከጼዴቅ ራሱ አብርሃምን ተገናኘው። አብርሃም የተስፋ ቃል አለው። የተስፋው ቃል ደግሞ *"ክርስቶስ ባንተ ይመጣል፤ አህዛብ ባንተ ይባረካሉ"* የሚል ነው። ነገር ግን አብርሃም መልከጼዴቅን ሲያገኘው በመጀመሪያ መልከጼዴቅ አብርሃምን ባረከው ነው የሚለው። ልክ ከባረከው በኋላ አብርሃም ካገኘው ምርኮ ላይ አስራትን ለመልከጼዴቅ ሰጠው። *"ይህ ሰው የተስፋ ቃል ያለውን እንኳን ሳይቀር የባረከ ነው። ይህ ሰው ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ እዩ፣ እናት እና አባት ለትውልዱም ቁጥር የለውም"* ብሎናል የዕብራውያን ጸሐፊ ማነው ሲባል? በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ የሚኖር ካህን ነው ብሎ ገልጦታል።በሌላ አማርኛ የክርስቶስ ምሳሌ ነው። የዘር ግንዱ ሌዋዊ አይደለም፤ ክህነት አይገባውም። የዘር ግንድ መስፈርቱን ሳያሟላ ድንገት መጥቶ የተገናኘው ታላቅ ሊቀካህን ነው። ጥላው የክርስቶስ ኢየሱስ ነው፤ ኢየሱስ ክርስቶስ ደግሞ የመልከጼዴቅ አካል ነው። ኢየሱስ ክርስቶስ የመጣው ከሌዊ ነገድ ሳይሆን ከይሁዳ ነገድ ነው። ኢየሱስን ስናይ ከሌዊ ነገድ ስላልሆነ ክህነት አይገባውም ልንል እንችላለን።

ከመስቀል በፊት በነበረው ሕይወት በሙሉ የክህነት ሥራ የተሰጣቸው ሌዋውያን ናቸው። ነገር ግን በአዲስ ኪዳን የዕብራውያን ጸሐፊ እንዲህ አለ፣ *"ካህኑ ሲቀየር ሕጉም አብሮ ሊቀየር ግድ ነው።"* አሁን በሌዊ የሚሰራውን የክህነት ጥላ ዘጋውና ተፈጸመ ብሎ ሌላ አዲስ ካህን አስነሳ። ስሙም ኢየሱስ ይባላል። እሱ የሁላችን

ሊቀካህን ነው። እሱ እንደ ብሉይ ኪዳን ያለ ካህን አይደለም። እነሱ በየቀኑ መስዋዕት ያቀርባሉ። የብሉይ ኪዳን መቅደስ ውስጥ ወንበር የለም። የአዲስ ኪዳን መቅደስ ሰማያዊቷ ድንኳን ውስጥ ግን ወንበር አለ። በብሉይ ኪዳን *"እሳት ከመሰዊያው ላይ እንዳይታጣ"* ነው የተባለው። ምክንያቱም ኃጢአት ሰርቶ የሚመጣ አለ። በእጣ ክፍሉ እየተፈራረቀ ነው የሚጠብቀው እሳት ከጠፋ እስኪያያዝ ድረስ ኃጢአተኛ ሊሞት ይችላል። እሳት ከመሰዊያው እንዳይጠፋ ማለት ጸሎት እንዳይቆም ማለት አይደለም።መስዋእት የሚቀርብበት እሳት ሁሌ ዝግጁ መሆን አለበት። ከመስቀል በኋላ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ የምድር ድንኳን ውስጥ ሳይሆን የገባው ሰማያዊቷ ድንኳን ውስጥ ነው። እሱ ሊቀካህን ነው እኛ ደግሞ ካህናት ነን። ሌዊ ካህን ነው፤ አሮን ደግሞ ሊቀካህን ነው። ካህን የሚሆነው የሊቀካህን ልጅ ነው። ሊቀካህን ኢየሱስ ነው፤ አንተ ደግሞ ካህን ነህ ማለት ልጅ ነህ ማለት ነው። አዲስ ፍጥረት ሆኖ ሲገባ ከእርሱ ጋር አብረን ገብተናል።

በብሉይ ኪዳን በየቀኑ ነው መስዋዕት የሚቀርበው። በመንግስቱ ወንጌል ደግሞ ይቅር ብለህ ነው ይቅር የምትባለው። ከመስቀል በኋላ ግን ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ይቅር በለኝ ሳትል፣ መስዋዕት ሳታቀርብ፣ መጽሐፍ እንደሚለው *"በመረቀልን በህያው እና በአዲስ መንገድ"*፤ ጌታ ኢየሱስ የመረቀው አዲስ መንገድ አለ። በአዲስ መንገድ ላይ አዲስ ሰው ነው የሚገባው።የበፊቱ መንገድ በሌዊ ነበር። አሁን ግን ወደ ሰማይ መግቢያ በር አለ። *"ማለትም በሥጋው ሰውነት"* ሲል ይሔ ሥጋ ተከፍቶ ገብተናል ማለት ሳይሆን፣ በሥጋው በሰራው ማለትም በፈጸመው፣ባጠናቀቀው የክርስቶስ ስራ ወደ አብ መግባት ሆኖልናል። ስንገባ እኛ ብቁዎች ሆነን አልገባንም። ስለእኛ የገባ አለ። ሲገባ በሌዊ መንገድ አልገባም። ሲገባ በአብርሃም መንገድ አልገባም። የገባው በአዲሱ መንገድ ነው። የገባው በአዲስ ህይወት ነው። የገባው አዲስ ሰው ይዞ ነው። የብሉይ ኪዳን ለአንድ አመት ብቻ ነው፤ ይሔኛው ግን ለዘለዓለም ነው። በብሉይ ኪዳን መቀመጥ አይፈቀድም፤ እሳት ቆሞ ሲያነድ ነው የሚውለው። ወደ አዲሱ ሊቀካህን ስትመጣ ግን ሁሉን ካጠናቀቀ በሁላ በግርማው ቀኝ ተቀመጥ አለው። ለምን ሲባል ስራው ተጠናቋል። የብሉይ ኪዳኑ ሊቀካህን ስራው ስላልተጠናቀቀ አያርፍም፣ አንደኛው ካህን ፈረቃውን ሲጨርስ ሌላኛው ይተካል። በአዲስ ኪዳን ግን የሚተካካ የለም፣ አንድ ነው ግን ለዘለዓለም ነው፡፡ የዕብራውያን መልዕክት ምዕራፍ 8፥1 ላይ

> *"ከተናገርነውም ዋና ነገሩ ይህ ነው፤ በሰማያት በግርማው ዙፋን ቀኝ የተቀመጠ እንዲህ ያለ ሊቀ ካህናት አለን፤"*

የተቀመጠው *ሥራ* ስለጨረሰ ነው። ዳግመኛ ስላንተ ጉዳይ መስዋዕት አይቀርብም። *"አንድ መስዋዕት አቅርቦ ለዘላዓለም የሚቀደሱትን የዘላለም ፍፁማን አድርጓቸዋል።"* እንዴ ነው ያቀረበው *ሥራው* ግን ለዘለዓለም ነው። ልክ ኢየሱስ ሔዶ ቁጭ ሲል መልአኩም ቁጭ አለ። ማን ያንከባልልናል ሲሉ ድንጋዩን አንከባልሎ መልአኩ ቁጭ ብሏል። መልአክ በብሉይ ኪዳን *"በእግዚአብሔር ፊት የምቆመው"* ነው እንጂ የሚለው የምቀመጠው አይልም። ሰማይ ስራ አልቆ ኢየሱስ ሲቀመጥ ግን እነሱም ቁጭ አሉ። መልአክ ከተቀመጠ አንተም ቁጭ በል፤ ስራው አልቋል። "ህያውን ከሙታን መካከል ስለምን ትፈልጋላችሁ፣ ተነስቷል እንጂ በዚህ የለም" ለእናንተ በተሰራው እኛም አርፈናል አሉ። 2ኛ ቆሮ 5፡19 እንደሚነግረን "እግዚአብሔር በክርስቶስ ሆኖ አለምን ከራሱ ጋር ያስታርቅ ነበር፣ አለምን ከራሱ ጋር ሲያስታርቅ የሰዎችን በደል አይቆጥርባቸውም ነበር።" ይላል። እግዚአብሔር ኃጢአትን መቁጠር አቁሟል።እግዚአብሔር በኃጢአት ጉዳይ መፍትሔ መስጠት አቁሟል። ምክንያቱም አንዴ ሰጥቷል። ሊቀካህን *ሥራው* ህዝቡን ወክሎ በእግዚአብሔር ፊት መስዋእትን ማቅረብ፤ እግዚአብሔርን ወክሎ ደግሞ መስዋእቱን መመርመር ነው። ኢየሱስ መስዋዕትም መስዋእት አቅራቢም ነው የሆው። ሆኖም ሲጨርስ በሉቃስ ወንጌል መጨረሻው ምእራፍ ላይ እየባረካቸውም ሳለ ከአይናቸው ላይ ደመና ሰወረችው። የእግዚአብሔር ስራ መባረክ ነው። ባርኮም ጨርሷል።እየባረከ ገብቷል ከዚህ በኋላ ባርከኝ ብትል ምኑን ነው የሚልህ። "አልሰማህም እንዴ? በደብረዘይት ተራራ ላይ አዝንቤው ነው የሔድኩት" ይልሃል። የሊቀካህን ስራው መባረክ ነዋ።አሁን የተቀመጠ ካህን አለህ።

አሁን ኃጢአት አይቆጠርም። ዳዊት፣ በእሱ ዘመን እየኖረ የአዲስ ኪዳን አማኞችን አየና እንዲህ አለ፣ *"እግዚአብሔር ሳይሠራ ደሞዙን የሚከፍለው ሰው እግዚአብሔር ኃጢአቱን የማይቆጥርበት ሰው ምን አይነት ብፁዕ ነው?"* ብሎ ተገርሞ ነው የሞተው። ያ ሰው እኔ እና አንተ ነን ምክንያቱም ሳይሠራ ክፍያ የተጀመረው አዲስ ኪዳን ላይ ነው፣ በክርስቶስ *ሥራ*። የሞተው እሱ የተጠቀምከው አንተ፣ ያረገው እሱ የገባኸው አንተ ነህ። ዳግም በክርስቶስ አምነህ ከዳንክ በኋላ "ጌታ ሆይ እኔ ኃጢአተኛ ነኝ" ብትል እግዚአብሔር "ልኩን የማያውቅ" ነው የሚልህ።

ምክንያቱም መጽሐፍ የሚነግረን *"በደላችሁን ሁሉ ይቅር አላችሁ"* ነው። *"ወደፊት ይቅር ይላችኋል"* አላለም። ይቅር የሚባለው ኃጢአተኛ ሰው ነው። አዲስ ፍጥረት ግን ይቅር አይባልም። የአለም ህዝብ ሁሉ እግዚአብሔር በመስቀል ላይ በልጁ በሰራው *ሥራ* ይቅር ተብሏል። እኛ ዳግም የተወለድን ግን ይቅር አይደለም

የተባልነው፤ አዲስ ፍጥረት ነው የሆንነው። ይቅር መባልና ዳግም መወለድ ሁለቱ የተለያዩ ናቸው። ዳግም መወለድ አዲስ ማንነት አዲስ ተፈጥሮ መያዝ ነው። ይቅር መባል ግን የድሮውን ይዘህ የሠራኸው ተትቶልሀል። እግዚአብሔር አይቆጥርብህም፣ ይቅር ብሎሃል። ስለዚህ ላስታርቅህ። ለዚህ ነው ጳውሎስ *"እግዚአብሔር ታርቋችኋልና እባካችሁ ታረቁ ብለን ስለ ክርስቶስ እንለምናለን በእኛ የማስታረቅን ቃል አኖረ"* ። የእኛ ሥራ ከክርስቶስ ጋር ታረቁ ብሎ መናገር ነው። "እምቢ ብትል ሲኦል ትገባለህ!" በሉ አላለንም። *"እግዚአብሔር ይቅር ብሎሃል፣ ታርቆሃል፤ ስለዚህ ይቅርታውን ተቀበል።"* በሉ ነው የተባልነው። ወንጌል ይሔ ነው፤ ኢየሱስ ብቻውን ሳይደመርበት ማለት ይህ ነው።

> *ሮሜ 3፡26-27 "እርሱንም እግዚአብሔር በእምነት የሚገኝ በደሙም የሆነ ማስተስሪያ አድርጎ አቆመው፤ ይህም በፊት የተደረገውን ኃጢአት በእግዚአብሔር ችሎታ ስለ መተው ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው፥ ራሱም ጻድቅ እንዲሆን በኢየሱስም የሚያምነውን እንዲያጸድቅ አሁን በዚህ ዘመን ጽድቁን ያሳይ ዘንድ ነው።*

የመጀመሪያው አዳም ኃጢአትን ሲያደርግ የመጀመሪያውን የኃጢአት መስዋዕት ያቀረበው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እግዚአብሔር በሰባተኛው ቀን አርፏል። ዘፍጥረት 3፡21 ላይ ደግሞ እንስሳን በማረድ ቆዳን አምጥቶ ሲያለብሳቸው እንመለከታለን።

ሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ለመታየት በራሱ የሠራውና የለበሰው ልብስ ግን የቅጠል ልብስ ነው። ቅጠል ጸሐይ ሲመታው የሚጠወልግና የሚደርቅ ነው። እንኳን በእግዚአብሔር ፊት በሰው ፊት ተቀባይነት አያስገኝም። ነገር ግን እግዚአብሔር በዘፍጥረት 3፡21 ላይ ቆዳን አምጥቶ አለበሳቸው፡፡ እዚህ ጋር ግን እግዚአብሔር ኃጢአትን ሸፈነ እንጂ አላስወገደም። ከዚህ ጊዜ ጀምሮ የተወለደ እያንዳንዱ ሰው ኃጢአትን እያደረገ ነው የመጣው። በብሉይ ኪዳን የኃጢአት መስዋዕት ሲቀርብ ወደ ቅድስተ ቅዱሳን የኃጢአት መስዋዕት ተይዞ ነው የሚገባው። በቅድስተ ቅዱሳን ውስጥ የስርየት መከደኛ አለ። ከስርየት መከደኛው በታች ደግሞ ሶስት ነገሮች አሉ። የአሮን በትር፣ የሙሴ ጽላት እና የህብስቱ መና። የሰው ልጅ ኃጢአት ተከምሮ ሲጨመቅ በሶስት ነው የሚጠቃለለው፤ ከዚያ በላይ የለም። ወይ ስልጣንን ይቃወማል፤ ወይ ሕጉን (የእግዚአብሔርን ቃል) ይተላለፈል፤ ወይ ደግሞ በመብል ምክንያት ያጉረመርማል።

ከነዚህ ውጪ የሆነ ኃጢአት የለም። እስራኤል በ40ው አመት ጉዞ ውስጥ የሰራቸው ነገሮች እነዚህ ናቸው። ስለዚህ እግዚአብሔር ኤግዚቢት አድርጎ በቅድስተ ቅዱሳን

ታቦት ውስጥ አስቀምጦታል። ከነዚህ በላይ ደግሞ የስርየት መክደኛ ተብሎ የሚሸፍን አለ። ከውስጥ ግን የአሮን በትር፣ የሙሴ ጽላት እና የህብስቱ መና አሉ። እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎት ነበር *"በስርየት መክደኛው ላይ ሆኜ አነጋግርሃለሁ"* ። የስርየት መክደኛው ላይ አንድ ካህን መስዋዕት ካቀረበ በኋላ ደሙን ይዞ ገብቶ በሂሶጵ 7 ጊዜ ይረጫል። 7 ቁጥር ፍፁም የሆነውን የእግዚአብሔርን ሙሉነት የሚያሳይ ነው። ስለዚህ ካህኑ 7 ጊዜ ሲያስነካ እግዚአብሔር የስርየት መክደኛው ላይ ሆኖ ያወራዋል። ኃጢአት ግን ተሸፍኖ ከስር አለ። እግዚአብሔር ኃጢአት ከስር እንዳይወጣ ምህረት (ስርየት) በሚባል መክደኛ አፍኖታል። እናም እሱ ከውጪ ቆሞ ነበር ሰውን የሚያወራው። ከመጀመሪያው ከአዳም ጀምሮ የነበረውን ኃጢአት እግዚአብሔር በደም እየሸፈነ እስከ ኢየሱስ ድረስ መጣ፤ ከዚያም ኢየሱስ ከአዳም ጀምሮ የነበረውን ሰው እኛንም አልፎ እስከ መጨረሻው ሰው ያለውን ኃጢአት ተሸክሞ መስቀል ላይ ጠረቀው።

ኃጢአት በራሱ ምንድነው? "sin" "missing the original mark" ይህም ማለት የተፈጠረበትን እውነተኛ ማንነት መሳት ወይም ከተፈጠረበት አላማ ውጪ መሆን ነው።አንዳንድ ሰው መዋሸት፣ መስረቅ፣ ኃጢአት ይመስለዋል። እግዚአብሔር ኃጢአት የሚለው መዋሸትህን ወይም መስረቅህን ሳይሆን ወደዚህ ድርጊት የጋበዘህን ተፈጥሮ ነው። ውሸት የሚባል ነገር የመጣው መጀመሪያ አንተ የተፈጠርክበትን አላማ ስለሳትክ ነው። የመጀመሪያው ሰው አዳም ኃጢአትን እንዲያደርግ የተፈጠረ ሰው አይደለም። ኃጢአት ውጪ ሆኖ አዳም ግን ከኃጢአት ውጪ (ያለ ኃጢአት) ሆኖ ይኖር ነበር። ቀድሞውኑም ኃጢአት ከእኛ አለም አይደለም፤ኃጢአት የሰው አለም ላይ አልተፈበረከም። ኃጢአት የተፈበረከው መላእክት አለም ላይ ነው። መላእክት አለም ላይ የተፈጠረበትን ማንነት ጥሎ ወደዚህ ምድር ሲጣል አዛዥ ሆኖ ወደ ሰው ልጅ መጣ እንጂ ኃጢአት የእኛ ተፈጥሮ አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስ በሮሜ 5፥12 እንደሚነግረን "ኃጢአት በአንድ ሰው ምክንያት ወደዚህ አለም ገባ" ይላል። ገባ ካለ ከዚህ ቀደም አልነበረም ማለት ነው ።ሰርጎ ገብ ነው። ሰርጎ ገብ በር የሚከፍትለት ካለ ነው የሚገባው። የመጀመሪያ ኃጢአትን ያደረገችው ሄዋን ነች። ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ በአንድ ሰው ምክንያት ኃጢአት ገባ አለ እንጂ ሁለቱ ተስማምተው አላለም። ይህ ማለት ሄዋን ብቻ በልታ አዳም ባይበላ ኖሮ፣ ሄዋን ኃጢአተኛ ተፈጥሮ አይኖራትም ነበር። ምክንያቱም ሁሌም እግዚአብሔር ጉዳዩ ከዘር ጋር ስለሆነ ነው። ኃጢአት በአንድ ሰው ምክንያት ወደ አለም ሲገባ እግዚአብሔር ዝም ብሎ "ሂድ ውጣ" ማለት አይችልም። ምክንያቱም ኃጢአት

ተያይዞ የሚያመጣው ደሞዝ ስላለ፤ ደሞዙ ደግሞ ሞት ነው። ስለዚህ የኃጢአት ደሞዝ ሞት ስለሆነ፣ ሰው መሞት አለበት፣ ወይ ደግሞ የሰው ልጆችን ኃጢአት መክፈል የሚችል ከኃጢአት ነፃ የሆነ ሌላ ፍጥረት መፈጠር አለበት። ይህንን ለማምጣት ነው እንግዲህ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ ወደዚህ ምድር የመጣው። እንደ እኛ በነገር ሁሉ ተፈትኖ አንድም ኃጢአት አልተገኘበትም። በባህሪው ፃድቅ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ በ2ኛ ቆሮ 5፡21 ላይ እንደሚነግረን "ኃጢአት ያላወቀውን እርሱን ስለ እኛ ኃጢአት አደረገው" ፤ ኃጢአት አደረገውና ኃጢአተኛ አደረገው ሁለቱ ይለያያሉ። ኃጢአት ከሆነ ያደረገው ቅድም ሾልኮ ገባ ያልነውን በአንድ ሰው ምክንያት ወደዚህ ዓለም ገባ የተባለውን እርሱን ሆነ ማለት ነው።

"ምኞት ፀንሳ ኃጢአትን ትወልዳለች ኃጢአት ደግሞ ሞትን" ጌታ ኢየሱስ የሄደው ጉዞ ከጌቴሴማኔ እስከ ጎልጎታ ነው። ጌቴሴማኔ ላይ "አባት ሆይ ብትወድ ይህች ጽዋ ከእኔ ትለፍ፤ ነገር ግን የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ትሁን" ብሎ የመጨረሻውን ጸሎት የጸለየበት ነው። ጌቴሴማኔ ማለት የስሙ ትርጉም "place of lust" ወይም "የምኞት ስፍራ" ማለት ነው።ጎልጎታ ሌላኛው ስሙ የራስ ቅል ነው - የሞት ስፍራ ነው። የተፀነሰው ምኞት ስፍራ ጋር ጌቴሴማኔ ነው ጽዋውን የተቀበለው። ፍፃሜን ያገኘው ጎልጎታ ላይ ነው። ከምኞት እስከ ሞት ያለውን ሂደት ጌታ ኢየሱስ አልፎበታል። ኢየሱስ የእኔ ፈቃድ ሳይሆን የአንተ ፈቃድ ይሁን ሲል ምን ማለቱ ነው? የእግዚአብሔር ፈቃድስ ምን ነበር? መልሳችን ይህ ነው።መድቀቁ፣ መቁሰሉ እና መሰቃየቱ የእግዚአብሔር ፈቃድ ነበር። ትን. ኢሳይያስ 53፡10 "እግዚአብሔር በደዌ ያደቅቀው ዘንድ ፈቀደ፤ እኛ ግን በእግዚአብሔር እንደተመታ ቆጠርነው እርሱ ግን የሁላችንን በደል ተሸከመ" ይላል።እግዚአብሔር እስከ መስቀል ድረስ ኃጢአትን እየሸፈነ ኖረ እንጂ አላስወገደም።

የሆነ ቤት ላይ ገብታችሁ በጣም የቆሸሸ ምንጣፍ ብታገኙ እና አዲስ ምንጣፍ ገዝታችሁ በላዩ ላይ ብታነጥፉበት፤ እንዳነጠፉችሁት የማያውቅ ሰው ሲመጣ ቤቱ አዲስ የሆነ ነው የሚመስለው ነገር ግን ቆሻሻው ከስር አለ። ሁሌ በየአመቱ ይህንን ብታደርጉም ቆሻሻው ከስር አለ።እግዚአብሔርም እንደዚህ ነበር ያኖረው። የሰው ኃጢአት ተወግዶ ሳይሆን በየአመቱ አዲስ እንስሳ እያረደ በደም መርጨት እየሸፈነ ነው ያኖረው። መስቀል ላይ የሞተው ኢየሱስ ወይም የእግዚአብሔር ልጅ ሆኖ ሳሆን። መስቀል ላይ የሞተው ኃጢአት የሚባለውን ስብዕና ይዞ ነው። ብዙ ሰው አልቅሶለታል። ነገር ግን ሰማይ ሲያይ "ወይኔ ልጄ ተገረፈ" አይደለም ያለው። "ኃጢአትን አስገረፍኩት" እንጂ "ልጄን አስገረፍኩት" ብሎ አስቦም አያውቅም።

መስቀሉን ከምድር ወደ ሰማይ ስታየውና ከሰማይ ወደ ምድር ስታየው ሁለት የተለያየ ትርጉም ነው የሚሰጠው። ከምድር ሲታይ

> *"እኛ ግን እስራኤልን እንዲቤዥ ያለው እርሱ እንደ ሆነ ተስፋ አድርገን ነበር፤ ደግሞም ከዚህ ሁሉ ጋር ይህ ከሆነ ዛሬ ሦስተኛው ቀን ነው።"*

ብለህ ነው የምትፈታው። ከሰማይ እግዚአብሔር ሲያየው ግን ኃጢአት ራሱ እንደሞተ ነው። ሰማይ ገደልኩት ያለው ኃጢአትን እንጂ ልጁን አይደለም። ልጁ በፍፁም መሞት የሚችል አይደለም፤ ማንም አቅም ያለው ሊገድለውም አይችልም። ኃጢአት እግዚአብሔርን አይገድልም፤ እግዚአብሔር ኃጢአትን ይገድላል እንጂ።

*"ነፍሴን በፈቃዴ እሰጣለሁ እንጂ ማንም ከእኔ አይወስዳትም"* ብሏል ጌታ ኢየሱስ። ጌቴሴማኔ ላይ ጸልዮ ሲወጣ ይሁዳ *"ኑ እኔ አውቀዋለሁ የት እንደሚጸልይ አብረን ስንበላ ስናሳልፍ ነበር እና ብዙ ጊዜ የሚጸልየው ጌቴሴማኔ ነው።"* ብሎ በ30 ብር ሊሸጠው ተስማምቶ ይዟቸው መጣ። ሲመጡ ጌታ ኢየሱስ ወጥቶ ተቀበላቸው። ብዙ ወታደሮች አሉ ይሁዳ ግን መሪ ነው። "ኢየሱስም ወጣና ማንን ትፈልጋላችሁ?" አላቸው። "የናዝሬቱን ኢየሱስን አሉት" ። ይሁዳ ራሱ አብሯቸው ሆኖ አላወቀውም። እናም *"እኔ ነኝ"* ሲላቸው ወደቁ። ድጋሚ ተነሱ፣ "አሁንም ማንን ትፈልጋላችሁ?" ኢየሱስን አሉ። *"እኔ ነኝ አልኳችሁ"* ሲል በድጋሚ ወደቁ። *"እኔ ነኝ"* የእግዚአብሔር ስም ነው። *"እኔ ነኝ"* በሚለው ስም ፊት ስም ማንም መቆም አይችልም። አያችሁ በፈቃዱ እንጂ ታልፎ የተሰጠው ማንም አቅም ስላለው አልገደለውም። ይህ እንዲሆን ያደረገው ደግሞ የእኔና የአንተ ፍቅር ነው። ልቡ ውስጥ ያለኸው አንተ ስለሆንክ። ዳዊት እንደዚህ አለ፣ *"ወደ ሰማይ ብሔድ አንተ በዚያ አለህ፣ ወደ ሲኦል ብወርድ በዚያ ትገኛለህ" አንተ* የሌለህበት ስፍራ የለም አለ።

አንድ ጊዜ ደግሞ አለ፣ቆይ እስኪ ብዬ ወደ እግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ገብቼ አእምሮውን ሳነበው፣እግዚያብሄር ስለ ሰው ልጆች ስባል ይህንን ጊዜ እንዲህ አለ *"ታስበው ዘንድ ሰው ምንድነው? ትጎበኘው ዘንድ የሰው ልጅ ምንድነው?"* ዝም ብሎ ቁጭ ብሎ እኮ አይደለም እንደዚህ ያለው፣ ዳዊት በአምልኮ ገብቶ ተመለከተው። ሲገባ እልፍ አእላፍ መላእክቶች አሉ፣ አንዴ አሳልፉኝ ብሎ የገባ ይመስለኛል ፤ ሲገባ ደግሞ 24 ሽማግሌዎች አሉ፣ አሁንም እነሱን አልፎ ሲገባ ኪሩቤሎች አሉ። በስተመጨረሻ እግዚአብሔር አእምሮ ውስጥ ሲገባ እግዚአብሔር እዛ ሁሉ አምልኮ ውስጥ ሆኖ የሚያስበው በልጁ በኩል ሰለሚፈጥረው የልጅነትና ያባትነት ህብረት ያስባል። ያንተ አባት በዚህ ሁሉ አምልኮ ውስጥ አንተን ያስባል። ከዓለም መካከል

መርጦ፣ ከሀገር መካከል መርጦ፣ ከሰፈር መካከል መርጦ፣ ከዚህም ህዝብ መሀል መርጦ አንተን ያስባል። አምልኮ ጎድሎት እንድታመልከው ፈልጎ አይደለም አንተን ሲስብ ነበረው። እግዚአብሔር ጉቦኛ አይደለም። እግዚአብሔር አምልኮ ጎድሎበት አያውቅም፣ እልፍ አእላፍ መላእክቶች ያመልኩታል።እግዚአብሔር ለመኖር አምልኮ አያስፈልገውም። ከሰው በፊት መላእክት ተፈጥረዋል አምልኮ ውስጥ ነበረ እግዚአብሔር ስላንተ ሲያስብ የነበረው። ስለዚህ እንድታመልከው ብሎ አንተን አልፈጠረህም። ታገለግለውም ዘንድ አልፈጠረህም። እግዚአብሔር የፈጠረህ ያለውን ሕይወት አካፍሎህ አብሮህ ለመኖር ነው። ፍቅር ግድ ብሎት እንጂ አምልኮ ጎድሎበት አልተፈጠርክም። በ1ኛ ቆሮ 13፡5 ላይ *"ፍቅር የራሱን አይፈልግም"* ብሎናል።በዮሐንስ መልዕክት መሰረት እግዚአብሔር ፍቅር ነው። ስለዚህ ፍቅር የሆነው እግዚያብሔር አምልኮ ፈልጎ እና ማንኛውንም የራሱን ፈልጎ አይደለም የፈጠረን ማለት ነው።

ኢየሱስ ከሞተ 2000 ዓመት አልፎታል አይደል? ። መቼም 2000 አመት የሞላው ሰው የለም? የሰው እድሜ ሰባ (70) ሰማኒያ (80) ነው ከዛ ቡሀላ ደካም እንደሆነ በቃሉ ተነግሯል ። እሺ እንዲህ ከሆነ ታዲያ አንተ እድሜ የኢየሱስ ስራ እንደሚቀድምህ ታስተውላለህ? ታዲያ መቶ አመት ካልሞላህ ስራው እውነት እንደሆነ አንተ በምን ታውቃለህ? አልነበርክም በቦታው። እኔና እናንተ ኢየሱስ በነበረበት ዘመን ገና አልተወለድንም፤ ሥራው ግን አልፎ መጥቶ የልጅ ልጆቻችን ጨምሮ እስከ መጨረሻው ሰው ያለውን ጠቅልሎ ነው መስቀል ላይ የተሰራው። የኢየሱስ ክርስቶስ ስራ ያለፈውን የአሁኑን ደግሞም የወደፊቱን ኃጢአትህን ሙሉ ለሙሉ አስወግዶታል። ወንጌል ይህ ነው። ነገ ኃጢአት ሳትሠራ በፊት እግዚአብሔር የነገህን ኃጢአት ከፍሎታል። ወንጌል ማለት መልካም ዜና ማለት ብቻ አይደለም። ለማመን የሚቸግር ነገር ግን እውነት የሆነ ዜና ማለት ጭምር እንጂ። ለዛ ነው ብዙ ሰዎች ለመቀበል የሚከብዳቸው። "ገና ኃጢአት ሳልሰራ እግዚአብሔር የነገውን ኃጢአቴን ይቅር ብሎኛል?" ብሎ እሚጠይቅ ይኖር ይሆናል።እኔ እምልህ አዎ! ነው። ምክንያቱም እኔ አይደለሁም ይህን ያልኩት መጽሐፉ ነው።

## *በረከት በብሉይ ኪዳን፣ በመንግስቱ ወንጌል እና በአዲስ ኪዳን*

በብሉይ ኪዳን ስለ በረከት ብዙ ጥቅሶችን እናገኛለን። በዋነኝነት ዘዳግም 28ን ነው የምናየው። ከዚህ በፊት እንዳየነው ዘዳግም 28 ላይ እሺ ብለህ ስትታዘዝ ነው የምድርን በረከት (ስብ) የምትበላው። እምቢ ብለህ ባትታዘዝ ግን ዋጋ ትከፍላለህ፣

እርግማንም ተያይዞ ይመጣል። ስለዚህ በብሉይ ኪዳን ለመባረክ ብቸኛው መንገድ ህጉን እንደሚገባ መታዘዝ እና መታዘዝ ነው። እዚህ የመንግስቱ ወንጌል ላይ ግን ኢየሱስ ሌላ ነገር ሲያስተምር ታገኙታላችሁ። *"በምትሰፍርበት መስፈሪያ ይሰፈርልሃል"* መስፈሪያውን የምትሠራው አንተ ነህ፣ በሰፈርክበት መስፈሪያ ይሰፈርልሃል። በብሉይ ኪዳን ግን እንዲሰፈርልህ መጀመሪያ ትሰራለህ። ካልታዘዝክ ደግሞ አልታዘዘም ተብሎ አይታለፍም ፤ ስላላሟላ እርግማን ይድረስበት ነው የሚለው። እዚህ ጋር ግን እርግማን የሚባል ነገር አያገኝህም ነገር ግን መስፈሪያ ጆጉን ይዘህ የምትመጣው አንተ ነህ።

ከመስቀል በኋላ ግን አንድም ቦታ ላይ መስፈሪያ ይዘህ ና አይልም። ስፈርም አይልም። የሚለው *"አምላኬ እንደ ባለጠግነቱ መጠን በክብር በክርስቶስ ኢየሱስ የሚያስፈልጋችሁን ሁሉ ይሞላባችኋል"* ነው። አሁን እዚህ ጋር መስፈሪያው አንተ ሳትሆን እራሱ ኢየሱስ ክርስቶስ ሆኗል። ጳውሎስ በ1ኛ ቆሮ 8 እና 9 ስለ መዝራትና ስለ ማጨድ የተናገረውን እንይ። መዝራት እና ማጨድ ጥሩ ትምህርት ነው። ነገር ግን የአማኝ ትምህርት አይደለም። መዝራት እና ማጨድ ለፍጥረታዊ ሰው ጭምር የሚሰራ ሕግ ነው። እኛ ስለ እዚህ አናወራም። እግዚአብሔር ለማጨድ አልዘራም። እግዚአብሔር ልቡ ውስጥ *ነገ አምኖ "ይህን ያህል ህዝብ ይከተለኛል"* በሚል አይደለም አንድያ ልጁን ወደ እኛ ህይወት የዘራው። እግዚአብሔር ሲዘራ እንዲዘራ ያደረገው ፍቅር እና ፍቅር ብቻ ነው። ለራሱ ጥቅም አስቦ *"መቶ እንዲሆንልኝ"* ብሎ አይደለም። እግዚአብሔር የማባዣ ማሽን አይደለም።

ሁለተኛ ደግሞ እግዚአብሔር ቁማርተኛም አይደለም። ቀይዋን ያየ አይጫወትም። 10 ሰጥተህ 1000 የምትጠብቅበት ቤት የለውም። በጣም ብዙ ጴንጤ እግዚአብሔር ስለሰጠህ ስጥ ብትለው መስጠት አይፈልግም፤ ግን "ጌታ ይለኛል ዛሬ መቶ ብትሰጥ በዚህ 3 ወር ውስጥ እንዲህና እነዲያ ይሆንለሃል" ከተባለ አንድ ሺውን ይሰጣል። ስለዚህ ፍቅር ሳይሆን ከልቡ የመነጨው ቁማር ነው። እግዚአብሔር የሚልህ "አልሰጥህም፣ ከሰጠሁህ ስጥ" ነው። ከተሰጠህ ይልቅ እግዚአብሔርን ምን ያክል እንደምትወደው ማየት ይፈልጋል። ስትሰጥ እንዲሰጥህ አስበህ ከሆነ የመጀመሪያ የሳትከው ነገር እሱ ነው።

አንዲት እህት ይህን ታሪኳን ነገረችኝ፣ አንድ ሰው በጉባኤ "ጌታ ተናግሮኛል፣ በዚህ አንድ ወር ውስጥ 30,000 የሰጠ የአመቱን ያጭዳል። የሌላችሁ ሰዎች ፎርም ሙሉና በዚህ 15 ቀን ውስጥ ታስገባላችሁ። በዚህ 15 ቀን ውስጥ ያስገባ ሰው እግዚአብሔር፣ በአንድ አመት የሚያገኘውን ገቢ አባዝቶ በዚህ አንድ ወር ውስጥ ይሰጣችኋል"

አላቸው። የአመት ደሞዝ በአንድ ወር ከተሰጠማ ማን የማይፈልግ ሰው አለ። አንዳንዶቻችን የእግዚአብሔር ባህሪ ስላልገባን በአቋራጭ መበልጸግ ነው የምንፈልገው። እናም ይህች እህት እና ሌሎችም ሰዎች ሰጡ። ነገር ግን አመት አለፈ ምንም የሆነ ነገር የለም። መሸወዷ የገባት ይህን እውነት ስትማር ነው። *"ስጥ ይሰጥሃል፣ በምትሰፍርበት መስፈሪያ ይሰፈርልሀል" ይህ* የእኛ ወንጌል አይደለም። የመንግስቱ ወንጌል ላይ ነው ያለው። ጳውሎስ ጋር ስትመጣ ስጥ ይሰጥሃል አይልህም። ረሃብ ስለነበረ ነው ያዘዘው። የመቄዶኒያ ቤተክርስቲያን ቅዱሳን የነበራቸውን የልግስና ባለጠግነት እይ፣ ከድህነታቸው ጥልቀት ይሰጡ ነበር። ሀብታም ሆነው አይደለም የሰጡት። የድህነት ጥልቀት ውስጥ ነበሩ ግን ካልሰጠን ብለው ይለምኑን ነበር። ግድ የሚላቸው ማካፈል እንጂ ማብዛት አይደለም።

"ጌታ እንዲህ ይለኛል፣ ሌቦች አላችሁ እዚህ ቤት አስራት የምትበሉ፣ አስራቱን ለሚሰጥ ሰው የሰማይን መስኮት ባልከፍትለት ብሏል፣ ስለዚህ በታማኝነት ስጥ። ፈትኑኝ ብሏል ፈትነው፡፡" ወንድሜ፣ አስራት የሚሰራው በሁለት መንገድ ነው። አዲስ ኪዳን ላይ አስራት አታገኝም ብሉይ ኪዳን ላይ ነው ያለው። አስራት ለመክፈል በመጀመሪያ አይሁዳዊ መሆን አለብህ። ሁለተኛው አንድ ሰው አስራት ለማስወጣት (ክፈል) ለማለት ሌዋዊ መሆን አለበት።ይህ በህጉ የተደነገገ ነው እኔ አይደለሁም ያልኩት። ከሙሴ በፊት ግን አስራት ተጀምሮ ነበር።አብርሃም ለመልከጼዴቅ አስራትን አወጣ። አስራትን እንዲያወጣ የሚያዘው ሕግ ግን አልነበረም፡፡ መልከጼዴቅ ሄዶ ተገናኘው እና አብርሃምን ባረከው። አሁን መጀመሪያ የባረከው መልኬ ጼዴቅ ነው። አብርሃም ከተባረከ በኋላ ነው ካገኘው ምርኮ ላይ ለመልኬ ጼዴቅ አስራትን ያወጣው። አብርሃም የአስራት እውቀት ውስጡ ነበረው። ነገር ግን በሕግ ተጽፎለት ይህንን አድርግ ተብሎ አይደለም፡፡ አብርሀም በነበረበት የኑሮ ዘመን ላይ የነበረው ባህል አንድ ሰው ምርኮ ማርኮ ሲመጣ በምርኮ ካገኘው ነገር ላይ እንደ መልኬ ጼዴቅ አይነት ታላቅ ሰው እንኳ መጥቶ ባይገናኘው ሰፈር ውስጥ ይቆምና ማነው የከበረ ሽማግሌ ብሎ ይፈልጋል። ይፈልግና ያንን ሽማግሌ ሄዶ ካገኘው ነገር ላይ ያካፍለዋል። ሲያካፍለው መልእክቱ አንድ ነው፣ "አንተ በከበሬታ ወይም ደግሞ ከፍ ባለ ነገር በሰፈር ካሉት ሰዎች የተሻልክ ነህ፡፡ ከእኔም ትሻላለህ፣ይህንን ድል እንኳን ያገኘሁት በእናንተ ባርኮት (ምርቃት) ነው።" በሚል ለዛ ሰው ክብር እንዳለው የሚያሳይበት መንገድ ነበር።

ብሉይ ኪዳን ላይ ደግሞ አስራትን መክፈል እንደ ሕግ ሆኖ እናገኘዋለን። እንደ ሕግ ሆኖ የመጣው ግን ለሌዊ እና ለአስራአንዱ ነገድ እንጂ ለኢትዮጵያዊ አይደለም።

የሰማይን መስኮት ባልከፍትላችሁ ፈትኑኝ ያለው አስራት ለሚበሉ በሚልክያስ ዘመን ለነበሩ አይሁድ እንጂ ዛሬ ላይ ለምንኖር የአዲስ ኪዳን አማኞች አይደለም። አስተውሉ እግዚአብሔር ቅደም ተከተልን የሚያከብር የስርአት አምላክ ነው፡፡ የአብዬን ለእምዬ ጠቅሶ እኛን አስፈራርቶ ብር አይቀበልም፡፡ ሰዉ “አስራት ከበላህ ከወር ወር ተበዳሪ ትሆናለህ” ተብሎ እርግማን ሲነገረው “አሜን! እውነት እኮ ነው” ብሎ ይሄዳል። እንደተነገረው እና እንዳመነው የብድር ህይወት ወሩን እየተበደረ ይጨርሳል፡፡ ምክንያቱም አስራት ባለመክፈልህ ተበዳሪ ትሆናለህ ስላሉት አሜን ስላለ እንጂ እግዚአብሔር ተበዳሪ ስላደረገው አይደለም። አስተውል፣ እግዚአብሔር ኃጢአተኛ ሳለ ሞቶልህ፣ ሳታውቀው አውቆህ ካወቀህና ካወቅከው በኋላ ከሞተልህ እና ህይወቱን ከሰጠህ በኋላ አስራት አልከፈለም ብሎ ተበዳሪ የሚያደርግ አምላክ ይመስልሀልን? ።ሙት ሳለሁ ከሞተልኝ ህያው አድርጎኝ እንዴት ተበዳሪ ያደርገኛል? በአዲስ ኪዳን ላይ ከመስቀል በኋላ አንድም ቦታ ላይ አስራትን ክፈሉ ብሎ ሐዋርያትም ሆኑ ኢየሱስ አስራትን ሲያስወጡ አታገኝም። በአዲስ ኪዳን ዕብራውያን ላይ ብቻ “አስራትን የሚያስወጣ በዚያ አለ” የሚል አንድ ጥቅስ አለ። ይህንን ጥቅስ በትክክል ካልፈታነው እንስታለን።

“የሳሌም ንጉሥና የልዑል እግዚአብሔር ካህን የሆነ ይህ መልከ ጼዴቅ አብርሃም ነገሥታትን ገድሎ ሲመለስ ከእርሱ ጋር ተገናኝቶ ባረከው፤ ለእርሱም ደግሞ አብርሃም ከሁሉ አስራትን አካፈለው። የስሙም ትርጓሜ በመጀመሪያ የጽድቅ ንጉሥ ነው፣ ኋላም ደግሞ የሳሌም ንጉሥ ማለት የሰላም ንጉሥ ነው። አባትና እናት የትውልድም ቍጥር የሉትም፥ ለዘመኑም ጥንት ለህይወቱም ፍጻሜ የለውም፣ ዳሩ ግን በእግዚአብሔር ልጅ ተመስሎ ለዘላለም ካህን ሆኖ ይኖራል። የአባቶች አለቃ አብርሃም ከዘረፋው የሚሻለውን አስራት የሰጠው ይህ ሰው እንዴት ትልቅ እንደ ነበረ እስኪ ተመልከቱ። ከሌዊ ልጆችም ክህነትን የሚቀበሉት ከህዝቡ ማለት ከወንድሞቻቸው፣ እነርሱ ምንም ከአብርሃም ወገብ ቢወጡ፣ ከእነርሱ አሥራትን በሕግ እንዲያስወጡ ትእዛዝ አላቸው፤ ትውልዱ ከእነርሱ የማይቈጠረው ግን ከአብርሃም አሥራትን አውጥቶአል፣ የተስፋ ቃል የነበረውንም ባርኮአል። ትንሹም በታላቁ እንዲባረክ ክርክር የሌለበት ነገር ነው።” (ዕብ 7፡1-7)

ስለዚህ አንድ ሰው አስራት ለማስወጣት ሌዊ መሆን አለበት ማለት ነው። ከሌዊ ውጪ አስራት የማስወጣት መብት የተሰጠው አካል ማንም የለም። ኢትዮጵያዊ አይመለከተውም። ይሔ ሰው አስራትን እንዲያስወጣ የተሾመ ቢሆንም በአብርሃም ወገብ ሆኖ እርሱ ራሱ ለመልከጼዴቅ አስራትን አውጥቶአል። ጥያቄው የአስራት

ጉዳይ ሳይሆን ሁልጊዜም ትንሹ በትልቁ እንዲባረክ ግድ አለበት። ትንሹም ሁል ጊዜም የትልቁን ትልቅነት የመመስከር ግድ አለበት።አብርሃም መልከጼዴቅ ከእሱ እንደሚሻል እውቅና የሰጠው በአስራት ነው።

“በዚህስ የሚሞቱ ሰዎች አሥራትን ያስወጣሉ፣ በዚያ ግን የሚያስወጣ በሕይወት እንዲኖር የተመሰከረለት እርሱ ነው። ይህንም ለማለት ሲፈቀድ፣ አሥራትን የሚያስወጣ ሌዊ እንኳ በአብርሃም እጅ አሥራትን ሰጥቶአል፤ መልከ ጼዴቅ በተገናኘው ጊዜ ገና በአባቱ ወገብ ነበረና። እንግዲህ ህዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን፣ እንደ አሮን ሹመት የማይቈጠር፣ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሳ ወደፊት ስለ ምን ያስፈልጋል?” (ዕብ 7፡8-11)

በምድር ድንኳን ውስጥ ሞት የከለከላቸው ሰዎች አስራትን ያስወጣሉ። በሰማያዊ ድንኳን ደግሞ ሌላ አለ ኢየሱስ የሚባል ክህነቱ የሌዊ አይነት ሳይሆን እንደ መልከጼዴቅ ለዘላለም ካህን የሆነ።መልኬጼዴቅ ልክ አብርሃምን እንዳገኘው አስራት አምጣ አላለውም ባረከው እንጂ። ልክ ሲባርከው አብርሃም እጅግ ተገርሞ እኔ ያሰብኩት ጋሽ እከሌን ነበር የሰፈር ሽማግሌ ብዬ፣ አንተ በእርግጥ ትለያለህ ያለው ይመስለኛል። ምክንያቱም የዘር ግንዱን እንኳን አያውቀውም እናትና አባት የሌለው አካል ነው የተገናኘው። ታላቅ መሆኑ ገብቶታል አበራረኩ ለየት ያለ ነው፣ የሰፈር ሽማግሌ እንደሚባርከው አይነት አይደለም።ስለዚህ ካገኘው ነገር ሁሉ አካፈለውና ታላቅ መሆኑን መሰከረለት። ይህንን ሲያደርግ ሌዊ በአብርሃም ወገብ ውስጥ ሆኖ አብሮ ታላቅ መሆኑን መስክሯል። በብሉይ ኪዳን ሞት የከለከላቸው ሲሆኑ እሚያሶጡት ከመስቀል በኋላ ግን በህይወት እንዲኖር የተመሰከረለት አስራትን ያስወጣል። የበፊቱ የክህነት ስርአት ፍፁም ቢሆን ኖሮ የኢየሱስ ክህነት ባላስፈለገ ነበር። ይህ ማለት የበፊቱ ስርአት አንተን አይመለከትህም ማለት ነው። ምክንያቱም እግዚአብሔር ያልረካበት እና ያልተደሰተበት ነው። ይህ ስርአት ስላላስደሰተው ነው የቀየረው ህዝቡን ሳይሆን ካህኑን ነው። ምክንያቱም ሁልጊዜ ህዝቡን የሚወክለው ካህኑ ነዋ።

*“ክህነቱ ሲለወጥ፣ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና።” (ዕብ 7፡12)*

በሌዊ ሲሰራ የነበረ የክህነት አሰራር ሕግና ደንብ አለው፡፡ መስዋዕት አቅርበህ ነው ኃጢአትህ ይቅር የሚባለው፣ አስራትን ከፍለህ ነው የሰማይ መስኮት የሚከፈትልህ፣ ይህኛው ህጉ ነው። ህጉን የመሰረተው ደግሞ ካህኑ ነው። ካህን ባይኖር ህጉ

አይሰራም። ጥያቄው በሌዊ ስር ነህ ወይስ በኢየሱስ ስር ነህ? ነው። አሁንም አስራት ከፍዬ መስኮት አስከፍታለሁ ካልክ አሁንም በሌዊ ስር ነህ። ሊቀካህንህ የሆነው ኢየሱስ ከሆነ ህጉ ተቀይሯል።ምክንያቱም ከጸጋ በታች እንጂ ከሁግ በታች አይደለንም እና። "ከላመጣህ ቆልፌዋለሁ፣ ከወር እስከወር ተበዳሪ ትሆናለህ፣ በቀዳዳ ኪስ ውስጥ ታስቀምጣለህ" የሚልህ ሌዊ ነው።የኢየሱስ ክህነት ጋር ስትመጣ ግን ሳትከፍለው በፊት ባርኮሃል፤ እየባረከህ ነው ከፍ ከፍ ያለው፡፡ ይህ ደግሞ ጸጋ ነው። እንደውም መጽሐፍ ሲነግረን ስላንተ ራሱን መባና አስራት አድርጎ ለእግዚያሔር አቅርቦልናል። ነገ እንደማትከፍል ሌባ እንደሆንክ ስለሚያውቀው ራሱን አስራት አድርጎ ቀረበልን ። አየህ ወንጌል ማለት ኢየሱስ ሲደመር ምንም ነው። በኢየሱስ ስራ ላይ የአንተ አስራት ሰማይ አያስከፍትም። በሌዊ ክህነት ከፍለህ እንኳን ስትጨርስ መስኮት እንጂ በር አይከፈትም። በኢየሱስ ክህነት ግን በመረቀልን በህያው እና አዲስ መንገድ፣ መራመድ ሆኗል። በሩ እኔ ነኝ ብሏል።እሱ በከፈተው እኛ ገብተናል። እግዚአብሔር አሁን አስራት አልከፈክም ብሎ አይጠይቅህም። ህያው እግዚአብሔር ምስክሬ ነው! ለሆስፒታል አታወጣም፣ ሌባ አይሰርቅህም፣ ተጠብቀህ ትኖራለህ፣ እየሰረቅህ ይባርክሃል። ፍቅሩ ሲገባህ ግን እያለቀስክ ትሰጣለህ። እግዚአብሔር ወደኸው እንድትሰጥ እንጂ ፈርተህ ወይም ደግሞ አንድ ሺህ እንዲሆንልህ አስበህ አትስጥ።

እና አሁን አስራት በአዲስ ኪዳን የለም ማለት ነው? የለምም አለምም። የለም ስንል የብሉይ ኪዳን አይነት አስራት ነው የሌለው። አለ ስንል ደግሞ "በህይወት እንዲኖር የተመሰከረለት" ይህም ማለት አስራት ብለን ስሙን አንጥራው እንጂ ለእግዚአብሔር ቤት መስጠት የግድ ያስፈልጋል። ይሄ ምንም ጥያቄ የለውም። ስትሰጥ ግን "ባለፈው እገሌ 10 ብር ሰጥቶኛል 1 ብር የጌታ" ብለህ አስልተህ ሳይሆን በውስጥህ የእግዚአብሔር መንፈስ ስላለ በልብህ እንደሞላው ደስ እያለህ ነው መሆን ያለበት። ስትሰጥ ግን ምን እያልክ መሰለህ "በህይወት እንዲኖር የተመሰከረለት" ይህም ማለት ኢየሱስ ሞቶ እንዳልቀረ ከሙታን መካከል ተነስቶ በአብ ቀኝ በመቀመጥ በአዲሲቱና በሰማያዊቷ ድንኳን ውስጥ ስለአንተ የሚማልድ ሊቀካህን እንዳለና፣ ከእኔ የሚሻል ነው ብለህ እውቅና እየሰጠኸው እንጂ ለመባረክም አይደለም።አሁንም ስትሰጥ አትባረከም፤ ሰው ሁሉ ሰጥቶ የውስጥ ደስታ ያገኛል።መጽሐፍ ቅዱስም "ከሚቀበል ይልቅ የሚሰጥ ብፁዕ ነው" ብሎናል እሱ ላይ ድርድር ውስጥ አንገባም። ምድር ላይ የምድር የስበት ሕግ አለ፤ ከዛ በላይ ደግሞ አውሮፕላን የሚሄድበት ኤሮዳይናሚክ የሚባል ሌላ ሕግ አለ። ልክ እንደዚሁ የመዝራትና የማጨድ የተፈጥሮ ሕግ አለ፤

እኔና እናንተ ደግሞ ሰብረን የገባንበት የእግዚአብሔር የልቡ ትርታ የሆነ ሕግ አለ፣ እሱ ደግሞ የፍቅር ሕግ ይባላል። ያ የፍቅር ሕግ ደግሞ ለብዛት እንዲሆንልኝ ብሎ አያሰጥም። ለእኔ የተከፈለው ዋጋ ሲገባኝ ስለእኔ ቆሞ የሚማልደው በአብ ቀኝ የተቀመጠው ካህኔ ማን እንደሆነ ስረዳው እራሱ የተደረገልኝ ምንም ባደርግ ስለማይመጥን ሀሴት እያደረግኩ እኔ ብቻ በልቼ ልሙት ባለማለት፣ ሌሎችም ወንጌል ሰምተው እንዲድኑና አብረው እንዲያመልኩ እሰጣለሁ። ቀድሞውኑም ለራሳችን ሞተን ለእግዚአብሔር እንድንኖር ነው የሞተልን። የእኔ የሚባል ህይወት የለንም።ስለዚህ ከመስቀል በኋላ "በልቡ እንዳሰበ" ነው እንጂ ከ100 አስር አይደለም። እኛ ደግሞ የክርስቶስ ልብ ስላለን ከመቶ መቶ ነው የምንሰጠው።

በአንድ ጉባኤ ውስጥ አንድ ሺ ሰው ተገኝቶ አንድ ሺ ሰው ዘርቶ ከመካከል ሁለት ሰው ወጥቶ "ይገርማችኋል ባለፈው መቶ ሰጥቼ እቤት ስሄድ አንድ ሺ አገኘው" ስላለ እውነት ይመስለናል።ይሄ ሰው የዛን ቀን ባይሰጥም የተዘጋጀለትን ከማግኘት አይጎድልም። ሌላውስ የእግዚአብሔር ልጅ አይደለም? የሚሰራ ከሆነ ለሁሉም ሰው እኩል መስራት አለበት። ብዙ ሰው ልቡ እየዛለ ከእግዚአብሔር ቤት እየሸሸ ነው በህይወቱ ለውጥ ይፈልጋል ግን መንገዱ ትክክል ስላልሆነ አያገኝም፣ ለውጥ የምትፈልግ ከሆነ በልብህ ባለው ደስታና ሙላት አድርግ፡፡ ትርፍ ጠብቀህ በንግድ ሂሳብ ካደረከው ከስረሃል። አንዳንድ ሰው "ከመሬቱ ነው" ይላችኋል። አንዳንዱ ደግሞ "አዘራርህ ነው፣ ቅር እያለህ ስለ ዘራህ ነው" ይላችኋል። ዘር ከሆነ ስንዴ ቅር ብሎህ ዘራኸኝ ብሎ አልበቅልም ይላል እንዴ? "ኮኔክት አድርገህ መስዋዕት ሰዋ" የኢየሱስ መስዋዕትነት አንሶ አንተ ሰውተህ እግዚአብሔርን አታወርደውም። ለእግዚአብሔር የምትሰዋለት የለም እንደውም "ለእኔ የሚሰዋ የውሻ አንገት እንደሚሰብር" ነው ብሎ ዘግቶታል። ራሱ ግን የሰዋው ኢየሱስ የሚባል መስዋዕት አለ ሰማይን ከምድር ያስታረቀ፣ አንድ መስዋእት ብቻ ነው አንድ ያደረገን "ስትሰዋ ሌላ ብዙ የምትሰዋው ይበዛልሃል" አይበዛም፡፡ "መኪና ብትሰጥ አውሮፕላን ይሆንልሃል" አይሆንም። እግዚአብሔር አስማተኛ አይደለም። እያንዳንዳችን ሒደታዊ የሆነ ለውጥ ውስጥ ነን (በነፍሀ) አንተ ስትቀየር ነው ኢኮኖሚህ እራሱ የሚቀየረው። በረከት ያለው አንተ ውስጥ እንጂ የምትሰጠው ነገር ላይ አይደለም። የአንተ አእምሮ ሲቀየር ነገሮችን እንደ ማግኔት መሳብ ትጀምራለህ። የአንተ በአእምሮ መለወጥ ነገሮችህን ይለውጣል።

በኢትዮጲያ የመንግስት አሰራር ውስጥ ዲፕሎማ ያለው ሰው እና ዲግሪ ያለው ሰው እኩል ነው ደሞዛቸው? ዲፕሎማ ያለው ሰው 1000 ብር ስለዘራ ከዲግሪው የበለጠ

ይከፈለዋል? እግዚአብሔር ቁማር አያውቅም። ይሔ ሰው አንድ ሺህ የሚዘራበትን ተምሮ ዲግሪ ላይ ቢደርስ ደሞዙ እኩል ይሆናል፡፡ በህይወታችሁ ላይ ምትሀት አትጠብቁ። እግዚአብሔርን እያወቃችሁ በሄዳችሁ ቁጥር ህይወታችሁም በዛው ሂደት ውስጥ ነው እየተለወጠ የሚሔደው። በመጀመሪያ ደረጃ እግዚአብሔር በፋይናንስ አይለካም። ለምን? አንተ ዘርቼ ይሄን ያህል ሚልዮን ብር ላይ ደረስኩ ስትል ከአንተ የሚሻል ጌታን የማያውቅ ብዙ ህዝብ አለ፡፡

አንዳንዶች ደግሞ ዘር አትቀላቅል ይሉሀል።መጽሐፍ ቅዱስ ሲነግረን በዘሌዋውያን ዘር አትቀላቅል ብሎ ለካህን ተናግሯል። አንድን ገበሬ ሔዳችሁ ዘር አትቀላቅል ትሉታላችሁ፤ ዘር ሳይቀላቅል መዝራት የገበሬው ድርሻ ነው። መሬቱ ምን አጠፋ? እግዚአብሔር መሬቱን የተቀላቀለ ዘር አታብቅል ብሎታል? አላለም። እናንተ የእግዚአብሔር እርሻ ናችሁ ብሏል መጽሐፍ ቅዱስ። የእግዚአብሔር እርሻ ከሆንክ እግዚአብሔር መጥቶ ሲዘራብህ መቀበል ብቻ ነው።አንተ አይደለህም ችግሩ ዘሩን የያዘ አለ። አትቀላቅል የተባለው ዘሪው እንጂ የሚዘራበት ሰው አይደለም። ስለዚህ ህዝቡ ሳይሆን መሪዎች ናቸው በህዝቡ ላይ የሚዘራውን ዘር አጣርተው መዝራት ያለባቸው። እርሻ ከሆንክ ተቀባይ ነህ። የእግዚአብሔር እርሻ ደግሞ ምንም አይነት ዘር ቢዘራበት የሚያፈራው የእግዚአብሔር የሆነውን ነው።ምክንያቱም የመሬቱ ባለቤት እግዚአብሔር ነው። የማንም ዘር አንተ ላይ አይበቅልም የእግዚአብሔር የሆነው ብቻ ነው የሚበቅለው። ደስ ብሎህም ሆነ አዝነህም ብትዘራ ዘር ከሆነ ትርፍ ልታገኝ የግድ ነው። ውጤትማ ከሌለው በመንፈሳዊ ዓለም ላይ ይህ መርህ ተቀባይነት የለውም ማለት ነው።ተቀባይነት ያለው በልብህ እንዳሰብክ ደስ እያለህ ሀሴት እያደረግህ መስጠት ነው።በአዲስ ኪዳን ስለተባረክን እንሰጣለን እንጂ ለመባረክ አንሰጥም።ምክንያቱም በክርስቶስ ያልተሰጠን ስለላለ። አንዳንዶች ይህን እውነት ሲማሩ እርግማን ከሌለበት ለምን እሰጣለሁ ብለው እርግፍ አድርገው ይተዋሉ።ነፃነት የምትወጣው በነፃነትና በሃላፊነት ስሜት እንድትሰጥ እንጂ ነጻነትህ ላለመስጠት ነጻ ያድርግህ።

## እምነት በብሉይ ኪዳን፣ በመንግስቱ ወንጌል እና በ አዲስ ኪዳን

በብሉይ ኪዳን እምነት የሚባል ነገር አትጠየቅም። እምነት ከሙሴ ሕግ በፊት አብርሃም ጋር ነው ያለው። "አብርሃምም አመነ እምነቱም ጽድቅ ሆኖ ተቆጠረለት" ይላል። አብርሃም ያመነው እግዚአብሔርን ነው። የአብርሃም እምነት በነገሮች ላይ ሳይሆን ነገሮችን በሚሰራው በእግዚአብሔር ላይ ያለ እምነት ነው።የሮሜ መጽሐፍ

ጸሐፊ ጳውሎስ ሲነግረን "የሳራ ማህፀን ሙት እንደሆነ በእምነት ሳይደክም ተመለከተ። ለእግዚአብሔር ክብር እየሰጠ በእምነቱ በረታ እንጂ ባለማመን ምክንያት ተስፋ አልቆረጠም" ይላል።አብርሃምን ምንድነው ያመነከው ብላችሁ ብትጠይቁት ሁለት ነገር ይላቹሀል። አንደኛ እግዚአብሔር ልጅ እሰጥሃለሁ ብሎ በሚሰጠው ልጅ ውስጥ ምን አይነት እምነት የሳራ ማህፀን ሙት እንደሆነ እያየ ሙት በሆነ ነገር ውስጥ ህያው ሆኖ የሚወለደውን ልጅ እየተመለከተ ለእግዚአብሔር ክብር ይሰጥ ነበር። ሁለተኛው ደግሞ የተሰጠውን ልጅ መስዋዕት በማድረግ ነበር የተገለጠው። በዛ ውስጥ ደግሞ የዕብራውያን ጸሐፊ ሲነግረን አብርሃም "ባርደው እንኳን ይነሳል ብሎ አምኖ ነበር" ለምን ዘር በይስሃቅ ይጠራልሃል ተብሎ ነበር። ይህን ጳውሎስ በሁለት ቃል ጠቅልሎ አስቀምጦታል። "የሌለውን እንዳለ አድርጎ በሚጠራ ለሙታን ህይወትን በሚሰጥ ባመነበት በእግዚአብሔር ፊት የሁላችን አባት ነው" አብርሃም የሞተ ልጄ ይነሳል የሚል እምነት የለውም።

ብዙ ጊዜ የምንሰበከው ዛሬ ብታምን የሞተው ነገርህ ይነሳል ተብለን ነው። በፍፁም አብርሃም እንደሱ አላመነም፤ ነገሮች ይሰራሉ የሚል እምነት ነገሮችን አይሰራም። ብዙ ጊዜ የምንሳሳተው ህይወታችንም አምነናል ብለን ካሰብን በኋላ የማይሰራው ያመነው ወይ ቤት እንዲሰጠን ነው፣ ያመነው ወይ መኪና ለማግኘት ነው። በነገሮች ላይ ያለን እምነት ፍሬ የለውም። አብርሃም ያመነው የሌለውን እንዳለ አድርጎ በሚጠራ እንጂ በሚጠራው አይደለም። የአብርሃም እምነት የሞተ ይነሳል አይደለም፣ የሞተን የሚያስነሳ አለ ነው። የአብርሃም እምነት የጎደለው ነገር ይሞላል አይደለም፣ በጎደለው ነገር ላይ የሚሞላ አለ ነው። አይኖቹ ሞይው ላይ እንጂ አይኖቹ ቦሃቃው ላይ አልነበረም። ሙት የሆነ ማህፀን አይቷል ነገር ግን ይወለዳል ብሎ ያለ አለ። የሌለን እንዳለ አድርጎ የጠራ አለ ብሎ የጠራን ያከብር ነበር። ወንድሜ፣ እግዚአብሔር ላይ ያለህ እምነት እንጂ የሚሰራው ነገሮች እንዴት እንደሚለወጡ ያለህ እምነት አይሰራም። በሽታህ እንዲፈወስ ብታምን አይሰራም፣ አትፈወስም። እምነት የተሰጠህ በሽታን የሚነቅል አለ ብለህ በነቃዩ እንድታምን ነው።

የብዙ ሰው እምነት- አምነት ሳይሆን ተስፋ ነው። ተስፋ ደግሞ ነገሮች ሊሆኑም ላይሆኑም ይችላሉ ግን ይሆናሉ ብሎ ተስፋ ማድረግ ነው። ዕብራውያን ምዕራፍ ፲1ን ስናነብ ደግሞ "እምነት ተስፋ ስለምናደርገው ነገር የሚያስረግጥ የማናየውንም ነገር የሚያስረዳ" ነው ይላል። በመጀመሪያ እምነት አንተ የምታምነው ነገር አይደለም። ሰው ማመን የሚባል ነገር አይችልም:: የሰው እምነት በአምስቱ የስሜት ህዋሳት ነው። ከዚህ ውጪ የሰው እምነት የለም። አንዳንድ ሰው በእምነት ይህን አገኘው፣

በእምነት ይህን ገዛሁ ይላል። አንዳንድ አገልጋዮች ለበሽተኛ ይጸልዩና ካልተፈወሰ ስላላመነ ነው ብለው ያለክኩበታል። ኢየሱስ ስላላመናችሁ ነው ብሎ በሰው ላይ ሲሄድ አታገኙትም። ሰዎቹ ኢያምኑም እሱ ግን ስራውን አላቆመም። ባለማመናቸው ምክንያት ብዙ ተዓምራት አልሰራም አለ እንጂ ምንም አላደረገም የሚል ቃል አታገኙም።ያልሰራው ደግሞ ለሌሎች የሚገለጠው ጉልበቱ ሙሉ አልሆነም ነው እንጂ እርሱ እምነት አልባ አልነበረም አልፎ ይሰራ ነበር።ሰው እምነትን ተቀብሎ ወይም ተሰጥቶት ነው እንጂ ሰው እምነት የለውም። እምነት ስጦታ ነው! ። አንዳንዶች በእምነቴ ነው የዳንኩት ይላሉ። እምነትንና ማመንን መለየት አለብን። እምነት ስንል ማንነት ነው ስሙም ኢየሱስ ይባላል። ማመን ደግሞ በጎ ፍቃድ እና በጎ ምላሽ ነው።

በመንግስቱ ወንጌል ላይ ሁለት ሰዎች በእምነታቸው ተመስክሮላቸዋል። ደቀመዛሙርቱ ደግሞ ብታምኑ ይህ ተራራ ተነቅሎ ይሄዳል ብሏቸዋል። አንድ ጊዜ መጥተው እምነት ጨምርልን ሲሉት "የሰናፍጭ ቅንጣት ታህል እምነት ቢኖራችሁ ይህን ተራራ ተነቅለህ ሂድ ብትሉት ይሄዳል" አላቸው። የሰናፍጭ ቅንጣት የምታህል እምነት ቢኖራችሁ ካላቸው የላቸውም ነበር ማለት ነው። ያለው ሰው እኮ ነው ጨምርልኝ የሚለው የሌለው ሰው እኮ ስጠኝ ነው የሚለው። የሰው እምነት አላቸው። አሁን የሰራችሁትን ሽሮ በኋላ እንደምትበሉት እርግጠኛ ናችሁ። የሰው እምነት አይቶ፣ ሰምቶ፣ ዳሶ ነው የሚያረጋግጠው። የእግዚአብሔር እምነት እና የሰው እምነት ይለያያል።የእግዚአብሔር እምነት እዚህ ግዑዙ አለም ላይ ያለ እምነት አይደለም። እምነት የራሱ የእግዚአብሔር አለም ላይ ማለትም መንፈሳዊው አለም ላይ ያለ መንፈስ ነው፤ ማንነት ነው ስሙ ኢየሱስ ይባላል።

ሁለት ሰዎች በአስደናቂ ሁኔታ ኢየሱስን በእምነታቸው አስገርመውታል። አንዱ ሮማዊው መቶ አለቃ ነው። ይህ ሰው ወደ ኢየሱስ መጣና "ልጄ ታሞ ቤቱ ተኝቷል እና ልጄን ፈውስልኝ" አለው። "ኢየሱስም መጥቼ እፈውሰዋለሁ" አለ ሰውየው ግን "ወደ ቤቴ ልትመጣ አይገባህም ቃል ብቻ ተናገር ብልቴናዬም ይፈወሳል። እኔ ራሴ መቶ አለቃ ነኝ፣ 50 አለቃውን ና ስለው ይመጣል ሂድ ስለው ይሔዳል። ከላይ ደግሞ አለቃ አለኝ ና ሲለኝ እመጣለሁ ሂድ ሲለኝ እሄዳለሁ።" አለው፡፡ ኢየሱስ ይህን ሰምቶ "በእስራኤል እንኳን እንደዚህ ያለ እምነት አላየሁም" አለ። ለምንድ ነው በእስራኤል እንዲህ ያለ እምነት ያላየው? በዚህ ሰውዬ ለምን ተገረመ? ።

ሌላኛዋ ደግሞ ሰራብታይቱ ሴት ናት። ልጄን ፈውስልኝ ብላ ወደ እሱ መጣች። እሱ ግን የልጆችን እንጀራ ለቡችሎች መስጠት አይገባም አላት። እሷም "ቡችሎችም

ቢሆኑ የልጆችን ፍርፋሪ ይበላሉ" አለችው። ያኔ ኢየሱስን አቆመችው። ተገረመባትና "እንዲህ ያለ እምነት በእስራኤል እንኳን አላገኘሁም" አለ። ኢየሱስ በእነዚህ በሁለቱ ሰዎች ተደምሞባቸዋል። ከነዚህ ከሁለቱ ውጪ ሌላ አታገኙም። እነዚህ ሁለቱ ሰዎች የተለየ እምነት የነበራቸው እስራኤል ደግሞ እምነት የሌላት ለምንድ ነው? በእስራኤልና በሁለቱ ሰዎች መካከል ያለው ልዩነት ምንድ ነው? ሁለቱም ሰዎች አህዛብ ከመሆናቸው የተነሳ የሙሴ ሕግ የሚባል ነገር የላቸውም፤ ብቸኛ ያላቸው እውቀት ኢየሱስ ብቻ ነው።እስራኤል ደግሞ ያላቸው የሙሴ ሕግ ነው። ኢየሱስ በሽተኛ እንኳን ሲፈውስ፣ "ይህ ሰው ኃጢአተኛ ነው በሰንበት ፈውሷል፤ አንተ ግን እግዚአብሔርን አክብር" ይሉ ነበር። በሰንበት ስለፈወሰ ኢየሱስ ለእነሱ ኃጢአተኛ ነው። ይህ ምን ያህል እውር እንደነበሩ ያሳያል። ይህ ምን አይነት አባባል ነው? በኃጢአተኛ የተፈወሰ ሰው እንዴት እግዚአብሔርን ያመሰግናል? ሕግ ሲያጨልምብህ እንደዚህ ነው የምታስበው። ሁለቱ ሰዎች ግን ያላቸው እውቀት እና የሰሙትም ስለኢየሱስ ብቻ ስለነበረ፣ ቀጥታ ወደ ኢየሱስ እምነት ገብተው ተቀብለዋል። እምነት ማንነት ነው ካልን በገላትያ 3፡22-24 ላይ ያለውን እስኪ እንይ።

"ነገር ግን በኢየሱስ ክርስቶስ ከማመን የሆነው የተስፋ ቃል ለሚያምኑ ይሰጥ ዘንድ መጽሐፍ ከኃጢአት በታች ሁሉን ዘግቶታል። እምነትም ሳይመጣ ሊገለጥ ላለው እምነት ተዘግተን ከሕግ በታች እንጠበቅ ነበር። እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል"

ይህ ጥቅስ ብዙዎችን ግራ አጋብቶአል። ሰው የሚረዳው ህጉ እየጎተተ ይዞት መጥቶ ክርስቶስ ጋር እንደሚያደርሰው ነው።መጀመሪያ በተጻፈበት በግሪክ የተጠቀመውን ቃል ሄዳችሁ ስታነቡት ክርስቶስ እስኪመጣ እንጂ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ አይልም፡፡ ወደ ክርስቶስ ሰዎችን የሚያመጣው መንፈስ ቅዱስ ነው። ሕግ ግን ክርስቶስ እስኪመጣ ብቻ ነው እንደውም "END" ነው የሚለው። ይህን "ኢንድ" የሚለውን ትርጉም በ "ኮንኮርዳንስ" ሄዳችሁ ስታነቡ "EXPIRED" ያደረገ ነው የሚለው። ኤክስፓየርድ ያደረገ ማለት ዴት ላይኑ ያለፈበት ማለት ነው። እንዲህ አይነት ምግብ ስትበሉ ወዲያውኑ በህይወታችሁ ላይ ህመም ወይም መመረዝ ነው የሚያጋጥማችሁ። ልክ እንደዚሁ አዲስ ኪዳን ላይ ሙሴን ስትቀላቅሉትም መንፈሳዊ መመረዝ ያጋጥማችኋል። ምክንያቱም የቆይታ ጊዜው አልፏል። የሙሴ ሕግ መስቀሉን አይሻገርም።

በዚህ ክፍል ሞግዚት ተብሎ የተጠቀሰው “ፓይዳጎጎስ” የተባለ ሰው ነው። ፓይዳጎጎስ “ስኩል ማስተር” በግሪክ የቤት ውስጥ ሰራተኛ ተብሎ የሚቀጠር ሰው ነው። እኛ የቤት ውስጥ ሰራተኛ የምንቀጥረው ምግብ እንዲያበስሉልን፣ ቤት እንዲጠርጉልን እና ሌሎች ስራዎች እንዲሰሩልን ነው። በእስራኤል ግን ፓይዳጎጎስ የሚቀጠረው ቤት እንዲጠርግ ሳይሆን አንድ ሰው ህፃን ልጅ ወልዶ ለዛ ልጅ ተብሎ የሚቀጠር አለ የተባለ ምሁር አስተማሪ ነው።ያ ምሁር የተባለ ሰውዬ የሚቀጠረው ጫማ ማሰር፣ ንፍጥ መጥረግ ብቻ ሳይሆን ፊደል እንዲያስቆጥረው እና ለአቅመ ትምህርት እንዲያደርሰው ነው። እናም ይህ ሰው የሚያስተምረው ህፃን ፊደል ለይቶ ትምህርት ቤት እስኪገባ ድረስ እዛ ቤት ውስጥ ደሞዝ ሳይከፈለው ነው የሚኖረው። ልክ ህፃኑ የመጀመሪያ ትምህርት ቤት በሚሄድበት ቀን ፓይዳጎጎስ ደግሞ የቆየበትን ዓመት ክፊያ ተቀብሎ ይሰናበታል፤ ተመልሶ ወደ እዛ ቤት አይመጣም። እንግዲህ ጳውሎስ ሕግን ነው ፓይዳጎጎስ (ሞግዚት) ብሎ ያስቀመጠው። ያ ማለት ሕግ ክርስቶስ ሲመጣ በሰላም ተሸኝቷል፣ ተመልሶ አይመጣም።ስለዚህ ቤተክርስቲያን ውስጥ እንዳታስገቡት፣ ካስገባችሁት ይመርዛል።

እምነት ላይ ነው ያለነው።ብዙ ሰው ስለ እምነት ሲነሳ ዕብራውያን ምዕራፍ 11ን ነው የሚያነሳው። ዕበራውያን ምዕራፍ 11 የብሉይ ኪዳን ጥቅስ ነው፤ አስራ ሁለት ደግሞ የአዲስ ኪዳን ጥቅስ ነው።ዕብራውያን ምዕራፍ 11 የእምነት አባቶች የሚባሉትን ነው የሚዘረዝረው። እነዚህ ሁሉ የተሰጠውን የተስፋ ቃል ሳይወርሱ በእምነታቸው ተመስክሮላቸው ሞቱ ብሎ ይዘጋል። ምክንያቱም እግዚአብሔር ለእኔ ለእናንተ የሚሻል ነገር አይቶአልና። እነርሱ ተመስክሮላቸው ከርቀት ተሳልሞውት ሞቱ። በበረሀ ሄደው፣ በመጋዝ ተሰንጥቀው፣ በአንበሳ ድል ተበልተው ሞቱ።ዕብራውያን ምዕራፍ 12 ላይ ስንገባ ግን “የእምነታችን ጀማሪና ፈፃሚ የሆነውን ክርስቶስን ተመልክተን …”። የእምነት አባቶችን ለእኛ እንደምሳሌ አነሳቸው እንጂ ፈጽሞ በእነርሱ እንድንኖር አልነገረንም። የሚነግረን እነዚህ ሁሉ እንደደመና በዙሪያችን ካሉልን እኛ ደግሞ ቶሎ የሚከበንን ኃጢአት አስወግደን የእምነታችን ጀማሪ እና ፈጻሚ የሆነውን ክርስቶስን ተመልክተን በፊታችን ያለውን ሩጫ በትዕግስት እንድንሮጥ ነው። አየህ እምነት ክርስቶስ ጋር ተጀምሮ አልቋል።የእምነት አባቶች ተመስክሮላቸዋል ግን ያልወረሰ ሰው ምሳሌ አይሆንህም። ጀምሮ የወረሰ ኢየሱስ ብቻ ነው። እነዚህ ሁሉ አሉ ነገር ግን አንተ ኢየሱስን እያየህ ሩጥ። ሞዴልህ ኢየሱስ ነው።

ብዙ ሰው የሚቸገረው እንደዚህ ነው ጌታን አምኖ በእምነት ወደ ቤተክርስቲያን የመጣ ይመስለዋል። ማንም ሰው በእምነት ወደ ቤተክርስቲያን አልመጣም በማመን እንጂ። "ጸጋው በእምነት አድኖአችኋል" ። ብዙ ሰው ይህን ጥቅስ የሚረዳው፣ ጸጋው ከእግዚአብሔር ዘንድ እምነት ደግሞ ከራሱ እንደሆነ አድርጎ ነው። እናም የእግዚአብሔር ጸጋ እና የእሱ እምነት ተደምሮ ደህንነት እንዳገኘ ነው የሚመስለው። በፍጹም እንደዚህ አይደለም። የእግዚአብሔር ጸጋ ልዕለ ተፈጥሮአዊ ኃይል ያለው በእግዚአብሔር ሉአላዊነት ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር ስራ እና አቅርቦት ነው። የማይታየው እግዚአብሔር የማይታየው መንፈስ አለም ላይ ስለአንተ የከፈላቸው ድንቅ ድንቅ የሆኑ የመስቀል ስራዎቹ አሉ። እኛ ካላየን አናምንም፤ በአምስቱ የስሜት ህዋሳቶቻችን ነው የምናምነው። ስለዚህ የማናየውን ነገር ለማመን የግድ የምናምንበትን እምነት መስጠት አለበት።ጳውሎስ በሮሜ 10፡8 ላይ "የምንሰብከው የእምነት ቃል ነው" ብሎናል። ቃሉ በተሰበከበት ቅጽበት ራሱ ቃሉ ክርስቶስ ስለሆነ አንተ እየሰማህ ስትመጣ በምትሰማበት ቦታ ውስጥ እምነት ይገባል። ያ የገባው እምነት እጅ ስጥ ይልህና እጅ ያሰጥሃል።የማን? የእግዚአብሔር የራሱ ጸጋ የእግዚአብሔር የራሱ እምነት አንተን ወደ ማመን አመጡህ እና ደህንነት የሚባለው ነገር ተፈፀመ እንጂ በደህንነትህ ስራ ላይ አንተ እምነት አላዋጣህም። እምነት አንተ ካዋጣህ፣ ኢየሱስ + የአንተ እምነት እኩል ይሆናል ደህንነት ይሆናል ማለት ሳሆን። ጸጋው በእምነት ሲል የራሱ ጸጋ የራሱ እምነት ነው። እግዚአብሔር ጸጋን ሰጥቻችኋለሁ ቢል ሰው በምን አይነት እምነት ይቀበለዋል? አይቻልም ለሰው ልጅ ስጦታን ያዘጋጀው ራሱ እግዚአብሔር ነው። እምነት ተሰጥቶን ነው እንጂ የምንኖረው በእኛ እምነት እግዚአብሔርን አምነነው አይደለም የምንኖረው። እግዚአብሔርን በእምነት አንቀሳቅሰው የሚል ስብከት አይሰራም፤ እግዚአብሔር በአንተ እምነት አይንቀሳቀስም። ለምን? ያመንክ ቀን፣ "ወይኔ ይሄ ልጅ እንዴት በልዩ ሁኔታ እንዳመነኝ የሚደንቅ ነው አይልህም" ምክንያቱም ካመንክም ሰጥቶህ ነው። ስጦታ ተሰጥቶህ ስለሆነ ምንም አይነት የምትመካበት ነገር የለህም። "ማንም እንዳይመካ ከስራ አይደለም ፣ የሚመካ ግን በእግዚአብሔር በራሱ እንዲመካ ኢየሱስ ክርስቶስ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችን፣ ቅድስናችን እና ቤዛነታችን በተደረገልን በእሱ ነው" ።በእምነት ይህን ገዛሁ ብላችሁ ያወራችሁ ቀን ተሸውዳችኋል። እምነት ስለሌለህ ነው ብለህ በሰው ላይ የፈረድንም ቀን ከሰው ሁሉ ይልቅ ኮናኝ ሆነናል።

ጌታ ኢየሱስ እንዲህ አለ፣ "ሰይጣን እንደ ስንዴ ሊያበጥርህ መጣ እኔ ግን እምነትህ እንዳይጠፋ ስለአንተ ማለድሁ" የጴጥሮስን እምነት የጠበቀው የክርስቶስ ምልጃ እንጂ ጴጥሮስ በራሱ እምነት አይደለም።

"ነገር ግን ሰው በክርስቶስ ኢየሱስ በማመን እንዲጸድቅ እንጂ በሕግ ሥራ እንዳይሆን አውቀን ስጋ የለበሰ ሁሉ በሕግ ስራ ስለማይጸድቅ እኛ ራሳችን በሕግ ሥራ ሳይሆን በክርስቶስ እምነት እንጸድቅ ዘንድ በክርስቶስ ኢየሱስ አምነናል፡፡" (ገላትያ 2፡16)

ባንተ እምነት አላመንክም በክርስቶስ እምነት ግን አንተ ራስህ እግዚአብሔርን አምነህ ጻድቅ ሆነሃል።የክርስቶስ እምነት የማይናወጥ፣ የማይወጣ፣ የማይወርድ ፍፁም የሆነ እምነት ነው። ለዚህ ነው ጳውሎስ "አመንኩ ስለዚህም ተናገርኩ ተብሎ እንደተፃፈ ይሆን ዘንድ ያው አንዱ የእምነት መንፈስ ስላለን ገልጠን እንናገራለን" ማመንም መናገርም ያለው በዚያው በክርስቶስ የእምነት መንፈስ እንጂ የሰው እምነት በእግዚአብሔር መንግስት ውስጥ ምንም አይነት መዋጮ የለውም።

"ከክርስቶስ ጋር ተሰቅዬአለሁ፤ እኔም አሁን ሕያው ሆኜ አልኖርም ክርስቶስ ግን በእኔ ይኖራል፤ አሁንም በሥጋ የምኖርበት ኑሮ በወደደኝና ስለ እኔ ራሱን በሰጠው በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት የምኖረው ነው" ። (ገላትያ 2፡20)

ምን ዓይነት ንግግር እንደሚናገር ተመልከቱ፣ ኢየሱስ በስጋ ወራት ሲሰቀል አብሮ አልተሰቀለም። ታዲያ ምን እያለ ነው? "በስጋ የምኖርበት" እና በስጋ "የምኖረው" ይለያያል። "በስጋ የምኖርበት" ካለ ሰውየው እየኖረ ያለው የሆነ ቦታ ላይ ነው ማለት ነው። "የምኖረው" ካለ ግን የራሱን ኑሮ ነው። ብዙ ሰው ግን በስጋ የምኖረው ብሎ ነው የሚያነበው። በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለኝ ሳይሆን "በእግዚአብሔር ልጅ ላይ ባለ እምነት" ነው የሚለው። እምነት ያለው የእግዚአብሔር ልጅ ክርስቶስ ላይ ነው። ይህም ማለት ክርስቶስ አለህ ማለት እምነት አለህ ማለት ነው። ምን አይነት እምነት? ሰማይና ምድርን አንድ ያደረገ እምነት ነው ያለህ። አንተን በእግዚአብሔር ፊት ያጸደቀ እምነት ይዘህ እንዴት መኪና አይገዛም ብለህ ታስባለህ፡፡ የትኛው ነው የሚበልጠው? ።

> *"የኢየሱስ ክርስቶስ ባሪያና ሐዋርያ የሆነ ስምዖን ጴጥሮስ፣ በአምላካችንና በመድኃኒታችን በኢየሱስ ክርስቶስ ጽድቅ ካገኘነው ጋር የተካከለ የክብር እምነትን ላገኙ፤" (2ኛ ጴጥ 1፡1)*

ጽድቅን የተቀበልከው ሰርተህ ነው ወይስ ተሰጥቶህ ነው። ካገኘነው ካለ ወይ ወድቆ ነው ያገኘኸው ወይ ተሰጥቶህ ነው እንጂ ሰርተህ አታገኝም። ጴጥሮስ ይህን

የሚጽፈው በክርስቶስ አምነው ለሚኖሩ ለተበተኑት አይሁድ ነው። ከተሰጠን ጽድቅ ጋር የተካከለ የሆነውን የክብር እምነት ላገኙ ነው። እምነትን አግኝተህ ነው፤ እምነት ተሰጥቶህ ነው። ባለማመንህ አይደለም ያልተፈወስከው። ወጥተህ የምትመሰክረው ነገር የለህም ማለት እምነት የለህም ማለት አይደለም፤ እምነት እንዳለህ ስላላወቅህ ነው እንጂ። አሁን እምነት እንዳለህ ሰምተሃል፣ ይህ እምነት ከዚህ በኋላ ላንተ ይሰራል። የክርስቶስ ኢየሱስ እምነት በእግዚአብሔር ፊት አጽድቆናል፣ በእግዚአብሔር ፊት ፍፁም አድርጎናል፣ የእግዚአብሔር ልጅ አድርጎናል። ሁላችን በእምነት በኩል የእግዚአብሔር ልጆች ሆነናል። ልጅ ያደረገህ እምነት እዚህ ምድር ላይ የሚያስፈልግህን እያንዳንዱን ነገር በመስጠት አብሮህ ነው። በመስጠት በማካፈል በዛ እምነት በማኖር አብሮህ ነው።ይህ ደግሞ የክብር እምነት ነው። እምነት ስለሌለህ ነው ያልተፈወስከው ሲሉህ አትቀበል። እምነት እራሱ ስራ ከሆነ ከሕግ አይለይም። እምነት ስራ አይደለም፤ እምነት ስጦታ ነው።ክርስቶስ ያለው ሰው ሁሉ እምነት አለው። እምነት ተሰጥቶን እንጂ ሰርተን አላገኘነውም ።